# ላንዳፍታ

በፍቅር፣በሰላም፣በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ፣
መቻቻል

መጋቢት ፲፱፻፹፮
፪ኛ ዓመት ቁጥር ፬
$2.75

የአማርኛና የእንግሊዝኛ የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በየሁለት ወር የሚታተም

## "ዕርቅና ሰላም በኢትዮጵያ"



ዶክተር በየነ ጴጥሮስ



Former President Jimmy Carter

ከአትላንታው ስብሰባ ተሳታፊዎች በከፊል



የደቡብ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ግንባር ተወካዮች

In This Issue:
"Mockery on Democracy"
"The Ethics of Ethnocentrism"

### በዚህኛው እትም

- የአትላንታው ስብሰባ ውሳኔና የኢህአዴጉ መሪ መልስ
- በቅርብ ከኢትዮጵያ የደረሱን ዜናዎች
- ከዶክተር ታዬ አንደበት

ኑሮ በአሜሪካ
ዕጣዬ
የዴብራ ጦስ

ል
ብ
ወ
ለ
ድ

# LANDAFTA

*An Amharic & English Ethiopian Cultural Bi-monthly Magazine*
*(Amharic is the official language of Ethiopia)*

March, 1994 Vol. 2. No. 4



# የኢትዮጵያ መንደር







## ETHIO VILLAGE

### CAFE & RESTAURANT

**3462 N. Clark St.**
**Chicago, IL 60657**
**(312) 929-8300**

CATERING AND CARRY OUT AVAILABLE



ቀይ ወጥና ዝግኑ ዶሮ ወጥ አልጫው፤
አትክልት ከሥጋ ጋር ምንቸት አብሽ ክትፎው።
የአበሻ ዳቦና ቆንጆ የማር ጠጅ፤
ሽታው ግቡ ይላል ሳይገቡ ከደጅ።
ቆርጠው በሩን ከፍተው ገባ ሲሉ ገና፤
አገር ቤት የገቡ ያስመስላልና።
የሰኞ ዕለት ዱለት የበግ ወጥ ፍትፍቱ፤
ረቡና ዓርብ ዕለት የጾም በያይነቱ።
በስምንት ዓመት ልምድ የሙያ ክምችት፤
ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ዝግጅት፤
ኢትዮ ቪሌጅ ይምጡ ሲያሻዎት መደሰት።

# ማ ው ጫ

# CONTENTS


2 ከአዘጋጁ

4 ደብዳቤዎች

8 እንዲህ ሆነ
በካርተር ማዕከል የተደረገው ስብሰባ
ኢትዮጵያ ከሰላሙ ጉባኤ ወዲህ (ከኢትዮጵያ ወኪል)

15 ኢንተርቪው
ከዶ/ር ታዬ ወልደሰማያት አንደበት

23 ልብ ወለድ
"የዴብራ ጦስ" (ገረሱ)

26 ኑሮ በአሜሪካ
ቢል ካምብል ለኢትዮጵያውያን ሰርቲፊኬት ሰጡ።
የአትላንታ ኮሚኒቲ ማህበርን ማጠናከር
"ዕጣዬ" (አብረኸት)

28 አዳምና ሔዋን
"ምን ትመክሩኛላችሁ?" (እ.ለ.)
"አላለልኝ ይሆን!" (ትዝታ አለብኝ)

35 ENGLISH COLUMNS
"Human Rights in Ethiopia"
"The Ethics of Ethnocentrism"
(Dechassa D.)
"Mockery on Democracy"
(The Jebessas)
"A Sense of Identity"
(Birhane Worku)
"The Lost American Dream"

44 የአበው ቅርስ

45 የግጥም ጉባኤ

45 ቢስቁም ባይስቁም

46 ጨዋታና ስንጠረዥ




ዶ/ር ታዬ ወልደ ሰማያት (15)



ሚ/ር ማይክል ላንግፎርድ (26)



ወጣት ብርሃኔ ወርቁ (40)

የሽፋን ፎቶ – ፕሬዚዳንት ካርተርና የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ተወካዮች


"ላንዳፍታ" የግል መጽሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጆቹን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የጸሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።
©COPYRIGHT LANDAFTA 1994

ላንዳፍታ
መጋቢት ፲፱፻፹፮
፪ኛ ዓመት ቁጥር
LANDAFTA
March, 1994 V. 2 - No. 6

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*
**Contributing Editors**
*Girma Zegaye*
*Abera Sisay*
**Editorial Advisors**
*Dr. Abera Molla*
*Haile Demissew*
*Solomon Melesse*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*
*Zelleke Nigatu*
**Editorial Assistant**
Woinishet Bekele

**Distribution**
Atlanta, GA
California Mart
Taste of Ethioipia
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
E.C.A.C.
Tesfaye B. (Hoddo)
Yeshi Gessesse
Denvers, CO
Tibeb Taye
Dallas, TX
ET. Beauty Supply
Hartford, CT
Dr. Tilahun G. Hiwot
L.A., CA
K RAH Market
New York
Gion Ethiopian Rest.
Oak Land, CA
Albo-African Shop
Seatle, WA
Amy's Merkato
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Bayibih Medlu
Washington D.C.
Addisu Gebeya
Family Food Market
Merkato Market
Nini Market
Indian Super Market
San Diego, CA
Hotel Sandiego Gift Shop
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu

Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
Phone/Fax (404)728-9122

# ከአዘጋጁ

"እውነተኛ ሰላም ማለት የጦርነት አለመኖር ማለት ብቻ አይደለም። እውነተኛ ሰላም በሰዎች አዕምሮና መንፈስ ውስጥ ያለ ነው። ሰላም ማለት ፍርሃትና ጭንቀት የሌለበት ሁኔታ ማለት ነው። ሰዎች የረዥም ጊዜ ዕቅዳቸውን ነድፈው ያለምንም ችግርና ጥርጣሬ ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን በመጠቀም በተግባር የሚያውሉበት ሁኔታ ነው። ሰላም አለ የሚባለው ተግባር ላይ ውሎ ባለው ሕግና ፍትሕ ላይ ሙሉ እምነት ሲኖር ነው።"

"ሰላም እያለ ስለ ሰላም መጥፋት ያወራሉ፤" እየተባለ ለሚሰነዘረው አባባል ትምህርት ቢሆን ይህችን ብለናል።

ከታሪካዊው የታህሣሡ የሰላምና ዕርቅ ጉባኤ ማግስት ጀምሮ በኢትዮጵያ የፖለቲካ አየር ትንሽ መልኩ ለወጥ ያለ ይመስላል። በተለያዩ ድርጅቶች ስብስብ የተፈጠረው የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት መቋቋምና ተግባሩን ከዚያው ከአዲስ አበባ በይፋ መጀመር፤ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ይህን ምክር ቤትና ተቃዋሚ ኃይሎችን በአትላንታ ለውይይት መጋበዝ፤ በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የበለጠ መግባባት መፈጠር፣ ወዘተ... በዚህ ባለፈውና ባሁኑ ወር በኢትዮጵያውያን መካከል የሚወሩ አበይት ርዕሶች በመሆናቸው ይህንኑ ሰፋ ባለ መልኩ በዚህ እትም አቅርበናል።

የመጽሔታችንን ይዘት አድማሱን ሰፋ ከማድረግና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ገጾች ከመክፈት በቀር ቀደም ሲል የነበሩ አምዶቻችን እንደተጠበቁ ናቸው። የዝግጅት ክፍላችን በአገራችን ባለው አሳሳቢ ሁኔታ ትኩረት በመስጠት ዜናና ኢንተርቪው እንዲሁም ከምሁራን የሚላኩልንን መጣጥፎች ያቀርባል። እባካችሁ አስተያየታችሁን ላኩልን።

"በፍቅር፣ በሰላም፤ በአንድነት ተከባብሮ ለመኖር መደማመጥና መቻቻል!" የሚለው መርሆአችን ሁሌም እንደተጠበቀ ነው፤ የዕድገት መሠረቱ እሱ ነውና።

## GOOD NEWS

*Expanding its scope of readership, LANDAFTA has added English Columns to its pages begining with this issue. The magazine's major medium of publication will still remain to be Amharic. We would appreciate if contributors send their articles focusing specific areas pertaining to:*

- *Ethiopians Abroad - Lifestyle & Adaptation*
- *Ethiopian Society & Culture*
- *News & Views on Current Ethiopian situation*
- *The Cause of peace and national unity*
- *The National Economic Development*
- *Ethiopian Environmental Issues*

*NB. LANDAFTA reserves the right to edit, summerize, accept or reject wholly or partially the articles sent. Views expressed on the articles published are solely the responsibility of their respective authors.*

*Landafta is an independent magazine published in Amharic and English bi-monthly. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# FROM THE EDITOR

*"A condition of true peace is much more than the absence of armed struggle. True peace lies in the minds and hearts of people. Peace is also freedom from fear and worry. Peace is a condition that enables people to have long term plans with confidence to utilise their physical, intellectual and spiritual resources. Peace is confidence in the rule of law and in due process."* *(taken from EHRCO , Sixth Report)*

# The Road to Peace and Democracy

## The first step!

Ethiopians abroad and at home have been preoccupantly following the meeting held at the Carter Center. Everyone had a barrel full of questions in mind: Are we going to get relieved of the problems at last? Is peace truly going to prevail in Ethiopia finally? Are all opposition forces ready to come to a round table discussion at last? Is EPRDF going to have a tete-a-tete discussion with its opponents? What happened at the Carter Center? Is this a break-through or a bottle neck in the post-communist politics of Ethiopia?

Curious Ethiopians elsewhere made many phone calls to their friends in Atlanta to know about the meeting. Atlanta once more became a focal point. Everybody was anxious and curious to know what the outcome of this meeting would be.

Former President Carter with his persistent effort to initiate lasting peace in Ethiopia organized this meeting despite the ruling EPRDF's outright opposition. The meeting, according to many participants, was one in which cognizance and understanding prevailed. All forces had a chance to explain their concerns and positions: their desire for true peace and democracy. They had the chance to bring to the world the present predicament of the country. They had the chance to reveal the fear they have with regards to the dangers of the current ethnocentric political process in Ethiopia. Former President Carter had the chance to know the true picture. He also had the chance to hear what the opposition forces had to say - a chance he never had before. In the past he listened what EPRDF had to tell him.

The meeting of February 6 to 8 at the Carter Center consisted of worthwhile discussions on the restraints existing towards peace and democracy in Ethiopia. To build a credible democratic political setup, it was agreed that all political forces including the EPRDF should come to an open discussion, a domain where not guns but words speak. It was agreed that with the continuous effort of Former President Jimmy Carter, all forces including EPRDF will have a meeting with international observers, (Governments and the United Nations) present. President Carter finally agreed that he will talk to President Meles about it and make the necessary arrangements. What is interesting about this meeting was that all opposition forces agreed to settle the matters peacefully and come to a round table discussion.

This historic meeting created opportunities and challenges not only for the concerned parties but also Former President carter's image which was tarnished by a few unfortunate sequence of incidences that put Ethiopia at odds in 1974. Since then the Ethiopian people have perceived his involvement with searching skepticism and deep resentment. This could offer a turning point for regaining momentum of reconcilement on the part of the Carter Center. Notwithstanding the magnitude of the opportunities and challenges before Dr. Beyene Petros, the Chairman of Alternative Council and his colleagues, it is worth mentioning that EPRDF's sincerity to travel on the road of peace and democracy is in critical test. This is a unique chance the two previous governments did not have: a chance to explain what they stand for confronting its opposing counterparts. Now is the time for EPRDF to take advantage of this opportunity. Military might won't reach us anywhere. EPRDF has to learn from its predecessor. Mengistu's mistake was to completely rely on force rather than peaceful settlement. History has shown that a government that has no sustenance from the people is short lived.

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት እንደምናችሁ?

ዛሬን ውሎ ለነገ ለመድረስ ደፋ ቀና ሲባል ጊዜው በጣም ይሮጣል። ለመሆኑ እንዴት ናችሁ? እንዴትስ ከረማችሁ? ገና እንዴት አለፈ? አዲሱ ዓመትስ እንዴት ነበር? ሁሉን ቻይ የሆነው እርሱ መዳኃኔዓለም ምሥጋና ይድረሰው እኛ ደህና ነን። እነሆ መቆየት ደግ ነው በአቶ ሄሮማን ኮሄን ሽምጋይነት በቻርተሩ የተወሰነልንን የሽግግር ዘመን እኛ ጨረስን ፖለቲከኞቻችን አልጨረስ አሉ። እኛ ግን ድርሻችንን ተወጥተናል። ያልጨረሱት የቤት ሥራ (Home Work) ቢኖር እርሱ ሌላ ነገር ነው። የቤት ሥራ ያልሠራ ተማሪ እንኳ ይንበረከካል። ፈተናም ይወድቃል። መምህሮቻችን እንዲህ ነበር ያስተማሩን! እንኳን ሹም ቀርቶ!መቼስ ሽግግር ማለት ችግር ሲበዛ በችግር የማለት ያህል ነው። በዚች አጭር የሽግግር ወቅት ብዙ አይተናል።

"ዴሞክራሲ" በሽበሽ ነው። በአደባባይ ወጥቶ መሰለፍ፣ ሲጮሁ መዋል ይቻላል። መብት፣ ነፃነት፣ ግዴታ፣ ንግግር ዲስኩር ሞልቷል። ፖለቲካ ወሬ ሀሜት እንደልብ ነው። መንግሥት የሚነቅፍ፤ ባለሥልጣን የሚተች ጋዜጣ መጽሔት ማንበብ (አቅሙ ካለ) ክልካዩ የለም። የፖለቲካ ፓርቲ ለማቋቋም፣ የብሔር ብሔረሰብ፣ የዘር የማንዘር ድርጅት ፈጥሮ "ነፃ አውጪ " ነኝ ማሰኘት ጠያቂም የለበትም። ባለታሪክ ማዋረድ፣ የሌለ ታሪክ መጻፍ፣ ታሪክ መናድ፣ ቆርጦ መቀጠል አያስወቅስም፤ አያስከስስም። ስዉ መጀመሪያ ሰሞን ሁሉም የምር መስሎት ያዋጣኛል ባለው መልክ ሮጧል። የሚሰማው ያለ መስሎት ሰልፍ ወጥቶ የቻለውን ያህል ጮኾ ልኩን አይቶታል። ፍርድ ተጓደለብኝ ያለ ተበደልኩ ባዩ ብዙ ኳትኗል። ተራብኩ ያለዜጋ የሀገሩን መሪዎች ሃዘኔታ ለማግኘት የዓለምን ሕዝብ ቀልብ ለመሳብ በረሃብ አድማ ነፍስ ሥጋውን አጐሳቁሏል። ግን የምትሆነው የምትደረገው ያቺው የደንቧ ናት። ከልኩ አታልፍም።

የኔ ቢጤው ተራ ዜጋ ድካምና ፋይዳቢስ የአደባባይ ጩኸት ተረፈው። ይብስኑ ችግር በችግር ላይ ፈላ። መከራ በመከራ ላይ ተደራረበ። ዘር ተቆጥሮ ከተጫረ ዕልቂትና የጉሣ ግጭት ሕይወትን ለማትረፍ እንደ አውሬ በርግገው የመጡ ጉስቋላ ባላገሮች በየከተማው ፈሰሱ። ከኤርትራና ከአስብ ያለ የሌላቸውን ተነጥቀው በስድብና በውርደት የተሸኙ ዜጐች አደባባዩን ሁሉ አጥለቀለቁ። እርጥብ አራስ ከነሕፃኗ ሜዳ ላይ ወድቃ "ስለማርያም" አለች። የሠራዊቱ አባላት ሜዳሊያና ቆባቸውን መንገድ ላይ ደርድረው "ስለወንድ ልጅ አምላክ " አሉ። በዘር በእምነት በጉሣ በሰበብ በአስባቡ ከየመሥሪያ ቤቱ የተባረረው፣ መስሪያ ቤቱ የተዘጋበት ሁሉ እጁን ለልመና ዘረጋ። ውሎ ለማደር ሕይወትን ለማሰንበት ልመና ብቸኛው አማራጭ ሆነ። የሚታፈርበት መሆኑም ቀረ።እምቦቃቅላ ሕፃናት እርቃናቸውን እየሄዱ የተራበ አንጀታቸውን እያሳዩ የፈደል "ሀ ሁ"ን ሳይሆን ረሀብን ቆጠሩ።

ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ፣ ፍንዳታ ቤት አልባ ያደረጋቸው፣ የዘር ነገር ከአገር ያወጣቸው ብዙ ኢትዮጲያዊያን መድረሻ አጡ። ይኖሩ ከነበሩበት ካምፕ ተገፍትረው የተባረሩ የሠራዊቱ ቤተሰብ ሥርቻውን ሁሉ ሞሉት። የቻለ በየአደባባዩና በየአጥሩ ግቢ ሥር የላስቲክ ጐጆ ቀለሰ። ያልቻለ ቡቱቶውን ጠቅልሎ እዋለበት ውሎ ሲመሽ አንዱ ጥግ ኩርትም ብሎ ማደር ያዘ። በየጥጋጥጉና በየሥርቻው የዘላን ጐጆ የመሰሉ የላስቲክ ቤቶች እንደአሸን ፈሉ። አንድ ሰሞን ጉድ ተባለ። በእነዚህ ጐጆዎች ውስጥ የሽግግሩ ዘመን የችግር መዓት ያወረደባቸው ዜጐች የሕይወትን ፈተና ተቋቋሙበት።

ትላንት የራሳቸው ኑሮ የነበራቸው አባወራዎች ልጅ፣ ውሻ፣ ድመት ኰተታ ኰተት ቅራቅንቦ ይዘው የዛሬውን ኑሮአቸውን መሰሉበት። በእነዚህ ጐጆዎች ዙሪያ ሕይወት ዑደቷን ቀጥላለች። ሕብረተሰቡ የሚችለውን ያደርጋል። ሙልሙል ጋግሮ ያድላል። ሽሮ አንተክትኮ እንጀራ ጋግሮ በየጐጆው ያቃምሳል። የሞተ ይቀብራል። የወለደች ያርሳል። ዓውዳመት ሲሆን ለበዓል ያዘጋጀውን ይዞ ሄዶ ይካፈላል። የዋጋ ንረት የሚሉት አባዜ ሁሉን እያደቀቀው እጁ ቢያጥርበትም የኅብረተሰባችን መተሳሰብና መተዛዘን እጅግ ይደንቃል። በዚህ ላይ የመሥሪያ ቤቶች መዘጋት፣ የሠራተኛ ቅነሳ፣ የጉሣ ጦርነቶች እያንዳንዱን ጐጆ በሞትና በሕይወት መካከል አንጠልጥሎ በችግሩ ላይ ሌላ ችግር ደረበበት። በአዲስ አበባ ከተማ በየሰፋሩ የተቀመጡ የቆሻሻ መድፊያ ውስጥ ታፍሶ የተደፋን ቁሻሻ እንደቁራ እየጫሩ ወስፋት የሚያስታግስ ነገር የሚፈልጉ ብዙ ዜጐች ማየት ዛሬ እንግዳ ነገር አይደለም። መከራ ለአፍ ይከብዳል ሆነና ይህ ሕዝብ ሁሉን ችሎታል። ያልቻለ፣ ያልሆነለት ረገፈ። አፈር ገባ።

እንግዲህ እኛ ይህንን እንመስላለን። ሽግግሩን እንዲህ እንዲህ ተወጥተነዋል። እኛ ድርሻችንን ጨርሰናል። የድርሻቸውን ያልጨረሱ ፖለቲከኞቻችን ሰሞኑን ጋዜጠኞች ሰብስበው ኲስተር ብለው የሽግግሩ ወቅት መራዘሙን ነግረዋቸዋል። ጋዜጠኞች እንዴት ይሆናል ብለው አልጠየቁም። የተነገራቸውን እየተንጣጡ ነግረውናል። በቃ! ከእንግዲህ ዓይን ያወጣ የጉልበተኛ ነገር የአንበሳ ሥራ መሆኑ ነው። "አንበሳ ምን ይበላል ቢሉ ተበድሮ፤ ምን ይከፍላል ፣ ማን ተናግሮ? " ይባል የለ።

ለመሆኑ ይሄ ሽግግር እናንተንስ እንዴት አድርጓችሁ ይሆን? በአገር፣ በወንዝ ናፍቆት፣ በዘመድ አዝማድ ፍቅር አሳቀቃችሁ ይሆን? ወይስ ግሪን ካርድ ለማውጫ፣ የመኖርያ ፈቃድ ለማግኘት እሰየው የሚባልበት አጋጣሚ ፈጠረላችሁ ይሆን? በሉ ደህና ክረሙልኝ።

የእናንተው ወርቃየሁ (ከአዲስ አበባ)

# ሰላምታ ከአሜሪካ ይድረስ ለወገኖቻችን!

(በጥር 1986 ወርቃዩሁ ካገር ቤት ለጻፉት መልስ ብጤ)

እንደምን ከረማችሁ ወገኖቻችን? እኛ ቢከፋም ቢለማም ደህና ነን። በእኛም በኩል ዘላባጅ፣ ቀባጣሪ ደንፊ አስፈሪ አንስጋ እንጂ በሁለንተናችን ከናንተው ጋ ነን። ወገኖች፤ ጨዋታውን ከምን ልጀምርላችሁ? እኛማ ለንደን ኮንፍረንስ ሊደረግ ነው ተብሎ የኮንፍረንሱ ተካፋዮች እነማን መሆናቸውን ካወቅንበት ዕለት አንስቶ ከጆሮው አጠገብ ከባድ ፈንጂ እንደፈነዳበት ጆሮአችን ውስጥ ኪል እንዳለብን አለን። ከዚያም ቀጥሎ ኤርትራን አስገንጥዬ አዲስ አበባ ላይ መንግሥት አቁሜያለሁ፣ እኔን የማይመስል ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት እንዲሁም ሌሎች የመንግሥት ተቋሞችን ይጥፋ ብሎ ወገኖቻችንን ለልመናና ቤት የለሽ አድርጐ ከበተናቸው ጊዜ አንስቶ የረባ እንቅልፍ መተኛት አቅቶናል። ለዚህም በደላላነት ለሠሩት አቶ ኮሽን የፕሬዚንዳንት ቡሽ ጉዳይ አስፈጻሚ ከአዋዋሉን አንስቶ ወባ እንደያዘው ሰው ጥርሳችንን እያፋጩን በሕልማችን መሣሪያ ይዘን ወደረሳነው ሽፍትነት ስንሄድ በሌላ በኩል ደግሞ ያን መከራ ያየ ሕዝብ እንዳይበደል በማለት በሌላ ስልት የጠረጴዛ ውይይት ይገባቸው እንደሁ የሱን መዳረሻ (መዛለቂያ) እስከመጨረሻ ለማየት በዚሁ ያልተቋረጠ ትግላችንን ተያይዘነዋል። ሌላማ ቢያምርም ባያምርም ባገር ነው የሚባለው ለማንም ግልፅ ነው።

እኛማ ሌት ተቀን ባለቤቱ እገሌ ነው ተብሎ ለማይታወቀው፣ ምርቱ ትርፉ ለማን እንደሆነ ለማናውቀው ሕንፃና ማሺን ሲያቀባጥረን ይውላል፤ ላንዳፍታ ወደ አገር ቤት በቀን ሕልም ላጥ ብለን የመጣን እንደሆን፤ የሚቆረጠው በደንብ ሳይቆረጥ፣ የሚበሳ ከሆነ ሰፍቶ ወይም ጠቦ፣ የሚደረደር ከሆነ በቁጥር አቸንፎ፣ በመሥመር የሚስተካከል ከሆነ ተወላግዶ ወይም ተዛንፎ፣ የሚቆጠር ከሆነ አንሶ ወይም በዝቶ፣ አለዚያም ማሽኑ እጅህን ወስዶ ሊጐምደው ሲል ወይም የቅርብ አለቃህ እየተንጐራደደ ሲመጣ ከዚያች ከፍራክሽን የቀን ሕልም ብንን እንልና ሁሉን ነገር እረስተን የእንጀራ ጉዳይ ላይ ዓይናችን አፍጠን ሥራውን እንያያዘዋለን።

ወርቃየሁ! የናንተን አያያዝ በጣም ወደነዋል፣ ብዙ ጊዜ በመከራ ማለፍ ምንም እንኳ የሚያደርሰው በደል ከፍተኛ ቢሆንም በአንፃሩ ትምህርት ሰጥቶ ያልፋል፤ ያገሬ ሰው ምንጊዜም ብልህ አይደለም! ቀጥሉበት፤ እኛም ምንም በሰው አገር ብንሆንም እራሳችን ላለመጣል፣ የተማረ፣ ያልተማረ፣ ከከተማ የመጣ፣ ከገጠር የመጣ፣ ቋንቋውን በደንብ የሚያውቅ፣ ምንም የማያውቅ፤ በዚህ ሃገር ውስጥ ተወልዶ ካደገው ጋር ዝንፍ አይልም፤ ይህም የተገኘው አባቶቻችንና እናቶቻችን ባቆዩልን የኢትዮጲያዊነት ኩራት ልምድ መሆኑን አይዘነጋም። ለዚህ አልጠግብ ባይ ሃገር የምናፈሰውን ጉልበትና ልምድ ለተጠማችው ሃገራችን ጠብ እናድርግላት ስንል በጉን ደርሰው እኛን እዚህ ለማስረጀት ይመስላል በሃገራችን ላይ ለ17 ዓመት ሙሉ ስንታገል ሌላ መርዘኛ አሜከላ ተከሉብን።

መቸም እነዚህ ነጮች በዚች ሃገር ላይ ያላቸውን ቂም ሳታውቁት አልቀራችሁም፤ ይህም በተለያዩ ጊዚያት የኢትዮጲያ ሕዝብ የመጣበትን ወራሪዎች ባለው በሌለው የአውሮፓን ጦር ድል በማድረጉ ለዚህም ለምሳሌነት ምኒሊክ በ1896 ዓ.ም. 17,700 የጄኔራል ባራተሪን ጦር በድስት ሰዓት ባልሞላበት ውስጥ ድል ሲያደርግ የለንደኑ Spectator በማርች ሰባት እንዲህ ሲል ጽፏል። "The most notable victory of an African over an European army since the time of Hannibal." ይልና "The Italians have sufferred a great disaster, greater than has ever occurred to a white man in Africa." ይላል። ስለዚህ መድሐኒቱ ኢትዮጲያን በዘር በጐሣ በሃይማኖት አለያይቶ በማሳነስ የኢትዮጲያዊነትን ኩራት ከሕብረተሰቡ በማጥፋት እኛ በኛ ስንራኰት እነሱ ለ3,000 (ለሦስት ሺህ) ዓመት ሲመኟት የነበረውን አላማቸውን የሚያስፈፅሙላቸው የዋሆች ተመቻችተው በመገኘታቸው፤ እኛ አንጀታችን ሲያር እነሱ በውስጥ ይፍነከነካሉ።

ወገኖቻችን ሆይ! መጃጃል አይበጀንም፤ ወገብን በገመድ ጠፍሮ በመድብለ ፓርቲ አማካኝነት የዴሞክራሲን ጮራ ለማየት፤ እኛም ባንችል ልጆቻችን የሚያዩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያለብን መሆኑን ለአንድ ደቂቃም ቢሆን መዘንጋት አይገባም።

በኢትዮጲያ እኛ መርጠን ያላስቀመጥነው መሪ እስካልመጣ ድረስ፣ የሥልጣን መወጣጫው መሠላል ሕዝቡ ሆኖ መውረጃው መሰላልም ሕዝብ መሆን ይኖርበታል። ይኸ በሃገራችን ላይ እስካልመጣ ድረስ የኢትዮጲያዊነት ግዴታችንን ተወጥተናል ማለት አንችልም።

ወገን ሆይ! ዛሬም ቢሆን ቴዎድሮስን ዮሐንስን ሚኒሊክን ኃይለሥላሴን የገጠማቸው ትንንቅ ሕዝባችንን ገጥሞታል። የ17 ዓመቱ ምፅዓት ሌላ መልኩን ይዞ ለሃገሪቱ ሕልውና ሳይሆን ለሃገሪቱ ጥፋትና ቀደም ሲል ያለፍነውን የዘር ሙጃ መልሶ በመዝራት ላይ ይገኛል። ይህ ሙጃ አድጐ አፍርቶ እኛን ከመበተኑ በፊት ከዚሁ መነቀል አለበት። ያ የሚሆነው ደግሞ እነገሌ ያደርጉት ሳይሆን እኔ አለሁ! አንተስ? እናንተስ? ካልሆነ አረም ማርባት እንጂ ጥሩ ፍሬ ማብቀል አይቻልም።

የናንተው ታገስ አላምረው
(ከሴንት ሉስ/አሜሪካ)



# የአንባብያን ደብዳቤዎች



"ላንዳፍታ" መጽሄት አዘጋጆች
በዚህ ወር ማለትም ጥር 1986 የወጣችውን መጽሔት ለመጀመሪያ ጊዜ በማግኘት አንብቢያታለሁ። በጣም የምትማርክ ናት። በተለይ የጣጤው ጽሁፍና የባሻ ወለም ዘለም ጽሁፍ አስደሣች ነው። የሚቀጥለውን ጥሁፋቸሁን በጉጉት እጠብቃሉሁ።
ጥላዬ ፍስሃ (ከዲ.ሲ.)

------------------------------

ይድረስ ለላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጅ ሰላምታዬ ይድረስ በየሁለት ወሩ የምትወጣው ብርቅዬዋ መጽሔት እንኳን ምን ግዜውም ወቅቷን ጠብቃ እጄ እንደደረሰች የምሠራበት አካባቢ እንዲሁም የምኖርበት አካባቢ በአፍሪካ አሜሪካንስ ጉብል የተሞላች በመሆኗና ባህላችውንም ከራሴ ባህል ጋር ለማመሳሰል በሙከራ ላይ ስላለሁ የዴብራ ጦስ ከሚለው ልብወለድ ጋር ናፍቆት ይዞኝ ይሆን በመጀመሪያ ለማየት የጓጓሁት ዓምድ እሱ ስለነበር ከምን ደርሶ ይሆን? ነበር ሀሳቤ ላይ የተጉላላው። አንብቤ ጣዕም ያለው ገፅ ላይ ስደርስ ለካ የታሪኩ ማገባደጃ ላይ ደርሼ ኑሮ "በሚቀጥለው እትም" ላይ ደረስኩ ለዚህ ጽሑፍ ደራሲ ለክብራቸው የሚገባውን ሰላምታ ለጥ ብዬ እጅ እበሳለሁ! ውብ ጽሑፍ. . ወደ እነ ዘለቀ ንጋቱ ባሻ ወለም ዘለም ጽሑፍ ላይ ስደርስም የአቶ ዘለቀ ንጋቱ እኝህ ለባለቤታቸው ወይንም ለሴት እህቶቻቸው ትልቅ ክብር የሚሰጡ ሰው ናቸው። እንዲያው አፌ ቁርጥ ይበል እሰይ አንበሳ ናቸው። ተወዲሁ የባሻ ወለም ዘለም የብዕር ስማቸው ጋር ትንንቅ ያዝኩኝ። በእራሳቸው የማይተማመኑ ሰው ይሁኑ? እጅሬ መቼ በቀላሉ የላቸውን ጽሑፍ ሳነብ ባሻ የሚባል ሰው ከደረቱ ሰፋ ከሆዱ ገፋ ያለና ሽበት ጣል ጣል ያረገበት ሰው ይመስለኝ ስለነበር እንዲያውም "የተማረ ሰው ምክንያት አያጣም፤" ሲሉ እጃቸውን ሰጡ ነበር ያልኩት። ዘራፍ ያሰኛቸው ለካ "ጡንቻ ራስ" መባላቸው በመሆኑ "ጡንቻዬን ከእጄና ከባቴ ላይ ባጣው የት ጠፋ እያልኩ እፈልገው ነበር። እርስዎ በመምህር መነጥርዎ አይተው ራሴ ላይ መሆኑን ስለነገሩኝ አመሠግናለሁ፤" አሉ ባሻ። የመጀመርያ ጽሑፋቸውን ዕድል ገጥሞኝ ባላነበውም "ድስት ግጣሙን አያጣም እንዲሉ" ጌታው ዘለቀን አዘዘባቸው። እንዲያው ለመሆኑ የአማርኛው መሣካት አጣጣሉ ሁለቱም ተከራካሪዎች የአማርኛ ምሩቅ ሳይሆኑ አይቀሩም የሚል ግምት አለኝ። አባባሌ የቋንቋው አከባበድ ጥቂት ምርምር ውስጥ ከተተኝ። ማጠቃለያ ጽሑፌ ስገባ ለባሻ ወለም ዘለም ጽሑፋቸው የመጀመሪያውን ባላነበውም ሁለተኛው ላይ ለቁንጅና ውድድር ተካፋዮች ይቅርታ መጠየቃቸውን ጠቅሰዋል መጽሔትህ ሽፍንሽን ሆናለች። ከፖለቲካው፣ ከመዝናናቱ ከጭቅጭቁ። አሁን በቅርቡ ቀይ ወጥ ነኝ ያሉት ጣጤው ጽሐፊ የእሳቸውም የሚደነቅ ነው። እራሳቸውን ለምን ከጣጤው መድረክ እንዳስገቡት ባይገባኝም በሞቅታ ያነበቡትን ገጽ ሁሉ መልስ አዘጋጅተው መላካቸው ጣጤ አያሰኛቸውም ባይ ነኝ። ሌላው የዴብራ ጦስና የጣጤውም ጨምሮ መጽሔቱን በውበት ላይ ውበት ተከኖበታል። መልካም አመት በርቱ። በቅርቡ ከአገር ቤት የመጣልኝ ደብዳቤ ቴምብሩ ላይ "የመላው አፍሪካ የደስታ በሽታ ማጥፊያ ዘመቻ" ይላል ትርጉሙ ስላልገባኝ ልኬልሀለሁ። ይህ ለባሻ ቀላል ሳይሆን አይቀርም ወይንም ለጌታ ዘለቀ።
ብርሃን አብርሃም (ከዲሲ)

ከአዘጋጁ፤ "የደስታ በሽታ" ማለት የአንድ ዓይነት የእንስሳት በሽታ ስም ነው።

------------------------------

ውድ የላንዳፍታ አዘጋጅ፤– በመጀመሪያ ሰላምታዬ ይድረስህ። በሀገራችን ለሕዝባችን የተስፋ ጭላንጭል በመሆን የጊዜውን የተዛባ የፖለቲካ ውዝግብና በጉሰኝነት ልክፍት እርስ በእርሱ ተከፋፍሎ በመናቆር የተፋጠጠው ሕዝብ ችግር በሠላም መንገድ ለመፍታት፤ የሀገራችንን ዳር ድንበር በመጠበቅ ለክብር፣ ለአንድነት፣ ለሠላም፣ ለዕድገትና ለሥልጣኔ ብሎም የመቶውን ዓመት ሳይሆን የሦስት ሺህው ዓመት ታሪክ በማደስና ማዕከላዊነትን የጠበቀ ምሶሶ አቁሞ ጣራውን በመዋቀር ሁሉንም የብሔረሰብና የፖለቲካ ድርጅቶች ያካተተ የሠላምና የእርቅ ጉባኤ ከታህሳስ 9 ቀን 1986 ዓ.ም. ጀምሮ ለአምስት ቀናት በአዲስ አበባ ግዮን ሆቴል መካሄዱ የሚታወስ ነው። ታዲያ ይህ በናፍቆት ይጠበቅ የነበረውን ጉባኤ ሂደት ለመስማት፤ አንዳንዶቻችን የየደቂቃውና የየሰዓቱን፣ ግማሾቻችን ደግሞ የየቀኑን የስብሰባ እልባት ለመስማት ጥዋት ማታ ስልክ ስንጠባበው በመክረማችን የAT & T ሰለባ ለመሆናችን የቴሌፎን ቢላችን በቂ ምስክር ነው። በዚህም ሳቢያ ጓያ እንደሰብረው የዚሁ ቴሌፎን ዕዳ ወገባችንን ያሽማደደው ግለሰቦች የጉባኤውን የመጨረሻ መቋጫ ደውለን ለማጣራት ባለመቻላችን ወርሃዊ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን ከመጠበቅ በስተቀር ከቶውንም አማራጭ አልነበረንም። በተከታታይ የፕረስ ሪሊዞች ቢወጡም ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት የተፈጠሩትን ክስተቶችና መሰናክሎችን ከመጠቆም በስተቀር ስለ ጉባኤው ሂደት ያወሱት አንዳችም ነገር አልነበረም።ታዲያ "የናቁት ይነግሳል የጠሉት ይወርሳል"እንደሚባለው የብሱንና

ውቂያኖሱን አቋርጦ ዜናውን ከነሆድ ዕቃው በተቻለ መጠን አምጥታ የዘረገፈችልን "ላንዳፍታ" ነበረች። በእርግጥ ሁሉም ጋዜጦችና መጽሔቶች ስለ ጉባኤው የየራሳቸውን ዘገባ አቅርበዋል። ነገር ግን "ላንዳፍታ" ባቀረበችው እጥር ምጥን ያለ ዜና እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙ ጓደኞቼ ስለ መጽሔቷ አድናቆት አውስተዋል። እኔም የመጽሔቷን አዘጋጆች በሙሉ በአንባቢያን ስም እያመሰገንኩ፤ ወደፊትም ስ ሀገራችን ስለ ወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጨለፍ እያደረጋችሁ የምታቀርቡ ከሆነ ብዙ አንባቢያንና ለመጽሔቷ ደንበኞች እንደ አሸን ማፍላት ስለምትችል በተቻላችሁ መጠን ግፋበት እላችኋለሁ።

ጉበዜ መሸሻ (ከዳላስ-ቴክሳስ).

-----------------------------

ለላንዳፍታ መጽሔት አዘጋጅ፤ መጽሔታችሁን እከታተላለሁ። ጥሩ ነው። አሁን አገር ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ማንሳሳት መጀመሯ ጎሽ የሚያሰኝ ነው። ታዲያ የፖለቲካ ጉዳይ ስታነሱ ጠንቀቅ በሉ። አለመዋሸት፣ ደግሞም አንባቢን ለማምታታት አትሞክሩ፤ ሐቁን ጻፉ። ይህን ልል የበቃሁበትን ምክንያት ልገልጽ እወዳለሁ። በውጪ አገር የሚታተሙ የአገራችንን ጉዳይ በተመለከተ የሚጽፉ መጽሔቶችን እከታተላለሁ። የሚያደርጉትን አስተዋጽዖም አደንቃለሁ። ታዲያ በቅርቡ ያየሁት አንድ መጽሔት በቁርጠኝነት ለአገራችን ሕዝብ ነፃነት የሚታገሉትን አንድ ታላቅ ሰው "ፕሬዚዳንት ይሁኑ" ብሎ ጽፎ አይቼ ቅር ስላለኝ ሁላችሁንም ለመምከር ይህን ለናንተ ጽፌአለሁ፤ (ለመጽሔቱም ጽፌአለሁ)። "ይህችን ይህችን አልወዳት!" አለ ኢያጎ። በየዋህነት ተጽፎም እንደሆን ማረም ያስፈልጋል። አለበለዚያ ግን በቁርጠኝነት ለወገናቸው ልዕልና የሚታገሉትን ሐቀኛ ሰው የሚያደርጉትን ትግል ለማኮላሸት የተጻፈ ይመስላል። ሰውዬው የሚታገሉት ለሥልጣን እንደሆነ አድርጐ ማቅረብም ከመምሰሉም በላይ ለተቃራኒ ፕሮፓጋንዳ በጣም አመቺ የሆነ ደካማ አባባል ነው። እንዳትሳሳቱብኝ፤ ሰውዬውን ስለማደንቃቸውና ስለምሳሳላቸው ነው ይህን ያልኩት። ኸረ ለመሆኑ ምኑ ውሉ ተያዘና ነው፣ የትኛው የዴሞክራሲ ሥርዓት ተንሰራፍቶ ሕዝቡ ለምርጫ ተመቻቸና ነው "ፕሬዚዳንት" የምናጭለት? እኛስ እዚህ ሆነን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማን እጪ አደረገንና? ደግሞስ ሰውዬው ራሳቸው ለፕሬዚዳንትነት እጩ ሆኜ ቀርቤአለሁ መቼ አሉና? ኸረ እባካችሁ እየተስተዋለ! በርግጥ በዚህ ዓይነት ታላቅ ተግባር ላይ የተሰማሩትን ውድ ምሁራኖቻችንን አስተዋጽዖአቸውንና ችሎታቸውን ማስተዋወቁና አድንቆ መጻፉ ትክክል ነው። ከዚያ በኋላ ለሕዝቡ መተው። በሐቅ ለአገራቸውና ለነጻነታቸው የሚታገሉትን የድርጅት መሪዎችና ምሁራንን ለሥልጣን እንደሚታገሉ አድርጎ የሚያስወራ ሁሉ እስካሁን ያየሁት ከጠላት ካምፕ ብቻ ነው። እና ለዚህ ዓይነቱ የጠላት ተራ ፕሮፓጋንዳ መሣሪያ እንዳንሆን ተጠንቀቁ እላለሁ። ገዳሙ በላይ (ከዲ ሲ)

-----------------------------

# ማሳሰቢያ

በላንዳፍታ መጽሔት ላይ እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉት መጣጥፍ፤ ደብዳቤ፣ ማስታወቂያና የመሳሰሉት ሁሉ ለዝግጅታችን ክፍል የሚደርሱበትንና መታተም የሚችሉበትን ጊዜ በማስመልከት ይህን እናሳስባለን።

ለSept እትም በ August መጀመሪያ ሳምንት
ለNov እትም በ Oct መጀመሪያ ሳምንት
ለJan እትም በ Dec መጀመሪያ ሳምንት
ለMarch እትም በ Feb መጀመሪያ ሳምንት
ለMay እትም በApril መጀመሪያ ሳምንት
ለJuly እትም በ June መጀመሪያ ሳምንት

በመጽሔቱ ላይ እንዲወጣ ለምትፈልጉት የግል ዜናዎች የሚቀጥሉትን ይመልከቱ።

**ዜና ዕረፍት -**
የሟቹን ጉርድ ፎቶ ከአራት መስመር ባለበለጠ አጭር የሕይወትረ ታሪክ ጋር
የአገልግሎት ዋጋ - $30.00 ብቻ

**ዜና ሠርግ -**
የተጋቡትን ሰዎች ፎቶ (አንድ ላይ) ከሶስት መስመር ካለበለጠ ዜና ጋር
የአገልግሎት ዋጋ - $30.00 ብቻ

**ዜና ልደት -**
የተወለደውን ሕፃን ፎቶ ከሁለት መስመር ካልበለጠ ዜና ጋር (የአባትና የእናት ስም ተጨምሮ)
የአገልግሎት ዋጋ - $25.00

**ዜና ምረቃ -**
ትምህርቱን የጨረሰው/ችው ግለሰብ ፎቶ ከመመረቂያ ልብስ ጋር፣ የተመረቀበትን ትምህርትና ት. ቤት ከሚገልጽ 2 መስመር አጭር ዜና ጋር
የአገልግሎት ዋጋ - $25.00

ደብዳቤ አስተያየትም ሆነ ጽሑፎች የምትልኩልን ትክክለኛ ስማችሁንና አድራሻችሁን እንዲሁም የስልክ ቁጥራችሁን እንድትልኩልን በትህትና እንጠይቃለን። በጽሑፉም ሆነ በደብዳቤው ስማችሁ እንዳይጠቀስ ከፈለጋችሁ ይህንኑ ከጽሑፉ ግርጌ ጥቀሱና የብዕር ስማችሁን ላኩልን። ትክክለኛ ስምና አድራሻችሁ ግን እኛ ጋ መኖር ስላለበት አደራ እንላለን።

አድራሻችን ፤- Landafta
P.O.Box 49301
Atlanta, GA 30359
ስልክ/ፋክስ፤ (404)728-9122

# በካርተር ማዕከል የተደረገው ስብሰባ

February 8 ና February 9 1994 አትላንታ በሚገኘው የካርተር ማዕከል ተቃዋሚ ኃይሎች የተገኙበት ስብሰባ መደረጉንና ሁላችንም የዚህን ስብሰባ ውጤት በጉጉት ስንጠባበቅ እንደነበር ግልፅ ነው። ስብሰባው ለጋዜጠኞች ክፍት ባይሆንም ከስብሰባው በኋላ የካርተር ሴንተርንና የተቃዋሚ ኃይሎችን ልዑካን በማነጋገር ያጠናቀርነውን የጉባኤውን ሂደት የዝግጅት ክፍላችን ያቀርባል።

ስብሰባውን የጠሩት የቀድሞው ፕሬዚዳንት ጂሚ ባርተር ሲሆኑ የተጋበዙት ድርጅቶች የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት፣ ኢድኃቅ፤ መድህን፤ የደቡብ ሕዝቦች ዳሞክራሲ ግንባር፣ የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅትና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ናቸው። በጥሪው መሰረት የመላው አማራ ሕዝቦች ድርጅት ብቻ ሲቀር ሌሎቹ ተገኝተዋል። ጂሚ ካርተር ስብሰባውን ሲጠሩ በኢትዮጲያ ያለውን ችግር በጣም ያሳሰባቸውና ለዚህም መፍትሔ ለመሻት የሚያስችሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ለመወያየት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ተሳታፊዎቹ ይኸው አጠቃላይ የመነጋገሪያ ርዕስ ብቻ ከጥሪው ጋር የደረሳቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ውይይቱ የተካሄደው በግልም በጋራም ነበር።



የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር

በመጀመሪያው ቀን የካርተር ማዕከል ኤክስፐርቶች የእያንዳንዱን ድርጅት ተወካዮች ለየብቻ አነጋገሩ። ምናልባትም ይህ ለየብቻ የማነጋገሩ ሁኔታ የተካሄደው ድርጅቶች በመካከላቸው የጎላ ልዩነት እንዳለ ለማረጋገጥ ከመፈለግ ወይም ባለው ልዩነት ሳቢያ ለማነጋገር ችግር ይፈጥራል ከሚል ፍርሃት የመነጭ ይመስላል። በዚሁ ቀን ድርጅቶች ለረዥም ሰዓታት ለየብቻ ለኤክስፐርቶች ኢትዮጲያ ያለችበትን ችግርና በበኩላችው ለዚህ ችግር ያላቸው መፍትሔ ምን እንደሆነ አቀረቡ በሚቀጥለው ቀን በመጀመሪያ ፕሬዚዳንት ካርተር ራሳችው የድርጅቶቹን ተወካዮች ለየብቻ አነጋገሩ። ከዚያም አጠቃላይ ስብስባ ተደርጐ ካርተር ግንዛቤአችውን ለማስረዳት ቻሉ። በተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የጐላ ልዩነት እንዳሌለ ለመረዳት መቻላቸውን አልደበቁም። "ሁላችሁም የምትሉት አንድ ነው፤" ነበር ያሉት። ቀደም ሲል ተቃዋሚ ድርጅቶቹ ራሳቸው መሐል ስምምነት የለም ተብሎ የተነገራቸው እንደገረማቸውም መግለጻቸው ታውቋል። ፕሬዚዳንት ካርተር ኢትዮጲያ ትልቅ ችግር ውስጥ እንዳለች ያሰጋቸው መሆኑንም ለመደበቅ አልፈለጉም። በተጨማሪ አድሎ አልባና ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ መሠረታዊ ነገሮች መሟላት እንዳለባቸው አምነዋል። የካርተር ማዕከል በኢህአዴግ ሊደረግ በታቀደው ምርጫ ላይ ምንም በታዛቢነት እንዲገኝ በኢህአዴግ ቢጋበዝም እነኚህ መሠረታዊ ጉዳዮች ካልተሟሉ ተሳትፎ ማድረግ እንደማይቻል ገልፀዋል።

ካርተር ተቃዋሚ ኃይሎችን ነፃና አድሎ አልባ ምርጫ ለማካሄድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ያላቸውን ሃሣብና መፍትሔ ብለው የሚያቂርቡትን እንዲአስረዱአቸው ጠየቁአቸው። የተቃዋሚ ኃይሎች ልዑካንም በመጀመሪያ ለ2 ዓመት ተኩል የተሞከረው የሽግግር ሂደት ውጤት አልባና ሀገሪቷን ለባሰ ችግር እየጋበዘ ያለ መሆኑን በማስረጃ ካቀረቡላቸው በኋላ የሚከተሉትን የመፍትሔ ሀሣቦች በጋራ ገልፀውላቸዋል።

1ኛ. አዲስ የሽግግር መንግሥትና ሸንጐ መቋቋም እንዳለበት። 2ኛ. ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች ገለልተኛ የሆነ የጦርና የፖሊስ ኃይል መቋቋም እንዳለበት። 3ኛ. ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች መፈታት እንዳለባቸው። 4ኛ. የፖለቲካ ድርጅቶች ያለተፅዕኖና ገደብ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው አለባቸው። 5ኛ. ነፃና ገለልተኛ የሆነ የአስመራጭ ኮሚሽን መቋቋም እንዳለበት።

6ኛ. የዜናና የሚዲያ አገልግሎት በሙሉ ነፃ ሆኖ ያለተፅዕኖ መሥራት እንዳለበት። 7ኛ. የሕገ መንግሥት ማርቀቁ ሥራ constituent assembly እስኪቋቋም መቆም እንዳለበት። 8ኛ. ተፅዕኖ የሌለበት ነፃ ምርጫ መካሄድ እንዳለበት በጋራ የገለፁ ሲሆን ይህም ካርተር ላቀረቡት ጥያቄ ሁሉ መልስ እንደሆነ ሊረዱ ችለዋል።

ሀገሪቷን ከገባችበት ቀውስ ውስጥ ለማውጣት፣ የርስ በርስ ጦርነትን ለማስወገድ ዘላቂና አስተማማኝ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ መወሰድ ያለበት የመጀመሪያ እርምጃ፣ እነኚህ ችግሮችና መፍትሔዎች ላይ ሰፊና ጥልቅ ውይይት ማድረግና በመሠረታዊ ሀሣቦች ላይ ስምምነት ላይ መድረስ መሆኑ ታምኖበት ይህንንም ሀሣብ በኢህአዴግ ለሚመራው የሽግግር መንግሥት ለአሜሪካንና ለሌሎችም መንግሥታት እንዲሁም ለተባበሩት መንግሥታት ፕሬዚዳንት ካርተር የሚያስተላልፉ መሆናቸውን ገልፀዋል። ለዚህ ስብሰባ ቅድመ ሁኔታ የተደረገው ኢህአዴግን ጨምሮ ተቃዋሚ ኃይሎች የኃይል እርምጃን አስወግደው ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንዳለባቸው ነው። በስብሰባው የተገኙ ተቃዋሚ ኃይሎችም ይህንኑ ለማድረግ መስማማታቸውንና ዝግጁነታቸውን መግለጻቸውና ታውቋል።

በዝግጅት ክፍላችን በኩል ተሳትፎ ያደረጉትን የአንዳንድ ድርጅት ተወካዮች በዚህ ስብሰባ ምን ያህል እንደረኩና ምን ውጤትም ሊገኝ እንደቻለ ለመጠየቅ ሞክረናል። በአጭሩ ለማስቀመጥ "ያለውን የተባበረ የተቃዋሚ ኃይሎችን አቋም በግልፅ በማስተዋወቅና ችግሩን ካርተር ተረድተው እንዲያምኑ በተደረገው ጥረት ቢያንስ ሰማንያ በመቶ ግባችንን መተናል።" በተጨማሪም እስካሁን ድረስ የተቃዋሚ ሃይሎችን በዚህ መልኩ አንድ ላይ ጠርቶ ያነጋገረ ስላልነበረ ይህ አጋጣሚ ኃይሎቹ ትግላቸውን ለማስተባበር የሚችሉበት መንገድ እንደከፈተላቸው ለማወቅም ተችሏል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የዓለም ክፍላት የፖለቲካ ችግሮች ላይ የአሜሪካን መንግሥት በሚወስዳቸው አቋም ላይ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት ጂሚ ካርተር በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ የነበራቸውን ኢህአዴግ ሰራሽ ግንዛቤ በጥያቄ መልክ እንዲያስቀምጡ የረዳ መሆኑን ተሳታፊዎችም የውጭ ታዛቢዎችም ይናገራሉ። በተለይም የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት በተቋቋመ ማግሥት መሆኑ ደግሞ ፩ኛ.የተቋቋመው የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት የበለጠ ተደማጭነት የሚያገኝበት ዓለምአቀፋዊ መድረክ እንደፈጥርለት ፪ኛ. በምክር ቤቱም ሆነ በዚህ ስብሰባ ላይ በመፍትሔነት የቀረቡት ሃሳቦች ፍጹም ተመሳሳይነት ስላላቸው መፍትሔዎቹ በተግባር እንዲተረጎሙ የሚያደርግ ጠንካራ የተባበረ ክንድ እንዳለ የሚያስመለክት ነው ሲሉ አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ኢህአዴግ የቀረበለትን ዕድል ተጠቅሞ ለታቀደው ስብሰባ የሚገኝ ከሆነ አንድ ውጤት ነው፤ አልሳተፍም ካለም የራሱን ማንነት የሚያጋልጥበትና እስካሁን ድረስ አለኝታዬ ነው ብሎ የያዛቸውን የአሜሪካን መንግሥትንና የሌሎችን ኃይሎች እምነት እንደሚያጣ ብዙዎች ተንብየዋል።

------------------------------

ዘግይቶ የደረሰን፤– የኢህአዴግ መሪ የስብሰባውን ጥሪ መልሱን ለካርተር ልከዋል። ገጽ 14 ) ■

## ዶ/ር በየነ በአትላንታ

## ለኢትዮጵያውያኖች መግለጫ ሰጡ

ዶክተር በየነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ የሰላምና ዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ሊቀመንበር በካርተር ማዕከል የተደረገውን የተቃዋሚ ሃይሎች ስብሰባ ባጠናቀቁ ማግሥት በአትላንታ ኢትዮጵያውያንን አነጋገሩ። አትላንታ በሚገኘው የሰላምና ዴሞክራሲ ኢትዮጵያውያን ድርጅት February 9 ቀን ክላርየን ሆቴል ውስጥ ባዘጋጀው በዚህ ጉባኤ ላይ በጣም ብዙ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል። በካርተር ማዕከል በተደረገው ስብሰባ ላይ ተካፋይ የነበሩ የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ፊታውራሪ መኩንን ዶሪ፤ አቶ አለላ መንገሻና አቶ ከድር መሐመድ በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተዋል።



ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ

ዶክተር በየነ ባደረጉት ሰፋ ያለ ንግግር፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሁን ጊዜ ያለውን ችግር፤ ለችግሮቹ መነሻ የሆኑትን በፖለቲካ አደረጃጀት በኩል የገጠሙትን መሰናክሎች፤ የፓሪሱንና የአዲስ አበባውን የሰላምና የዕርቅ ጉባኤ ከዚያም በኋላ የነኚሁ ጉባኤዎች ውጤት የሆነውን የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትን ይዞታ፤ በመጨረሻም ስለአትላንታው ጉባኤ ተሳትፎ በሰፊው አትተዋል። በየአዲስ አበባው ጉባኤ እንዳይካሄድ የተደረጉትን እንቅፋቶችና እነኚህን እንቅፋቶች በመቋቋም ጉባኤውን ለማዘጋጀት የተደረገውን ጥረትም ገልጸዋል። በተጨማሪ ምክር ቤቱ በጉባኤው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአጭር ጊዜ እቅዱን ነድፎ፣ ጽሕፈት ቤቱን አዲስ አበባ ላይ በማቋቋም ሥራውን መጀመሩን ገልጸዋል። ምክር ቤቱን የመሠረቱት በመጀመሪያ 31 ድርጅቶች ሲሆኑ ከስብሰባውም በኋላ 6 ተጨማሪ ድርጅቶች ገብተው አሁን 37 ድርጅቶች እንዳሉበት አስረድተዋል።

------------------------------

(ዶ/ር በየነ ያደረጉት ንግግር ሰፊና ታሪካዊ በመሆኑ በሚቀጥለው እትም በሙሉ እናወጣዋለን።)

እንዲህ ሆነ

# ኢትዮጵያ ከሰላምና ዕርቅ ጉባኤ ማግስት

በኢትዮጵያ ከላንዳፍታ ዜና ወኪል

የኢትዮጲያ የሰላምና የዴሞካራሲ ኃይሎች ምክር ቤት ከሰላሣ በላይ ድርጅቶችን በማቀፍ ታህሳስ 21 ቀን ሥራውን በይፋ ጀምሯል። የአጭር ጊዜ ፕሮግራሙን አፅድቋል። የምክር ቤቱ አጠቃላይ ግብ ጉባኤው የደረሰባቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን የትኩረት አቅጣጫውን በኢትዮጲያ ሠላም እንዲሰፍን፣ የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሰከነ ሁኔታ እንዲረጋገጥ፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ፅኑ የአገር አንድነት እንዲመሠረት ሲሆን በሽግግሩ ወቅት የተከሰቱ ችግሮች በውይይት የሚፈቱበትን መንገድ ያለመታከት መሻት እንደሆነ ተመልክቷል። ምክር ቤቱ ሰባት የሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ አባላትን የመረጠ ሲሆን ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ሊቀ መንበር፣ አቶ ተሾመ ገ/ማሪያም (ከብሔራዊ አንድነት ፓርቲ) ምክትል ሊቀመንበር፣ አቶ ጠሃ ሁሴን (ከኦሮሞ አቦ ነፃ አውጪ ግንባር) ጸሐፊ ሆነው ተመርጠዋል። ጉባኤውን ያዘጋጁት ኃይሎችና ተቃዋሚ ድርጅቶች ያገኙትን የፖለቲካ ድል ለማጥላላትና ለማናናቅ በመንግሥት በኩል በተለይም በሚዲያ በኩል ከፍተኛ ርብርቦሽ ሲደረግ ተስተውሏል። በየክፍለሃገራቱ ተደረጉ በተባሉት የተቃውሞ ሠልፎች "ሕዝቡ የጉባኤውን አደረጆችና ተሣታፊዎች አውግዟል" ሲሉ የመንግሥት ሚዲያዎች ሪፖርት አድርገዋል። "የዘውድ ናፋቂዎች ጉባኤ" "መብት ተጋፊ ጉባኤ". . . ወዘተ የተሰኙት አባባሎችንም ተጠቅመዋል። የመንግስት ሚዲያና መንግሥት ራሱ ከምንጊዜውም በላይ በዚህ ሁኔታ ትዝብት ላይ ወድቀዋል የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው። የዋሽንግተን ዜጐቻችን "የሠላም ጉባኤውን" አወገዙ ሲል የመንግሥት ጋዜጦች አቶ መስፍን አየነው የሚባሉትን የሠልፉን አስተባባሪ ጠቅሰው በፊት ገፅ ላይ በአቢይ ዜናነት ዘግበዋል። የሽግግር መንግስቱ የተወካዮች ምክር ቤትም በጉባኤው ላይ የተሣተፉ ሁለት ድርጅቶችን አባሯል።

በጉባኤው ማግስት ብዙ ወገኖችን ያነጋገረው ጉዳይ መንግሥት የቀረበለትን ጥሪ ውድቅ አድርጐ ጉባኤውን ፋይዳ ቢስ ካለው በኋላ በሥርቆሽ በር በፀጥታ ሠራተኞች አማካይነት በምስጢር የጉባኤውን ጠቅላላ ይዘት በቴፕ መቅዳቱ ነበር። "በሕግ ሊያስጠይቅ የሚችል ወራዳ ተግባር ተፈጽሟል" ሲል የሠላምና የዲሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤቱ ኢህአዴግን በዚህ ተግባር ይኰንናል።

በሌላ በኩል በአሜሪካዊው በሴናተር ሀሪ ጆንስተን የሚመራው የአፍሪካ ጉዳይ ንዑስ ኰሚቴ በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል ዕርቅና ሠላም ለማረድ ከካርተር ማዕከል ለዚህ ሂደት ከኢትዮጲያ የሽግግር መንግሥት የአዎንታ መልስ ማግኘቱ ተወስቷል። ከአገር ውስጥ ካሉት የፖለቲካ ድርጅቶች የደቡብ ኅብረት፣ መላው አማራ ሕዝብ ድርጅትና የሠላም የዴሞክራሲ ኃይሎች ምክር ቤት በካርተር ማዕከል ለሚካሄደው የተቃዋሚ ኃይሎች ስብሰባ መጋበዛቸው ታውቋል። (ይህ ዜና የደረሰን ከFeb 1 በፊት ነው።)

የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤቱ ጥር 17 ቀን በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ "በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት የሥልጣን ጊዜውን በማራዘም ሀገሪቱን ወደ አስተማማኝ ሠላምና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የማሸጋገር ሕጋዊነትም ሆነ ብቃት የለውም።" ብሏል። ከሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች የተወጣጣ የሽግግር መንግሥት እንደመሠረት ጉባኤው ያሣለፈውን ውሳኔ እንዲቀበልም ለኢህአዴግ በድጋሚ ጥሪውን አቅርቧል። በተያያዘ ዜና ጥር 28 ቀን 1986 ዓ. ም. ተቃዋሚ ሃይሎች የሚገኙበት ስብሰባ በካርተር ማዕከል እንደሚካሄድ ከአንድ የወሬ ምንጭ ተዘግቧል። (ጉባኤው ተካሂዷል፤ ዝርዝር ዜናው የሚቀጥሉት ገጾች ላይ ይገኛል።)

## የሽግግሩ ዘመን በጋዜጣዊ መግለጫ ላልተወሰነ ጊዜ ተራዘመ

በቻርተሩ መሠረት የተቋቋመው የተወካዮች ምክር ቤት ጥር 14 ቀን 1986 ዓ.ም. የሚያበቃውን የሥልጣን ዕድሜውን ላልተወሰነ ጊዜ አራዝሟል። የምክር ቤቱ ጸሐፊ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ሀቢሶ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ "የሽግግሩ መንግሥት ተልዕኮ ሥልጣኑን በሕዝብ ለተመረጠ መንግሥት ማስረከብ እንጂ ለተወሰኑ ምሁራን ማከፋፈል አይደለም፤" ሲሉ ገልፀው "የሽግግሩ ወቅት ሕገመንግሥት ወጥቶ ጊዜያዊ ምርጫ ተካሂዶ አዲስ መንግሥት እስኪመሠረት ድረስ ይቀጥላል፤" ብለዋል። የቻርተሩን መሠረተ ሃሣብ የካደው ይህ ጋዜጣዊ መግለጫ ምክር ቤቱ የሽግግር ወቅትን ማራዘም ስለመቻሉ ግን በዝምታ አልፈዋል። የሽግግር መንግሥቱ ቃል እንደገባው በሽግግሩ ጊዜ ውስጥ የሕዝቡን መብት ሳያስከብር፣ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ሳይሰይም ያለውጤት የተወሰነለትን ዕድሜ አጠናቋል በማለት የፖለቲካ ተቃዋሚዎች የሽግግሩን መንግሥት ሕጋዊነት ይጠይቃሉ። የሽግግሩ ወቅቱ መርዘም በደፈናው መገለፁ የተወካዮች ምክር ቤት በአንድ የተወሰነ ቡድን ፍላጐት በመመራት ላይ ያለ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ነው በማለትም ለቻርተሩ ሙሉ በሙሉ መጣስ ኢህአዴግን ይከሳሉ። እንዳንድ ውስጥ አዋቂዎች እምነትና አባባል የተወካዮች ምክር ቤቱ ከሕወሐት/ኢህአዴግና ከጥቂት ድርጅቶች በስተቀር በሙሉ የኢህአዴግ ሰራሽ ተለጣፊ ድርጅቶችና ግለሠቦች ስብስብ ነው ይሉታል። ቻርተሩን ካፀደቁት ድርጅቶች መካከል ብዙዎቹ ከምክር ቤቱ ለቀው መውጣታቸው ይታወቃል። በሌላበኩል ደግሞ በመጪው

ግንቦት ወር የሚደረገው የሕገመንግሥት ጉባኤ አባላት ምርጫ እንጂ የፓርቲዎች ምርጫ ባለመሆኑ የሽግግሩ መንግሥት ዕድሜ የሚራዘመው ከአንድ ዓመት በላይ ነው ሲሉ የፖለቲካ ጠበብቶች ይተነብያሉ።

## አምነስቲ ኢንተርናሽናል በሰላም ልዑካኑ መታሠር ቅሬታውን ገለጸ።

በሠላምና እርቅ ጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ወደ ኢትዮጲያ ሲመለሱ የታሰሩት ዜጐች ጉዳይ እጅግ በጣም ያሳሰበው መሆኑን በመጥቀስ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ለፕሬዚዳንት መለስ አስቸኳይ መልዕክት አስተላልፍል። ድርጅቱ በላከው በዚህ መልዕክት ግለሰቦቹ ከሚኖሩበት ሕጋዊ ፓስፖርትና ቪዛ ይዘው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ከአውሮፕላን ማረፊያ ተጠልፈው ወደ እስር ቤት መግባታቸው አሳዛኝ ድርጊት መሆኑን ገልጿል። የግለሰቦቹ መታሰር በስደት ላይ የቆዩ የፖለቲካ ተቀናቃኞችን ከሕዝብ ፊት ለመሰወር የታቀደ ድርጊት ነው ሲል መንግሥት የወሰደውን እርምጃ ነቅፍል። በተያያዘ ዜና የታሠሩት የመድህንና የኢድኃቅ ልዑካን ጥር13 ቀን 1986 (January 21st) ከማዕከላዊ ምርመራ ወደ ከርቸሌ መውረዳቸውን አንድ የዜና ምንጭ ዘግቧል።

## ኢህአዴግ የራሱን አባላት እያሰረ ነው።

የኢህአዴግን አሠራር የተቋወሙ ብዛት ያላቸው አባላቱ በሆለታ ገነት ጦር ሰፈር ውስጥ ለብቻቸው ተለይተው መታሠራቸው ተዘገበ። ኢህአዴግ በቅርቡ ባካሄደው ግምገማ ለዛሬው "ድሉ" ከፍተኛ አስተዋፅዖ አባሎቹ ሳይቀሩ በግምገማ ሽፋን በተካሄደው የማጥራት ዘመቻ ታስረዋል ተብሏል። ታሳሪዎቹ በሺህ የሚቆጠሩ መሆኑን ይኸው የዜና ምንጭ ገልጿል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ከዴሞክራሳዊ መስመር እያፈነገጠ የመጣውን የጅርጅቱን አሰራር በመቃወም ወደ ኤርትራና ወደሌሎች አገሮች እየኰበለሉ ያሉ አባሎች ቁጥር በርክቷል ሲል አትቷል። በሌላ በኩል ደግሞ የቀድሞው የመከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ መኰንኖች የጦርና የፀጥታ ባለሙያዎች እንዲሁም የተቃዋሚ ቡድን አባላት ባልታሰበ ጊዜና ቦታ ታድነው እየታሠሩ ናቸው ሲል አንድ ሌላ የዜና ምንጭ ዘግቧል። ተሃድሶ ገብተው ነፃ የወጡት ወታደራዊ መኰንኖች ጭምር ታፍነው መታሰራቸውን አረጋግጫለሁ የሚለው ይህ የዜና ምንጭ ድርጊቱ ኢህአዴግ ያለተቀናቃኝ ሀገሪቱን ለመግዛት የተቃዋሚዎችን የሠለጠነ የሰው ኃይል ምንጭ ለማድረቅ እየወሰደ ያለው እርምጃ ነው ሲል አክሎ ገልጿል።

## በሕገመንግሥት ዝግጅት ላይ የሚደረገው ውይይት በዝምታና በተቃውሞ ተጠናቀቀ።

በብዙ ዜጐች ዘንድ በጥርጣሬና በጥላቻ ዓይን የታየው የሕገመንግሥት መሠረተ ሃሳቦች ውይይት በመንግሥት ባለሥልጣኖች እንደተገለፀው በሕዝብ ንቁ ተሳትፎ ሳይሆን እጅግ ቀዝቃዛ በሆነ ስሜትና የዝምታ ተቃውሞ መጠናቀቁ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚደርሱት ዜናዎች አረጋግጠዋል። በሥራ ቀናት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ተዘግተው በየአካባቢው የተደረጉት ውይይቶች ከተጠበቀው እጅግ አነስተኛ በሆነ ተሳትፎ መሆኑም በይፋ ይነገራል። የኢትዮጲያ ንግድ ምክር ቤት ሕገ መንግሥት የማርቀቁን ሂደት የተቃወመው ሲሆን ሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎችም "በኢትዮጲያ ሕዝብ ላይ እየተደረገ ያለ ደባ " ሲሉ አውግዘውታል። ሰሞኑን የታተመ አንድ የግል ጋዜጣ ስምንት ሺህ ሕዝብ በሚኖርባት አንዲት ከተማ 14 ሰዎች "ንቁ ተሳትፎ አደረጉ" ሲል በፌዝ ዘግቧል። የሕገ መንግሥቱ ረቂቅ የኢትዮጲያን ዳር ድንበር የማያውቅ፣ ወሰንዋን የማይገልፃ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን የማያመለክት፣ የመንግሥትን አርማ የማያሳይ፣ የአገሪቱን ሰንደቅ አላማ የማይጠቅስ ሕዝባዊ አለኝታን የሚያሳጣ "የሊዝ ሕገመንግሥት ነው" ሲሉ ኢህአዴግን የማይደግፉ ወገኖች ይተቻሉ።

## ኤርትራ ከእስላሞች ጋር ጦርነት ጀመረች።

በምዕራብ ወሰን በሱዳን ድንበር በኩል የኤርትራ መንግሥት ከእስላም አክራሪዎች ጋር ጦርነት መግጠሟን የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ይፋ አድርገዋል። በተደረገውም ጦርነት ቅጥረኛ ተዋጊዎች ያሉዋቸው 20 ሰዎች መገደላቸውን፤ ተዋጊዎችም የቱኒዚያ፣ የአፍጋኒስታን፣ የሞሮኮና የፓኪስታን ዜጐች እንደሚገኙበት ጠቅለው መተላለፊያቸውም ሱዳን ናት ሲሉ ከሰዋል። የሱዳን መንግሥትም "መሠረተ-ቢስ" ውንጀላ ሲል የቀረበበትን ስሞታ አስተባብሏል። በሌላ በኩል የኢትዮጲያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ስዩም መስፍን "የጐረቤት ሀገርን ሠላም የሚነካ ሁሉ ይመለከተናል፤" ሲሉ በሱዳንና በኤርትራ መካከል ስለተፈጠረው ሁኔታ "Arab News" ለተባለው ጋዜጣ መግለጫ ሰጥተዋል። "ሱዳን እምነቷን ወደ ሌሎች አገሮች ከማዛመት መቆጠብ አለባት" ሲሉም አሳስበዋል። በተያያዘ ዜና ኤርትራ ውስጥ ባለው አስከፊ የኑሮ ውድነትና ዲምክራሲ አልባ አስተዳዳር የተማረሩ በርካታ ወጣቶች ቀይ ባሕርን በማቋረጠ ወደአረብ አገሮች እየጐረፉ መሆኑ ተዘግቧል።

## በርካታ የግል ጋዜጠኞች እየታሰሩ ነው።

ከጥር 14 ጀምሮ በግል የሚታተሙ የአምስት ጋዜጦች ዋና አዘጋጆችና ምክትል አዘጋጆች መታሰራቸው ታውቋል። ለመንግሥት ባለስልጣኖችና

በሥልጣን ላይ ላለው የኢሕአዴጌ አመራር ከፍተኛ ራስምታት የሆኑትን የግል ጋዜጦች ለማጥፋት መንግሥት እየወሰደ ያለው የማሰር እርምጃ በስፋት የሚቀጥል መሆኑንም ለመንግስት የዜና ምንጮች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይናገራሉ።

## የሽግግር መንግሥቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በሜርኩሪ ንግድ ይታማሉ ተባለ።

የኢትዮጲያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ታምራት ላይኔ በሜርኩሪ ንግድ እጃቸው እንዳለበት አንድ የአገር ውስጥ የወሬ ምንጭ የኢትዮጲያ አንድነት ድምፅን ጠቅሶ ዘግቧል። ዜናውን ያሰራጨው የወሬ ምንጭ (ጋዜጣ) ዋና አዘጋጅ ወዲያውኑ የታሠሩ ቢሆንም ከመንግስት የተሰጠ ማሰተባበያ ግን አልነበረም።

## ኮ/ል መንግሥቱ ራሳቸውን ለማጥፋት ሞከሩ በተባለ ማግሥት ኢትዮጵያ ልመለስ ነው አሉ።

ኰ/ል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ጥር 12 ቀን ሕይወታቸውን ሊያጠፉ ሲሉ ቅርባቸው ባሉ ቤታሳቦቻቸው ተርፈዋል በማለት አንድ የውጭ አገር የዜና ምንጭ እንደዘገበ ይነገራል። ኰሌኔሉ ሕይወታቸውን ለማጥፋት የሞከሩት በወታደራዊ ቀበቶአቸው መሆኑን የዜና ምንጩ ገልጾ አስቀድመውም ሁለት ገጽ ደብዳቤ መጻፋቸውንም ነገር ግን የመልዕክቱን ይዘት ለማግኘት እንዳልተሳካለት ጨምሮ ገልጿል። በሌላ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ዚምባቡዌ ሐራሬ ውስጥ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጡ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስና ከገለበጣቸው የኢህአዴግ መንግሥት ጋር በሁለንተናዊ መልኩ ግብግብ ለመግጠም ተዘጋጅቻለሁ አሉ። በBBC ሬዲዮ በተላለፈው በዚሁ ሬዲዮ መግለጫ ኮሎኔሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስቃይ እንዲያበቃ የዓለም ሕዝብ እገዛ ያደርግ ዘንድ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል። ቀደም ባሉት ቀናት ራሳቸውን ለማጥፋት ስለሞከሩት ጉዳይ የሰጡት አስተያየት የለም። የዚምባቡዌ መንግሥት የኮሎኔሉ ጋዜጣዊ መግለጫ ያበሳጨው መሆኑንና ኮሎኔሉ "አፋቸውን ባይዘጉ" ዚምባቡዌ የጥገኝነት መብታቸውን እንደገና ለመመርመር እንደምትገደድ መግለጫ ሰጥቷል።

## ኢትዮጵያ በኤርትራውያን መዳፍ እጅ ነች።

ኤርትራውያን በኢትዮጲያ ውስጥ በፖለቲካዊ፣ በኢኰኖሚያዊና በወታደራዊ መስክ አቢይ የሆነውን ሥራ እየተቆጣጠሩት ከመሆኑም ሌላ መሠረታዊና የሀገሪቱ የገቢ ማስገኛ ዘርፎችን በመያዝ ኢትዮጲያን በመዳፋቸው ተጽዕኖ ስር አስገብተዋል ሲል አንድ የዜና ምንጭ ዘገበ። በአለም አቀፍ የትብብር መስኰች ሳይቀር ኢትዮጲያ ከሌሎች መንግሥታት ጋር በምታደርገው ስምምነት በኢትዮጲያ ስም በመደራደር ውል የሚፈራረሙት ኤርትራዊያን ናቸው ሲል ዜናው ጨምሮ ገልጿል። እንደ ቢራ፣ አረቄ፣ ጫማ የመሳሰሉ የማያስፈልጉ ሸቀጦችን ከኤርትራ ወደ ኢትዮጲያ እንዲገቡ እየተደረገ ሀገሪቱ ለኢኰኖሚ መቆርቆዝ ተዳርጋለች ብሏል። መሠረታዊ የሆኑ ሸቀጦች ሽያጭና ክፍፍል በኤርትራዊያን እንዲያዙ ተደርጐ የኢትዮጲያ ሰብልና ሀብት ወደ ኤርትራ እየተጋዘ መሆኑ በተጨማሪ ተገልጿል። በተያያዘ ዜና መጠኑ ግዙፍ የሆነ የባሕር ዛፍና የጥንድ ግንድ ተጨፍጭፎ ለኤርትራ ነጋዴዎች በመሸጥ ላይ መሆኑንና የኤርትራ ሠሌዳ ቁጥር ባላቸው ከባድ መኪናዎች ሲጓጓዙ የዓይን ምስክሮች አይተዋል ሲል አንድ ሌላ የዜና ምንጭ ዘግቧል። ወደፊት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ይሆናል የሚባለው ሕገመንግሥት ዝግጅት ውስጥ ኤርትራዊያን ተሣትፎ እያደረጉ መሆኑ በውል ይታወቃል። የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚዳንት አቶ መለስ ዜናዊ በእናታቸው የኤርትራ ተወላጅ መሆናቸውንና እናታቸውም በውሳኔ ሕዝቡ ወቅት ለኤርትራ ነፃነት ድምጻቸውን ሰጥተዋል ሲል ጦቢያ የተሰኘ ወርሃዊ መጽሂት መመዝገቡ ይታወሳል።

## በኦጋዴን የመገንጠል ስጋት እያንዣበበ ነው።

በምሥራቅ ኢትዮጲያ በጅጅጋ፣ በጐዴ፣ በደገሀቡርና በሌሎችም ዘጠኝ ጠረፍ ከተሞች ፀጥታው እየደፈረሰና ኦጋዴንን የማስገንጠል ዘመቻ በአክራሪ እስላሞችና በሶማሊያ አንጃዎች እየተካሄደ መሆኑን ከሥፍራው የሚደርሱት ዜናዎች ይጠቁማሉ። "ኦጋዴን የሶማሊያ ምድር እንጂ የኢትዮጲያ አካል አይደለችም፤" ሲል በአካባቢው የመስፋፋትና ጦርነት የጀመረው የእስልምና አክራሪ ድርጅት (አልኢትሃድ) ራሱን እንደ ኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር በመቁጠር ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። የቀድሞው የሶማሊያ መንግስት በክልሉ የአስተዳደር ዘርፍና በከፍተኛ የኢትዮጲያ መንግሥት የሥልጣን እርከን ላይ የደረሱ ስለሆነ ለውጥረቱ መባባስ አስተዋፅኦ እንዳለው ታዛቢዎች ገምተዋል። በኦጋዴን የሚንቀሳቀሰውን የአክራሪ እስላሞች (አልኢትሃድ) እርምጃ መንግሥት ሊቋቋመው እንዳልቻለ የዓይን ምሥክሮች በይፋ ይናገራሉ። አንድ የኦጋዴን የፖለቲካ ድርጅት ሰሞኑን ለBBC በሰጠው መግለጫ "እኛ የሚበጀን ተገንጥሎ የራሳችንን መንግሥት ማቋቋም ነው" ሲል ገልጾ በዚህም ተግባራዊነት በቅርቡ ውሳኔ ሕዝብ ይካሄዳል ብሏል። ይህ በዚህ እንዳለ በጅጅጋ ከተማ ቆሞ የነበረው የቆራሂው ጀግና የደጃዝማች አፈወርቅ ወ/ሰማያት ሀውልት መፍረሱ በቦታው የነበሩ የዓይን ምስክሮች ገልፀዋል። ደጃዝማች አፈወርቅ በ1928 ዓ.ም. ጣሊያን ኢትዮጲያን ስትወር የኦጋዴንን በር ዘግተው ሲዋጉ የወደቁ ስመጥሩ አርበኛ ነበሩ።

## የጎሣ ግጭትና የጦርነት ስጋት

የሽግግር መንግሥቱ ኤታማጆር ሹም መላው የኢትዮጲያ ጠረፍ በሠራዊታቸው ቁጥጥር ስለመሆኑ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡ ቢሆንም በተለያዩ የኢትዮጲያ ክልሎች የጐሣ ግጭቶች መኖራቸውንና የኢሕአዴግ ወታደሮች ከታጠቁ ኃይሎች ጋር መዋጋታቸው የተለያዩ የዜና ምንጮች አስታውቀዋል። በጐንደር፣ በወሎ፣ በሸዋና በባሌ በኢሕአዴግ ሠራዊት ላይ ጥቃቶች መሰንዘራቸውን አንድ የአገር ውስጥ ጋዜጣ ጠቅሶ ከአዲስ አበባ ወደ ደብረብርሃን በሚወስደው መንገድ ላይ እንኳን የኢሕአዴግ ጦር ያለአጀቢ (ኰንቮይ) ለመንቀሳቀስ አቅቶታል ሲል ወሬውን አሰራጭቷል። በድሬዳዋ ከተማ አካባቢ በኢሕአዴግ ታጣቂዎችና በኢሣጉርጉራ ብሄረሰቦች መካከል ግጭት መፈጠሩን እንዲሁም በመተከል በፓዊ በደረሰው የጐሣ ግጭት በርካታ ሰዎች መሞታቸውን የተለያዩ የዜና ምንጮች ዘግበዋል። በእንግሊዝ አገር ውስጥ በአረብኛ ቋንቋ የሚታተም ወርሃዊ መጽሄትም "በብሄረሰቦች የእርስ በእርስ ጥላቻና ወላፈን ተወጥራ ኢትዮጲያ ለምርጫ እየተዘጋጀች ነው፤" ሲል ጽፍል። በሼክ ጀራ አባገዳ የሚመራ የኦሮሚያ ነፃነት እስላማዊ ግንባር (ኦነእግ) ከሃምሣ በላይ ተከታታይ ጥቃቶችን መሰንዘሩንና ወታደራዊ ድሎችንም አግኝቻለሁ ሲል የጦር ሜዳ ውሎ ዜናውን አሰራጭቷል። አክሎም ሁለት ሄሊኩፕተሮችን ከጥቅም ውጭ አደረኩ ብሏል።

## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት የአፍሪካ ጉዳዮች ረዳት ሚኒስትር ኢትዮጵያን ጎበኙ። ተቃዋሚ ኃይሎችን አነጋገሩ።

በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት የአፍሪካ ጉዳይ ረዳት ሚኒስትር የሆኑት ሚስተር ጆርጅ ሙስ በኢትዮጲያ ጉብኝት አድርገው የሽግግር መንግሥቱን ከፍተኛ ባለሥልጣናትንና የተቃዋሚ ኃይሎችን መሪዎች አነጋግረዋል። ካነጋገሯቸውም የተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የሰብአዊ መብቶች ሊቀመንበር ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም የመኢህድ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስና የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶ/ር በየነ ጴጥሮስ ይገኙበታል። ሚስተር ጆርጅ ሙስ ከመንግሥት ባለሥልጣናት ቀዝቃዛ አቀባበል የተደረገላቸው መሆኑን የዜና ምንጮች የዘገቡ ሲሆን የጉብኝታቸውም ዜና በመንግሥት ጋዜጦች ላይ በመደበኛ ዜናነት አልቀረበም። እንደአንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች በአሁኑ የሚስተር ጆርጅ ሙስ ጉብኝት ተቃዋሚ ኃይሎች በሚስተር ሄርማን ኰሄን አድልዎ ተፈፀመበት ስለሚባለው የኢትዮጲያ የፖለቲካ ሥልጣን በኢሕአዴግ በሞኖፖል መያዝ ለማስረዳት መልካም አጋጣሚ አግኝተዋል ይላሉ።

## ኦነግ የአዲስ አበባውን የሰላምና የዕርቅ ጉባኤ አወገዘ

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (OLF) የግዮኑን የዕርቅ ጉባኤ ተሳታፊዎች የአፄ ኃይለሥላሴና የደርግ መንግሥታት ቅሪቶች ከመሆናቸው በላይ የቀሩት ደግሞ የኢህአዴግ ተባባሪዎች ናቸው ሲል ጉባኤውን አውግዟል። አንዳንድ ታዛቢዎች እንደሚናገሩት ይህ የኦነግ መግለጫ የራስን ድርጅት ብቻ ትክክለኛ አድርጐ የመውሰድና በተለይም ስንት አናሳ ብሔረሰቦች የተሳተፉበትን ጉባኤ መናቁ ኦነግ ቆሜአለሁ ከሚልበት ዓላማ ጋር እንደሚቃረን እንዴት እንዳልታየው ይናገራሉ። ድርጅቱ ባወጣው መግለጫ ላይ ኦነግ ለኦሮሞ ሕዝብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መስፈን ትግሉን ይቀጥላል ብሏል።

## በአሜሪካዊው ዲፕሎማት ላይ የግድያ ሙከራ ተደረገ።

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ባልደረባ በሆኑ አንድ ዲፕሎማት ላይ ጥር 18/86 (Jan 26/1994) kqኑ 11:30 ላይ አዲስ አበባ የግድያ ሙከራ ተደርጐባቸዋል። ዲፕሎማቱ የUSAID ንብረት በሆነ መኪና ከድርጅቱ ወጥተው ወደ መስቀል አደባባይ በማቅናት ላይ እንዳሉ ተሽከርካሪ በያዙ ግለሰቦች ሶስት ጥይት የተተኮሰባቸው መሆኑን በድንገት ሊያመልጡ መቻላቸውንም ፖሊስ ይፋ አድርጓል። ሰሞኑን በወጣ አንድ ሌላ ዜና በአሜሪካዊው ዲፕሎማት ላይ ተኩስ የከፈትኩት እኔ ነኝ ሲል "የኢትዮጵያ አንድነት . . .ጓድ" የተሰኘ ምስጢራዊ ቡድን ባሰራጨው በራሪ ወረቀት ራሱን ይፋ አድርጓል ይላል። እንደተበተነው ወረቀት አባባል ቡድኑ ከጥር 15/86 ጀምሮ አገር የማዳን የነፃነት ትግልን በማፋፋም ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሶ አሁንም ተመሳሳይ እርምጃ እንደሚወስድ ዝቷል። አያይዞም ለማንኛውም ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የአሜሪካ ዜጐች በሙሉ የሰደዷትን፣ የአንቋሸሿትን ለጥፋት የደከሙላትን አገራችንን እስከ የካቲት ድረስ ለቀው እንዲወጡ አስጠንቅቋል። አንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች ጥርጣሬቸውን ሲገልጹ ሰሞኑን የአሜሪካ መንግሥት ተቃዋሚ ሃይሎችን አትላንታ ድረስ በመጋበዝ ማነጋገሩ ሃይሎቹን ማወቁ ነው በሚል ግምት በተቃዋሚ ሃይሎችና በአሜሪካ መሐል ግጭት ለመፍጠር ኢህአዴግ ራሱ ያደረገው ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። ይህን ጥርጣሬ የሚያጠነክረው 1ኛ. ተቃዋሚ ሃይሎች ለስብሰባ አሜሪካ በመጡበት ወቅት መሆኑ 2ኛ. ወረቀት በተነ የተባለው ቡድን ስም ከዚህ በፊት ተሰምቶ የማይታወቅ መሆኑና 3ኛ. ተኩሱ ተሰማ በተባለበት አካባቢ የሚነፍሰው ወሬ ተኩስ የተደረገው የመንግሥት ታርጋ ካለው መኪና ነው የሚል ወሬ መንፈሱ ነው ሲል አብሮ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

## ስዊድን 400 ኤርትራውያንን ልታባርር ነው ተባለ።

የፖለቲካ ጥገኝነት መብት አይገባቸውም የተባሉ 400 ኤርትራውያን ስዊድንን ለቀው እንዲወጡ ተወሰነባቸው። ለኤርትራውያኑ ስዊድንን ለቆ መውጣት ችግር ሆኖ የተገኘው ፓስፖርትም ሆነ ሌላ የጉዞ ሰነድ አለመያዛቸው ቢሆንም እነዚህ ዜጐች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የጉዞ ሰነድ ታድሎቸው ስዊድንን ለቀው ካልወጡሰብዓዊና ሌላም ዓይነት ዕርዳታ ሁሉ እንደማትሰጥ የስዊድን መንግሥት አስታውቋል።

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ በቋፍ ላይ ነው።

ከFeb 15/94 ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል ተብሎ በተቀረጸው አዲስ መዋቅራዊ ለውጥ ምክንያት አየር መንገዱ በቋፍ ላይ መሆኑን ከአየር መንገዱና ከሠራተኛው ማህበር የተገኙ የውስጥ ምንጮች ይጠቁማሉ። ድርጅቱን አደጋ ላይ ይጥላል ተብሎ በተፈራው በዚህ መዋቅራዊ ለውጥ የአየር መንገዱ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች ራሳቸውን የቻሉ ሆነው እንደሚደራጁ የተገለፀ ሲሆን የቴክኒክ አገልግሎትና የበረራ ዘርፎች ራሳቸውን የቻሉ ሆነው ለየብቻ እንደሚደራጁና ነገር ግን በቅንጅት እንደሚሰሩ ተመልክቷል። አየር መንገዱን ለኢንቬስተሮች ክፍት ያደርጋል በተባለለት በዚህ መዋቅራዊ ለውጥ ድርጅቱን ከኤርትራና ከጂቡቲ ጋራ በሽርክና መልክ ለመያዝ ሳይሆን አይቀርም ሲሉ የውስጥ አዋቂዎች ይተቻሉ። (ዝርዝር ሪፖርቱን ወደፊት ተከታትለን እናቀርባለን።)

---

# በቅርቡ የደረሰን

Feb. 17ና Feb 18 በተከታታይ ሬውተር ያስተላለፋቸው ሁለት ዐበይት ዜናዎች አራት ታስረው የነበሩት የሰላም ልዑካን መፈታትንና፣ በሚቀጥለው ሰኔ ኢህአዴግ ሕገ መንግሥት የሚያጸድቅ የሕዝቦች ሸንጐ (constituent assembly) ለማስመረጥ የወሰነ መሆኑን ይገልጻሉ። Feb 17 የወጣው ዜና ተረቀቀ የተባለውን ሕገመንግሥት የሚያጸድቁ 547 አባላት የሚኖሩት ሸንጐ ከሕዝቡ በሰኔ ወር ለማስመረጥ የተዘጋጀ መሆኑን በመንግሥት ዜና የተሰራጨውን ይጠቅሳል። ዜናው አቶ ሉልሰገድ እርቅይሁን የተባሉት የአስመራጭ ኮሚሽን ባለሥልጣን "በአገሪቷ በ32,000 የምርጫ ጣቢያዎች የሚከናወነው ይኸው ምርጫ 547 የምርጫ ክልሎች ሲኖሩት ከየአንዳንዱ ክልል 12 እጩዎች ያህል ሊወዳደሩ የሚችሉ መሆኑን" ገልጸዋል ይላል። የመድብለ ፓርቲ ምርጫ ግን ብዙ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከመንግሥት ምክር ቤት ለቀው በመውጣታቸው የሚዘገይ መሆኑን ይኸው ዜና ጨምሮ ጠቅሷል። ዜናው በተጨማሪ የመንግሥት ምክር ቤት በኢህዴግ ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ስር መሆኑንና ተቃዋሚ ኃይሎች ሕገመንግሥቱን ለማርቀቅ የቋቋመውን ኮሚሽን ሕዝቡን የማይወክልና ኢህአዴግ ሰራሽ በመሆኑ ያልተቀበሉት መሆኑን ገልጿል። Feb 18 ደግሞ ሬዌተር ባወጣው ተጨማሪ ዜና ደግሞ ኢህአዴግ አስሯቸው የነበሩትን የኢድኃቅ አባላትን ወ/ሪት ገነት ግርማን፣ አቶ መስፍን ተፈራን፣ አቶ ገነነው አሰፋንና የመድህኑን አቶ ሥዩም ዘነበን የፈታ መሆኑን ገልጿል። አቃቤ ሕጉ በመንግሥት ትዕዛዝ ክሱን እንዲሰርዝ መደረጉ ተጠቅሷል። አቶ አበራ የማነአብን ግን ከደርግ ጋር አብረው የሰሩ በሚል ምክንያት አለመለቀ ቃቸውን ዜናው ጨምሮ ገልጿል። ባለፈው ወር ሁለቱን የኦ ኤል ኤፍ አባላትን ለቅዋል። በዚሁ ዜና በኢህአዴግ ቁጥር ስር ያለው የሽግግር መንግሥት በተቃዋሚ ኃይሎቾ የቀረበበትን የተቃውሞ ክስ ሁሉ መሠረተቢስ ነው ማለቱ ተጠቅሷል።

## የኢህአዴግ መሪ በካርተር ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ መስጠታቸው ታወቀ።

አትላንታ ተደርጐ በነበረው ስብሰባ መሠረት ፕሬዚዳንት ካርተር የኢህአዴጉን መሪ በማነጋገር ያገኙትን መልስ ለተቃዋሚ ኃይሎች ማሳወቃቸው ተረጋገጠ። "አሁን በመካሄድ ላይ ባለው የፖለቲካ ሁኔታ ላይም ሆነ በመንግሥት መዋቅር ላይ ምንም መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ማድረግ አይቻልም። ቢሆንም ከማንኛውም ተቃዋሚ ኃይል ጋር በግልም ሆነ በቡድን መነጋገር እችላለሁ። ጦርነት ካወጁብንም ጋር ቢሆን።" የሚል መልስየኢህአዴጉ መሪ መመለሳቸውን ካርተር ለተቃዋሚ ኃይሎች ባስተላለፉት መልዕክት ገልጸዋል። "ተቃዋሚ ኃይሎች በደብዳቤ 'የምንመጣው በሰላም ነው' እስካሉ ድረስ ኢትዮጵያ ገብተው ከኔ ጋር ተነጋግረው መመለስ ይችላሉ።" ይላል መልሳቸው። "ጦሩን በተመለከተ ደርግ ከሥልጣን ሲወርድ ምንም አማራጭ ስላልነበረን ነው፣፣ አሁንም ቢሆን በቅርቡ ካለው የኢህአዴግ ጦር 20,000 ያህል የሆኑትን የትግራይ ወጣት ጦረኞች ከኢህአዴግ ጦር ወደ ሲቪልነት ለመመለስ (demobilize ለማድረግ) ተስፋ አደርጋለሁ። ፖሊስን በተመለከተ ሙሉ በሙሉ ትግሬዎች የሆኑት ያሉት ትግራይ ውስጥ ብቻ ነው፣ በሌሎች ቦታዎች ግን በአካባቢው የብሔር ባህሪ ላይ የተመሠረተ ነው። ምርጫንም በተመለከተ ማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ገብቶ ሊሳተፍ ይችላል። ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችም ይኖራሉ። መንግሥትም ማንኛውንም ተቃዋሚ ኃይል ግልጽ በሆነ አዕምሮ ልዩነትን ለማስታረቅ አማራጭ መንገዶችን ይዞ ከመጣ ልንወያይ እንችላለን፤ ነገር ግን አሁን ባለው የመንግሥት አወቃቀርና የፖለቲካ ሥርዓት ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ ለማድረግ አይቻልም፤" የሚል መልስ ማግኘታቸውን ካርተር ለተቃዋሚ ኃይሎች አሳውቀዋል። ካርተር ከተቃዋሚ ኃይሎች መልስ እንደሚጠባበቁና መልሳቸውን እንዳገኙ እንደሚያስተላልፉ ገልጸዋል።

# ዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት



የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ሊቀመንበር ናቸው። የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ዲግሪያቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የፒ ኤች ዲ ዲግሪአቸውን በፖለቲካ ሣይንስ ትምህርት በ1987 ያገኙት ከዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኢሊኖይ ነው። ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ለአንድ ዓመት በዚያው በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ኢሊኖይ በመምህርነት አገለገሉ። በ1988 ዓ.ም. ወደ አገራቸው በመመለስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማስተማር ጀመሩ። በ1993 የሽግግር መንግሥቱ ከመደበኛ ሥራቸው ካባረራቸው 42 ምሁራን መሐከል አንዱ ናቸው። ዶክተር ታዬ ወልደሰማያት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት ናዝሬት በሚገኘው ገላውዲዮስ ትምህርት ቤት በመሆኑ የናዝሬት ልጅ ናቸው። ገላውዲዮስ ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት የተማሪዎች ካውንስል ፕሬዚዳንት ሆነው አገልግለዋል።

ዶክተር ታዬ በ1993 ዓ.ም. ማገባደጃው ላይ በአዲስ አበባ በተካሄደው የ"ሰላምና ዕርቅ ጉባኤ" ላይ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርን በመወከል ተሳተፈዋል። በዚሁ ጉባኤ ላይ በዋና ፀሐፊነት ተመርጠው ጉባኤው በተሳካ ሁኔታ እንዲፈጸም አመራር ከሰጡት ግለሰቦች አንዱ ናቸው።

ዶክተር ታዬ በጉባኤው ማግሥት ወደ አሜሪካ በመምጣት በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በመገኘት ለብዙ ኢትዮጵያውያን ስለ ሰላሙ ጉባኤ አካሄድና ውሳኔዎች፤ ስለ ኢትዮጵያ መምህራን ማህበር መግለጫ ሰጥተዋል። በዚሁ ወቅት አትላንታ በመጡበት ጊዜ የዝግጅት ክፍላችን ቃለ መጠይቅ አቅርቦላቸው ነበር። ለቃለ መጠይቁ የሰጡትን መልስ ለኢትዮጵያውያን ካደረጉት ንግግር ጋር በማቀነባበር አቅርበናል።

# ከዶክተር ታዬ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ላንዳፍታ– በጉባኤው ላይ የተገኙት ማንን ወክለው ነው? ጉባኤውን ባጠቃላይ እንዴት አዩት?

ዶ/ር ታዬ– የምወክለው የኢትዮጲያ መምህራን ማህበርን ነው። ማህበራችን የሙያ ማህበር እንደመሆኑ መጠን ለዲሞክራሲ ሂደት ጥሩ መሣሪያ ይሆናል ብለን ስላመንን ነው የተሳተፍነው። ጉባኤው በአገር ውስጥ ያሉትን የዴሞክራቲክ ኃይሎች ማጠናከሪያና ሥልጣንን በጉልበት ለሚወስደው አካል በጉልበት ኃያልነት መወሰን እንደማይቻል ሊያሳይ ይችላል የሚል Thesis አለኝ። የምናገረውን በተለያየ መልኩ ልታዩት ትችላላችሁ፤ አንዳንድ ሰዎች በድርጅት መሣሪያነት፣ ሌሎች ሰዎች በኢትዮጲያዊነት ስሜት ያዩታል፣ ሌሎች ደግሞ ሥልጣን ላይ ባለው ኃይል አጋርነት ይመለከቱታል። እኔ ግን የማየው በኢትዮጲያ ሕዝብ አጋርነት፣ ሕዝቡ ማን እንደሚያስተዳድረው ራሱ መወሰን መቻል አለበት ከሚለው አንፃር ነው።

ላንዳፍታ– ጉባኤውን የኢትዮጲያ ሕዝብ እንዴት ተቀበለው? የሽግግር መንግሥቱስ? ከኢትዮጲያ ውጪስ ያሉ ወገኖች?

ዶ/ር ታዬ– የሰላሙ ስብሰባ ያገኘው ሕዝባዊ ድጋፍ ከጠበቅነው በላይ ነው ሆኖ ያገኘነው። የኢትዮጲያ ሕዝብ በደስታ ነው የተቀበለው። ከጉባኤው በፊት የነበረው 300 ሺህ ሕዝብ በላይ የተሳተፈበት ሕዝባዊ የድጋፍ ስብሰባ እራሱ ምስክር ነው። ሕዝቡን ለዚህ ድጋፍ ማሰባሰብ የተሰጠው ጊዜ ትንሽ ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ ማስታወቂያ ነው ያንን ያህል ሕዝብ የወጣውና የደገፈው። በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ባሉ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዎና ጋዜጣ ስለዚህ ድጋፍ የተባለው ደግሞ ሌላ ነበር። "አንዳንድ የተወናበዱ ሰዎች መሬት ይመለሳል ብለው ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው የሰላምና የዲሞክራሲ ጉባኤ ድጋፍ ሰልፍ ነው ሲሏቸው ተደናግጠው ተመለሱ፤" ብሎ ነበር የኢትዮጲያ ቴሌቪዥን ያቀረበው። ይህን ያህል አንድ መንግሥት መዋሸት ከቻለ እንግዲህ ምን ቀረን። ውሸት በአሁኑ ጊዜ ትልቅ የፖለቲካ ባህርይ እየሆነ መጥቷል። ካልዋሸህ ፖለቲከኛ መሆን አትችልም ማለት ይሆን? ለምንድነው እንዲህ የምትዋሹት ስትላቸው "የትግል ስልት ነው" ይላሉ።

(ወደ ገጽ 18 ይዞራል)

# የቡድን ጥላቻ (Prejudice)

ከአንበርብር

በሰዎች ዘንድ በተለያዩ ምክንያቶች ጥላቻዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ለጥላቻ ሁል ጊዜ ምክንያት አለው። የምክንያቱ መጠንከር ወይም ማነስ ጠይው በተጠይው ላይ የሚወስደውን እርምጃ ዓይነት ይወስናል። ቀለል ያለ ጥላቻ ብዙውን ጊዜ ከመዘጋጋት አያልፍም። ከረር ካለ ግን ችግር አለው። መጠፋፋት ደረጃ ላይም ሊይደርስ ይችላል። ይህ ጥላቻ በሰዎች ቡድኖች መሐል ከሆነ ደግሞ መጥፎ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። የሕዝብ ቡድኖች የምንላቸው እንደ ዘርና ጐሣ የመሳሰሉት ሲሆኑ በነዚህ መሐል የሚከሰቱትን ቅራኔዎች ከረው መጠፋፋት ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ መንግሥት ሕዝቦቹን ለማቀራረብ ትልቅ ሚና ይጫወታል። የአንድም መንግሥት ጥሩነት መለኪያው አንዱ የሕዝቦቹ ተፈቃቅረው ተከባብረውና ተረዳድተው መኖር መቻላቸው ነው። ይህ የመፈቃቀር ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ሁኔታዎችን ሁሉ ያመቻቻል። ይህን ለመግቢያ ያህል ካልን እስቲ ጥላቻን ጠለቅ ብለን ለመመርመር እንሞክር።

በመጀመሪያ ለዚህ ጽሑፍ የምንጠቀምባቸውን አንዳንድ የእንግሊዘኛ ቃላት የቀጥታ እንኳ ባይሆን ተመሳሳይ በሆኑ ትርጉሞች እንፍታቸው።

1ኛ. Hate-ጥላቻ (መጥላት)

አንድን ግለሰብ በአንድ ወይም በብዙ መጥፎ ተግባሩ፣ ወይም ባህርይው ሊጠላ ይችላል። ድርጊቱ ወይም ባህርይው መጥፎ የሚሰኘው ግለሰቡ በሚኖርበት ማህበረሰብ ተቀባይነት የሌለው ወይም የተኮነነ ከሆነ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ሁለት ግለሰቦች ባለመግባባት ወይም የተለያየ አስተሳሰብና አመለካከት ስላላቸው ሊጠላሉ ይችላሉ። አንድ ግለሰብ ሌላውን ግለሰብ ሲያጠቃ ሲበድል፣ ግፍ ሲሰራበት ተጠቂው ግለሰብ አጥቂውን ግለሰብ ሊጠላ ይችላል። ይህ ግለሰቦችን በግለሰብ ድርጊታቸውና ባህርያቸው መጥላት ስሜት በሰው ልጅ ባህርይ ውስጥ ሁልጊዜም ያለ ነው።

2ኛ. Prejudice-(የቡድን ጥላቻ)

ይህ የዘር፣ ሃይማኖት፣ ቀለም፣ ወዘተ ጥላቻ ሊሆን ይችላል። አንድ ግለሰብ ወይም ጥቂት ግለሰቦች በግልም ሆነ በጋራ የፈፀሙትን መጥፎ ተግባር ወይም ያሳዩትን መጥፎ ባህርይ ግለሰቡ ወይም ግለሰቦቹ ያሉበት ዘር፣ ጐሣ ወይም ሃይማኖት ቡድን አጠቃላይ ባህርይ አድርጐ የመውሰድ ዝንባሌ ነው።

"Prejudice is a term applied to catagorical generalizations based on in adquate data and without sufficent regard for individiual differences."

በግለሰቦች መሐል ሊኖር የሚችለውን ልዩነት ባለማጤን ወይም ሁን ብሎ ለመቀበል ፍቃደኛ ባለመሆን ድርጊቱን ወይም ባህርይውን ግለሰቡ የመጣበትን ቡድን አጠቃላይ ባህርይ አድርጐ የመውሰድ አዝማሚያ ትልቅ ስህተት ውስጥ ይከታል።

3. Stereotype-(ግትር ያለ በቡድን ላይ የሚታዩ ጥላቻ) መጥፎ ድርጊቱ፣ ወይም ባህርይው የተፈፀመው በአንድ ግለሰብ ወይም በጥቂት ግለሰቦች እንጂ ድርጊቱ ግለሰቡ የመጣበትን ቡድን (ዘር ወይም ጐሣ) የሚወክል አለመሆኑ በቂ መረጃ እየታየ ይህን እውነታ ለመቀበል አለመፈለግ፣ ግትር የቡድን ጥላቻ (stereotype) ይፈጥራል።

ብዙ ሰዎች የሰው ልጅን የተለያየ ባህርይ መርምረው ውሳኔ በመስጠት ፋንታ በግል ወይም በጥቂት ግለሰቦች ላይ ለተወሰነ ጊዜ የሚያዩትን ሁኔታ ዘላለም የሚፈጸም አጠቃላይ ባህርይ አድርገው ስለሚወስዱ ትልቅ ስህተት ውስጥ ይገባሉ። አንድ ምሳሌ እንውሰድ፤ አንድ ሰው አንዳንድ ፈረንሳዮች መጥፎ ነገር ሲያደርጉ አይቶ በአጠቃላይ ፈረንሳዮች ላይ የከፋ ጥላቻ መስርቷል እንበል። ይህ ጥላቻው ስሜታዊ የሆነ ዝንባሌ በአዕምሮው እንዲፈጥር ያደርጋል። ምንም ይሁን ምን አንድ ፈረንሳዊ የሆነ ሰው ጥሩ ነገር ሲያደርግ እያየ ያንን ጥሩ ድርጊት የሚተረጉመው ወይም የሚመለከተው ቀደም ሲል በውስጣዊ አዕምሮ ባረገዘው የጥላቻ ስሜት መነጽር ከሆነ እውነትን ይረግጣታል። በዓይኑ የሚያየውን ነባራዊ (objective) ነገር ትቶ በአዕምሮው ባረገዘው ስሜት (subjective) ከሆነ stereotype ሆኗል ማለት ነው። ይህ ሰው ያየውን ጥሩ ተግባር በአጋጣሚ እንደተፈጸመ አድርጎ በመውሰድ ራሱን ለማታለል ሲሞክር ይታያል።

4. Discrimination-(ለይቶ መጥቀም ወይም መጉዳት)

የተጠላውን ቡድን (ዘር፣ ጐሣ፣ ሃይማኖት) ከራስ ቡድን ለይቶ በመውሰድ፣ የራስን ቡድን ብቻ መጥቀም የሌላውን ቡድን ማግለል። ይህ የቡድን ጥላቻ (prejudiceን) በተግባር መተርጐሚያ፤ የተጠላውን ቡድን ማጥቂያ ዘዴ ነው።

"Social discrimination is unequal treatment of equals...it caries with it the idea of unfairness." Encyclopaedia of Social Sciences.

5. Segregation-(መነጠል)- (ነጥሎ ማስቀመጥ የተጠላውን ቡድን) (ዘር ወይም ጐሣ) ለይቶ (discriminate አድርጎ) ከሌላው በመነጠል ተጠይውን ቡድን ሊጐዳ በሚችልና የራሱን ቡድን ሊጠቅም ጂኦግራፊያዊ ወሰን ከልሎ ማስቀመጥ)

ከላይ መሠረታዊ የሆኑትን ቃላት ለመተርጐም ሞክረናል። ሰፋ አድርገን የምንመለከተው የቡድን ጥላቻንና (prejudiceን) ና በዚሁ ጥላቻ ሳቢያ

የሚፈጠሩትን ለይቶ የመጥቀምንና (Discrimination)፤ ነጥሎ የማስቀመጥን (Segregation)ን ይሆናል።

የጐሣ ጥላቻ(ethnic prejudice) ማለት እንግዲህ በተወሰኑ ጐሣዎች ወይም ጐሣ ላይ የሚደረግ ጥላቻ የሚንፀባረቅበትን ሁለት መንገዶች እንይ።

1ኛ. የተጠላውን ዘር ወይም ጐሣ አባላት የሆኑትን ግለሰቦች መጉዳት ሲሆን

2ኛው. የራስን ዘር ወይም ጐሣ አባላት ብቻ መጥቀምና ሌላውን ቸል ማለት ናቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የተጠላውን ዘር ወይም ጐሣ ቀጥታ በሆነ መንገድ ማጥቃት ሳይቻል ሲቀር የራስን ጐሣ ብቻ መጥቀም ይያዛል። እንግዲህ የራስን ዘር ብቻ በሁሉ ሁኔታ መጥቀም ለሌላው ዘር ዕድል መንፈግ ስለሚሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላውን ዘር ይጐዳል ማለት ነው።

በአዕምሮ ውስጥ የተቀረፀው ውስጣዊ የዘር ጥላቻ (ethnic prejudice)በተግባር ሲተረጐም ጠይው በተጠይው ላይ የሚከተሉትን ይፈፅማል።

1. ተጠይው የሆነውን ዘር አፀያፊ የሆኑትን ቅፅሎች መስጠት
2. ተጠይውን ዘር ከአካባቢ ማራቅ ወይም ለማራቅ መሞከር።
3. የተለያዩ ጐሣዎችን ለያይቶ የሚያይ ሕግና ልምድ መቅረፅ።
4. በትምህርት ዕድል፣ በሥራ፣ በመዝናኛ ክልሎች፣በፖለቲካ ተሳትፎ፣ በሀብት ክፍፍል ለራስ ዘር አድልዎ ማድረግና ሌላውን ቸል ማለት።
5. የተጠይውን ዘር አባላትን በጉልበት፣ በኃይል፣ ማጥቃት።
6. ተጠይ የሆነው ዘር ፈፅሞ ለማጥፋት መሞከር።

የቡድን ጥላቻ ተግባራዊ ገፅታውን ካየን የስህተቱን ምንጭ ለመመርመር እንሞክራለን።

1. የሰው ልጅ አዕምሮ የተለያዩ አነስተኛ ሁኔታዎችን በመመልከትና በመገምገም የአጠቃላይ የጋራ ባህሪ የመፍጠር ዝንባሌ እንዳለው የስነ ልቦና ሊቃውንት ይናገራሉ። በርግጥ በተናጠል የተፈፀሙ የተለያዩ ድርጊቶች ተመሳሳይ የሆኑ አንዳንድ ሁኔታዎችን ቢያሳዩ ከእነኚያ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ተነስተን የጋራ የሆነ ባህሪ ልንመሠርት እንችላለን። ይህን ግንዛቤና ድምደማ በሰው ልጅ ባህርይ ላይ ስናውለው ግን በጣም መጠንቀቅ አለብን። የአንድ ቡድን ወይም ዘር አባላት ከሆኑት ግለሰቦች ጥቂቶቹ በግለሰብ ደረጃ የፈፀሙትን ተግባራት ሆነ የሚያሳዩትን ባህርይ የቡድኑ የጋራ ስሜት አድርገን ከወሰድን ትልቅ ስህተት ውስጥ እንገባለን። ይህ ነው እንግዲህ Prejudiced የሚያሰኘን።

አንድን ባህርይ ወይም ተግባር የቡድን ጋራ ስሜት አድርጐ ለመውሰድ በአጠቃላይ የቡድኑ አባላት የሚፈፅሙትን፣ ቡድኑን ከሌላው ቡድን የሚለየው ፍፁም መለዮው ሆኖ መታየት አለበት።

2. ሌላው ደግሞ ድርጊቱ የተፈፀመበትን ሆነ ባህርይው የታየበትን ጊዜ ካለማጤን የማመንጭ ስህተት ነው። ይህም ማለት ቡድኑን ታሪካዊ ደመኛ አድርጎ የመውሰድ ዝንባሌ ነው። አንድ ቡድን በአንድ ታሪክ ሂደት (በአንድ ባለፈ የተወሰነ ጊዜ) የተለየ ባህርይ ነበረው እንበል። ይህ ባህርይው ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ፣ ዕድገት እየመጣ ሲሄድ በአንድ ቦታ ረግቶ የሚቀመጥበት ሁኔታ ስለሌለ ቡድኑ ባህርይውን ከጊዜ ሁኔታ ጋር፣ ከታሪክ መለዋወጥ እያገናዘበ ይቀይራል። ይህን ሁኔታ ካለማጤን ወይም ሁን ብሎ ላለመቀበል ከመፈለግ ቡድኑን በጥንት ታሪኩ ብቻ ገምግመን ልንኮንነው ከተነሳን Prejudiced ከመሆን አልፈን Stereotyope ሆነናል ማለት ነው። የአንድ ቡድን የተወሰኑ አባላት በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ አንድ ድርጊት አድርገው በዚያ ሳቢያ ጥላቻ ሊፈጥሩ ይችላሉ። ይህን ሁኔታ ስንመረምር ድርጊቱ ተፈጸመ የተባለበትን ወቅት በደምብ ማጤን ይኖርብናል። ጊዜ በተለወጠና የቡድኑ አባላት በአዲስ ትውልድ በተተካ ቁጥር የአዕምሮ ብስለትም እያደገ ይመጣልና የጥላቻ መሠረቱ የሆነው ነገር አብሮ ይጠፋል። ይህን ሐቅ ለመረዳት አለመሞከር ትልቅ ደካማነት ነው።

ከላይ በመጠኑ በሕዝቦች መሐል ሊፈጠሩ የሚችሉት ጥላቻዎች ዓይነትና መነሻቸውን ከሶስዮሎጂና በመጠኑም ከስነልቡና (psychology) አንጻር ላትት የሞከርኩ ሲሆን ከዚህ የበለጠ ትንተና ሊኖር አይችልም ለማለት አይደለም። ምናልባትም በአሁኑ ጊዜ ያለፈ ታሪክን ብቻ በማንሳት የአገራችንን ሁኔታ ለመገምገም ለምንሞክር ሰዎች ይህም ሌላ አቅጣጫ ይጠቁምና ሰፋ ያለ ውይይት ሊከፍት ይችላል የሚል ግምት አለኝ።

በሚቀጥለው ጽሑፌ ይህንን ከላይ የገለጽኩትን ግንዛቤ አሁን በአገራችን ላይ እየተፈጠረ ካለው ሁኔታ አንጻር ለመገምገም እሞክራለሁ። በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች፤ በጎሣዎችና ዘሮች መሐል ሊፈጠሩ የሚችሉትን አለመግባባቶች በማጉላት ወደ መጥፎ ጥላቻእንዲመራ ቅራኔዎችን የሚያጐሉ ኃይሎች መግር ያለባቸው ጉዳይ አለ ባይ ነኝ። በተለይ ደግሞ ይህን ጥላቻ እንዲያከር የሚያደርገው ኃይል የመንግሥት አካል ሆኖ ከተገኘ ብዙ አጠያያቂ ነገሮች ሊኖሩ ይችላልና እስቲ በሰፊው እንወያይበት።

---

አንበርብር የጂዎርጂያ ነዋሪ ናቸው።

---

# ዶክተር ታዬ . . .

( ከገጽ 15 የዞረ)

የፖለቲካ ውሸት ብዙ መሪዎችን "Pathological Liars" የሚሏቸው ዓይነት አድርጓቸዋል። ዝም ብሎ ውሸት በየምሽቱ እየፈጠሩ ያወራሉ። እዚህ ስመጣና ብዙውን ስጠይቅ "ምንድነው የሰማችሁት?" ብዬ ስል Distorted የሆነ ብዙ ነገሮች ሰማሁ። ከአገር ውስጥም ከውጪም በፋክስና በስልክ ብዙ ድጋፎች ደርሰውናል። አገር ውስጥ Hunger Strike እናደርጋለን ያሉ ድርጅቶች፣ ከሱዳን በእግራቸው የገቡ ኢትዮጲያውያኖችም እንደነበሩም ሰምተናል። የሰላም አስፈላጊነት ትልቅ መሆኑን በታላቅ ስሜት ነው የተቀበሉት። እዚህ ላይ ማከል የምፈልገው ነገር ቢኖር ጉባኤው እንደዚያ ያለ ሕዝባዊ ድጋፍ ያለው መሆኑን የተረዱት የጉባኤው ተካፋይ የድርጅትና የብሔረሰብ ተወካዮች በሙሉ ስሜትና ሁኔታ ነበር በጉባኤው የተካፈሉት። የሙያ ማህበራት እንኳን ሳይቀሩ የተገኙበት ስብስባ ነበር። የተገኙት ሁሉ በሙሉ ልብ ነበር የተሳተፉት፤ ብዙ ስብሰባዎች ተሳትፌአለሁ፣ አይቻለሁ፤ በዚህ ስብሰባ ለክርክር ብሎ የሚቃወም አላየሁም። ስብሰባው በጥሩ መንፈስ ያለቀ መሆኑን አይቻለሁ፣ እመስክራለሁ። አስቸጋሪ ናቸው የምንላቸው ነጥቦች እንኳ፣ ብዙ ክርክር በሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ላይ እንኳ በሙሉ ልብ ነበር የተሳተፉበት። ይህን ሁሉ ያመጣው በተደረገው ሕዝባዊ ድጋፍ የተገኘው የተሳታፊዎች ልበ ሙሉነትና ቆራጥነት ነው እላለሁ።

ላንዳፍታ–በጉባኤው የተወሰኑ አበይት ናቸው የሚሏቸው ውሳኔዎች የትኞቹ ናቸው?

ዶ/ር ታዬ – 1ኛ. የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት የመቋቋሙ ነገር በሙሉ ድምፅ ጸድቋል። ምክር ቤቱ ዋና ጽሕፈት ቤቱ አዲስ አበባ ሆኖ እንዲሠራ በመወሰን ሥራውን ጀምሯል። የዛሬ 2 ዓመት ተኩል የተሠራውን ስህተት ደግሞ ላለመፈጸም ሁሉንም አቀፍ የሆነ ምክር ቤት ነው። ይህን ምክር ቤት የመሠረተው ጉባኤ የሙያ ማህበራትን፤ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የሠራተኛ ማህበራትን ያቀፈ በመሆኑ ሁሉን አቀፍ ነው። የ31 አገሮች ዲፕሎማቲክ አባሎችና ብዙ NGO's በተመልካችነት መገኘታቸው ይህ ውሳኔ በሙሉ ድምጽ ለመጽደቁ ምስክሮች ናቸው። 2ኛ. የሽግግሩ መንግሥት ዕድሜ ጥር 14 ስለሚያልቅ ሁሉንም ኃይሎች ያቀፈ አዲስ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም በሙሉ ድምፅ ተወስኗል። እነኚህን ሁለት ውሳኔዎች አበይት ናቸው እላለሁ።

ላንዳፍታ– ጉባኤው በስፋት የተናገረባቸውን ሌሎች ጉዳዮች ሊያብራሩልን ይችላሉ።

ዶ/ር ታዬ– አዲሱን የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም በሚደረገው ጉዞ ላይ በአስቸኳይ ትልልቅ ውሳኔዎችን ወስዶ እንዲጨረስ ከሰባት ያላነሱ ነጥቦችን ወስኗል።

1. የተወካዮች ምክር ቤት መቋቋም ሁሉንም ኃይሎች እንዲያካትት፤

2. የጦሩን ጉዳይ በተመለከተ – ኢህአዴግ የሚመራው ጦር ነው ያለው። በአስቸኳይ ፕሮፌሽናል የሆነ army ለአንድ ሰው ተገዢ ያልሆነ ታማኝነቱ ለአገሩ የሆነ ጦር እንዲቋቋም መደረግ እንዳለበት።

3. ለስድስት ወር ያለ ፖሊስ ኖረናል። ኒው ዮርክ ለአርባ አምስት ደቂቃ ያለ ፖሊስ ቢሆን ይታያችሁ። የኢትዮጲያ ሕዝብ ምን ያህል ሥነሥርዓት እንዳለው ነው የምንረዳው በዚህ። ፖሊስ አስፈላጊ ነው። አሁን ያለው ፖሊስ ታማኝነቱ ለኢህአዴግ ብቻ ስለሆነ ለሕዝብ የሚያገለግል ፕሮፌሽናል ፖሊስ ማቋቋም እንደሚያስፈልግ፤

4. የሰኔው ምርጫ በአለም አቀፍ ታዛቢዎች እንደተገለፀው፤ በአገርም ያለው ሕዝብ እንደተመለከተው ሁሉ ጉባኤውም አልተቀበለውም። ምርጫው እንዲሰረዝና፤ ወደፊት ዴሞክራቲክ የሆነ ሁኔታ ሲመቻች ምርጫ እንዲካሄድ፤

5.የነፃ ፕሬስ ጉዳይን በተመለከተም የነፃ ጋዜጠኝነት ባህል እንዲጠናከር ድጋፍ እንደሚያስፈልገው፤ እዚህ ላይ ፕሬስን በተመለከተ አንዳንድ ነገር ብጨምር ደስ ይለኛል። ጥንትም አሁንም ቴሌቪዥንና ሬዲዮ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ናቸው። አሁን ያሉት በሽግግሩ ወቅት የሽግግሩን መንግሥት ስሜትና ሊሰራቸው የሚገባቸውን ሳይሆን የኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች ናቸው። ይህ ሁኔታ መቀየር አለበት። ነፃ መሆን አለባቸው። ከ30–40 ነፃ ጋዜጦችና መጽሔቶች በኢትዮጲያ ውስጥ አሉ። እነዚህ ነፃ ጋዜጦች ብዙ ነገሮች ያጋልጣሉ። "ይህ ዴሞክራሲ አይደለም ወይ? ይህ በደርግ ጊዜ ነበር ወይ? የሚሉ ክርክሮች ሊነሱ ይችላሉ። አዎ በአሁኑ ጊዜ ሰዎች የሚጽፉትን ይጽፋሉ፣ በዚያም ይታሠራሉ። የአፍሪካ ቀንድ፣ የኢትዮጲስና የጦማር ጋዜጦች ባለቤቶችና ፀሐፊዎች እስር ቤት ይገኛሉ። በተለይ የኢትዮጵስ ጋዜጣ አዘጋጅ ተፈራ አስማረ በእስር ላይ ባሉበት ሁኔታ መደባደባቸው ጋዜጣ ላይ ወጥቷል። ይህ የጋዜጠኞች መጕሣቆል አለ። ግን ባህሉ በስፋት እየተካሄደ ነው። ከአሁን ወዲያ ወደኋላ ሊመለስ የሚቻልበት ሁኔታም ያለ አይመስለኝም። መንግሥት መንገድ ላይ መሸጥ አትችሉም የሚል ፖሊሲ አውጥቶ ልጆች መንገድ ላይ ሲሸጡ ይነጠቃሉ፣ ይታሠራሉ። ቢሆንም በየጥጉ መሸጣቸው አልቀረም። ሰው በጥዋት በድብቅ ይከፋፈላል። ያ ባህል አለ። በመንግሥትም ሆነ በሌላ አካላት ወንጀሎች በሚፈፀሙበት ጊዜ በማጋለጡ ደረጃ ትልቅ ሚና የተጫወቱት ነፃ ጋዜጣዎች ናቸው።በመንግሥት ጋዜጦች ይሠሩ የነበሩ ብዙዎቹ

ተባረዋል። እንዳጋጣሚ በነፃ ጋዜጣ ውስጥ እየተቀጠሩ ማጋለጥ ጀምረዋል። አዲስ ዘመን ድሮ በሰልፍ የሚገዛ አሁን ግን ክፍለ ሀገር የሚላከው እንደተጠቀለለ ሳይሸጥ ተመልሶ ይመጣል። ጉባኤው በአዲሱ የሽግግር መንግሥት ሕዝቦቻችን ጋ ለመድረስ የሚያስችለን የነፃ ጋዜጣ ሁኔታ እንዲመቻችና ተፅዕኖዎች እንዲነሱ ወስኗል።

5. የፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በተመለከተም፤ ድርጅቶች እንቅስቃሴያቸው ታፍኖ በአሁኑ ጊዜ የሚንቀሳቀሱት በአዲስ አበባ ዙርያ ብቻ ነው። የደቡብ ሕዝቦች ህብረት ሃላፊዎች ያሉት አዲስ አበባ ነው። የራሳቸውን ሕዝቦች ሄደው ማናገር አይችሉም። ደጋፊዎቻቸው ደግሞ በየጊዜው እየታሰሩ ይፈታሉ። በየቦታው ሄደው መንቀሳቀስ ስለማይችሉ ቻርተሩ የሰጠውን መብት እንኳን ማክበር አቅቶታል። ድርጅቶች መሥራት ይችላሉ፣ ዴሞክራሲ አለ የሚለው ቻርተሩ ራሱ የፈጠረው ሁኔታ ከአዲስ አበባ እንኳ መውጣት አልተቻለም። የድርጅት ተወካዮች የራሳቸውን ሕዝብ (Consitituency) እንኳን ሄደው ማናገር አልቻሉም። እነዚህ ድርጅቶች ሕዝባቸውን ሄደው ከችግሩና ከስሜቱ ጋር አብረው እንዲሆኑ ያስፈልጋል የሚል አቋም ተወስዷል።

6. በሽግግር መንግሥቱ የታወጁት አዋጆች፣ የተፈረሙ ውሎች በተመለከተም፤- በዚህ 2 ዓመት ተኩል የወጣው አዋጅ እጅግ ብዙ ነው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ያህል አዋጅ ሲወጣ ታይቶ አይታወቅም። በሚኒስቴር ደረጃ ብዙ አዋጅ በመፈረም የሚታወቁት የውጭ ንግድ ሚኒስቴሩ አቶ አብዱልመጂድ ናቸው። (አቶ አብዱል መጂድ ኢትዮጲያዊ አይደሉም፣ የሶማሌ ዜጋ ናቸው የሚል ወሬ በሰፊው ይሰፍናል።) በውጭ ጉዳይ በኩል ብዙ የተፈረሙ ውሎች አሉ። እነዚህ ውሎች የኢትዮጲያ ሕዝብ የማያውቃቸውና የሽግግሩ መንግሥት የተሰጠው መብት (mandate) ስለሌለ እነዚህ ውሎች በሙሉ ጠቃሚ እስካልሆኑ ድረስ መጣል አለባቸው። ብዙ ውሎች ተካሂደዋል። አባይን በተመለከተ፣ በሱዳንና በኢትዮጲያ መካከል የሚሊተሪና የኢካደሚ ግንኙነትን በተመለከተ፣ ወዘተ...ውሎች ተደርገዋል። እነዚህ ጊዜውን ጠብቀው ከተገመገሙ በኋላ የኢትዮጲያን ጥቅም የማያስከብሩ ውሎች ሁሉ መሰረዝ አለባቸው። አዲስ የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ይህንን ቅድሚያ ሰጥቶ እንዲሠራ ተወስኗል።

ላንዳፍታ፤ እነኚህን ጠንካራ ውሳኔዎች ለመወሰን ሰፋ ያለ ውይይት የተካሄደ ይመስለናል። በአሁኑ የሽግግር ወቅት የተካሄዱት ነገሮችም በሰፊው የተገመገሙም ይመስለናል፤ የውይይቱን ፍሬ ሀሣቦች አጠር አጠር አድርገው ሊያስረዱን ይችላሉ፤

ዶ/ር ታዬ፤- በ2 ዓመት ተኩል ውስጥ የተደረጉትን ነገሮች ጉባኤው በሰፊው ተወያይቶበታል።

በውይይቱ መልክ የቀረበው የሽግግሩ የ2ት ዓመት ዴሞክራሲ ሂደቱን ገምግመናል። በቻርተሩ ላይ የተገባውን ቃል ራሱ መንግሥት ከማንኛውም የበለጠ ጥሶታል። ስለዚህም የዴሞክራሲ ሂደቱ መክኗል። ሊወለድም ሊያድግም ስለማይችል ነው ሌላ የሽግግር መንግሥት መቋቋም አለበት የተባለው። በግምገማችን መሠረት መክኗል የሚያሰኘውን ሁኔታ የፈጠረው:-

1ኛ. አገር በጐሣ ፖለቲካ (Ethniic Politics) መመራት አይችልም። ይህ በብሔረሰቦች መካከል ትልቅ ግጭት ፈጥሯል። ግጭቱ ማበጣበጥ ደረጃ ደርሷል። ቤት አንኳኩቶ ትዳር አፍርሷል፣ ባልና ሚስት አፋቷል። ድሮ አንድ ሰው ዕቃ ለመግዛትም ወደ መደብር፣ ለመዝናናት ወደመዝናኛ ቦታ ሲሄድ "የማ ሱቅ ነው?" ብሎ ጠይቆ የማያውቀው ሕዝብ አሁን "የማ ቤት ነው " ብሎ መጠየቅ ተጀምሯል። ይህ ሕዝብን የሚያቀራርብ ሳይሆን የሚያራርቅ ነው። በዕድር አቅም እንኳ ድሮ ዘር ተለይቶ አልነበረም ዕድር የሚገባው። የትግሬ ዕድር፣ የአማራ ዕድር፣ የኦሮሞ ዕድር ተብሎ አይታወቅም። አሁን ግን መልኩን ቀይሯል።

በሕብረተሰብ ደረጃ የጐሣ ፖለቲካ የሚመራው ሕዝብን ወደ ማጋጨትና ወደ ጦርነት ነው። ስለዚህ ይህ ጉባኤ እየተካሄደ ያለውን የጐሣ ፖለቲካ የዴሞክራቲክ ፈር ያልያዘና ሂደቱ መጥፎ መንገድ የያዘ፣ ሕብረተሰብን የሚያጋጭ ሆኖ አግኝቶታል።

2ኛ. ሰዎች የሚሾሙት፣ የሚሻሩት በችሎታቸው (merit) ሳይሆን በብሔረሰባቸው ነው። በውል በኔ አካባቢ ያለውን ልነግራችሁ እችላለሁ። አዲስ አበባ አካባቢ የትምህርት ቤቶች ዲሬክተሮች እንውሰድ። በመሠረቱ ዲሬክተር የሚሆኑ የዲሬክተርነትን ችሎታ ያሟሉ፣ ዕውቀቱ ያላቸው፣ ኮርሶች የወሰዱ መሆን ሲገባቸው ወደ 85% ትግሬ በመሆናቸው ብቻ ችሎታው ሳይኖራቸው ዲሬክተሮች ሆነዋል። ይህ (Mere Coincidence) በአጋጣሚ የሆነ አይደለም። በፕላን የተደረገ ነው። በየቦታው ሹመት ሽረት በብሔር ነው። ይህ እንግዲህ የዴሞክራቲክ ሂደቱ ትልቅ ችግር ውስጥ እንዳለ ነው የሚያስረዳን። ናዝሬት ያደግሁበት ቦታ ነው። እዚያ የሆነውን አንድ ነገር ልንገራችሁ። አንዱ ጓደኛችን ከአሚሪካን መጥቶ አንድ እንዲስተሪ ለመክፈት ፈልጐ ማዘጋጃ ቤት ይሄዳል።

"ብሔረሰብህ ምንድነው?" የቀረበለት የመጀመሪያ ጥያቄ፣

"ናዝሬት ነው የተወለድኩት፣ የናዝሬት ልጅ ነኝ" ይላል።

"እሱ አይደለም ብሔረሰቦን ነው የጠየቅነው" ይባላል።

"ቤተሰቦቼ አባቴ እናቴ አማሮች ናቸው።"

"በዚህ ከተማ በአሁኑ ጊዜ ቤት እንዲሰራ ኢንዱስትሪ እንዲከፍት ቅድሚያ የምንሰጠው ለኦሮሞ ነው።" ተብሎ ተሸኘ።

ይህ እንግዲህ በየቦታው እየሆነ ያለ ነገር ነው። የዚህ ዓይነት ወሰን (Boundary) መወሰን ብዙ ችግር ይፈጥራል።

3ኛ. አንድ ብሔርና ብሔረሰብ የሌላውን ኢትዮጲያ ብሔረሰብ ታሪካዊ ደመኛ አድርጐ የመውሰድ ሁኔታ በጣም አደገኛ በመሆኑ ይኸው አዝማሚያ በአስቸኳይ የሚጠፋበትን መንገድ ፈልጐ ሕዝቦች እንዲቀራረቡ የሚያደርግበትን ሁኔታ መሻት ሲገባ የምናየው የተገላቢጦሹን ነው። በምሳሌ ለማስረዳት፣ "የአማራው ሕዝብ በዚህ ሕዝብ ላይ የፈፀመው ወንጀል..." እየተባለ እንደዚህ በጅምላ አንድ ላይ ተወስዶ የሚባለው አባባል ትክክል አይደለም። አሁን ኢህአዴግ ራሱ እንኳ ይህን ማጠቃለል ያቃተው ይመስላል። "ጨቋኝ አማራ"..."ጭቁን አማራ" የሚል ቋንቋ ደግሞ ፈጥሯል። ይህን 2ት ዓመት ተኩል መንግሥት የInformationንና Disinformation ጽንስ ሀሣቦችን በተግባር በማዋሉ ሕዝቡ ትልቅ ውዥንብር ውስጥ ገብቷል። በዚህ ውዥንብር አንዱ ሌላውን እስከመግደል የደረሰበት አለ፤ በመምህራን ደረጃ የማውቀው፣ "አንተ ከዚህ ክልል የመጣህ ነህ? አንተ ከዚያ ክልል የመጣህ ነህ" በመባል ይደበደባል። በአርሲ የተፈፀሙ ነገሮችን ማንሳት ይቻላል። እነኚህ ጥፋቶች ትምህርት ሆነው ወደፊት የሚሻል የመቀራረብ ሁኔታ የሚፈጠርበት ሁኔታ እንዲደረግ ነው ፍላጐታችን።

4ኛ. አንድ ኢትዮጲያዊ በማንኛውም ቦታ በኢትዮጲያዊነቱ ኩርቶ የመኖር መብቱን የሚያስከብርበት ሁኔታ አልተፈጠሩም። የግለሰቦች መብት በግልፅ አልተቀመጠም። ግለሰቦች በየቦታው ተንገላተዋል። የግለሰቦች መብት የዴሞክራቲክ ሂደቱን ጠንካራ ስለሚያደርገው ይህ ወደ ፊት በግልፅ ሁኔታ እንዲቀመጥ ያስፈልጋል ነው የምንለው።

5ኛ. ከባድ የውይይት አጀንዳ የነበረው የኢትዮጲያ ሉአላዊነትና የብሔር ብሔረሰቦችን መብት የተመለከተ ነበር። የመጀመሪያው ክርክራችን አጀንዳው እንዴት ይካሄድ የሚል ነበር። በተለይ የሽግግር መንግሥቱ የሰላሙን ጉባኤ ስላልደገፈ ስብሰባው ተረግጠ የሚወጣበትን ሁኔታ በተስፋ ነበር የሚጠብቀው። ይህ Issue በኢትዮጲያ ፖለቲካ ውስጥ ብዙ ዓመት ሲያጨቃጭቅ የቆየና የበፊቱን ሕይወታችንን በሙሉ ያከራከረን ጉዳይ ነው። ይህ አጀንዳ በጣም አስፈርቶን ነበር። ብዙዎቻችን Nervous ነበርን። በጣም አጨቃጫቂ ይሆናል ተብሎ ተገምቶ ነበር። በርግጥም ረጅሙን ሰዓት የወሰደው እሱ ነበር። ስብሰባው ግልጥ ባለ መልክ የኢትዮጲያን ሉአላዊነት ተቀብሎ በዚያች ሉአላዊ አገር ውስጥ የብሔር ብሔረሰቦች መብት የራሳቸውን አስተዳደር፣ ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውን፤ በየአካባቢያቸው የሚያደርጉት ነገሮች የሚከበርበት ሁኔታ፣ ከዚያም አልፎ ተርፎ ሌላው ብሔረሰብ ወይም ግለሰብ በብሔሩ Discriminate የማይደረግበት ሁኔታ ግልፅ ባለ መልኩ በደንብ አድርጐ ማስቀመጥ ይኖርበታል በሚለው ሙሉ መተማመን ላይ ተደርሷል። በኢትዮጲያ ሉአላዊነት ተስማምቶ የነዚህን ብሔረሰቦች መብት የሚያስከብር ሁኔታ እንዲፈጠር በሙሉ ድምፅ አሳልፎታል።

6ኛ. ኤርትራን በተመለከተ:- አስፈሪ የነበረው የኤርትራን ሁኔታ ብዙ ሰዎች አይወያዩም ብለው ነበር። ምክንያቱም በዚያ አካባቢ ያለው ኃይል ይታወቃል። ያለው የEPLF ኃይል ነው። የኤርትራ ጉዳይ ምንም በReferendum ቢያልቅም የኢትዮጲያ ሕዝብ ስላልተሳተፈበት በስፋትና በግልፅ እንዲወያይበት የራሱን አቋም እንዲወስድ ለሕዝቡ ይህን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ ተነግሮ ውሳኔዎችም ለኢትዮጲያ ሕዝብ እንዲነገረው አቋም ላይ ተደርሷል። አሁን የምናየው የኤርትራን አዲስ አገርነት ብቻ ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ እንደ Confederation ያለ ይመስላል። ምክንያቱም ብዙዎቹ ነገሮች በግልፅ ተጨባጭ በሆነ መንገድ ስለማይታዩ ይህን ነገር የኢትዮጲ ሕዝብ በደንብ ተወያይቶበት ወደፊት ከኤርትራ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበት ሕዝቡ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል በሚል ተስማምቶ፣ የሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ በኢትዮጲያ ሕዝብ መወሰን አለበት ተብሎ ተወስኗል። በተለይም በኤኮኖሚው ሁኔታ፣ የባንኮች በእኛ ገንዘብ መጠቀም ሁኔታ ተነስቷል። ኤርትራ ሌላ አገር እስከሆነች ድረስና Central Bank ኢትዮጲያ ውስጥ እስከሆነ ድረስ ቁጥጥሩ በኢትዮጲያ መንግሥት መሆን ሲኖርበት የተለየ ባንክ አቋቁመው በአንድ Currency መሥራት እንደሌለባቸው የተነሱ ክርክሮች ሁሉ ነበሩ።

6ኛ. የቻርተሩ ዕድሜ ጥር 14 አልቋል። ቻርተሩ ዕድሜውን ወስኖ ነው የቀረበው። 2 ዓመት ግፋ ቢል ካላለቀ 6 ወር ይጨምራል ይላል ቻርተሩ። እሱም ጥር 14 ያልቃል። ከዚያ አንድም ቀን አይጨምርም ይላል ቻርተሩ። እንግዲህ የመጨረሻው ፈተና ነው። የሽግግሩ መንግሥት ሌሎቹን እንደመብት ያስገባቸውን ከጣሰ ያንን ቻርተር ደግሞ ከደመሰሰ፣ እንግዲህ እራሱ ላወጣው ሕግ ባለቤቱ ተገዢ ካልሆነ ሌላው እንዲገዛ እንዴት ይታሰባል? በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብም ዘንድ ቻርተሩ ተቀባይነት ያለው እስከዚያ ድረስ ነው። አልቆለታል። እንግዲህ የጉባኤው ውሳኔ ቻርተሩ የሰጠው ጊዜ ሲያልቅ አዲስ ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ነው።

7ኛ. ሕገመንግስትን በተመለከተ የማርቀቁ ጉዳይ 2 ዓመት ያህል ተሞክሯል። እስከአሁን ድረስ አላለቀም። የኢትዮጲያ ሕዝብ የማይፈልገውን ነገር

ፀጥ ባለ መልኩ መቃወም የሚችል ሕዝብ ነው። ሕገመንግሥቱ እየተረቀቀ ነው፣ ሕዝቡ ሊሳተፍ ይችላል፣ ካልፈለገው በሙሉ ሊለወጥ ይችላል በማለት እስከዚያ መብት ተሰጥቶ ሕዝቡ በየቀበሌው ተሰብሰብ ተባለ። በጣም የሚገርመው እኛ በመምህራን አማካይነት Poll ወስደናል። አዲስ አበባ ብዙ ሕዝብ ወጣበት የተባለው የቦሌ ቀበሌ ነው። ወደ 15,000 ሕዝብ ይኖርበታል። የመጣው 52 ሰው ብቻ ነበር። በሥራ ቦታ ላይ ተሳትፎ አድርግና ተነጋገርበት ቢባልም ሕዝቡ በዚያ ተቃውሞውን ያሰማ ነበር። ይኼን የፖለቲካ ቋንቋ የሚያውቅ መሪ ቀርቶ ማንም መረዳት የሚገባው የፖለቲካ ባህል ነው። ያንን ማወቅ ካልተቻለ ዝም ብሎ መለፍለፍ ብቻ ጥቅም የለውም። የሕዝብን ተቃውሞ መለካት መቻል ያስፈልጋል። ሕዝብ የሚስማማበትን ይደግፋል፣ የማይስማማበትን ይቃወማል። ለምሳሌ ለሰላሙ ጉባኤ 300,000 ሰው ሲወጣ ትቀጣለህ ሳይባል፣ በቀበሌ ሳይታዘዝ በራሱ ስሜት የወጣ ሕዝብ ነው። እስቲ ሞክሩኝ ብሏል የኢትዮጲያ ሕዝብ፣ አንድ ቀን ፍቀድልኝና መቃወሜንና መደገፌን በሰላማዊ ሰልፍ ልግለፅ ብሏል። በዚያው አኳያ ሕዝቡ የዚህ የሕገመንግሥት ማርቀቅና መደገፍ ሁኔታ ዝም ብሎ ጥሎታል። አልተቀበለውም። የሰላሙን ጉባኤ ግን በትልቅ ደስታ ነው የተቀበለው። እና ይህን መለካት መቻል ብዙ ዕውቀት አይጠይቅም። ይህን ለማስረዳት ስሞክር አንተ የምታወራው ስለ አዲስ አበባ ነው፤ ሰማንያ በመቶው የኢትዮጲያ ሕዝብ ገበሬው ከእኛ ጋር ነው የሚባል ቋንቋ አለ። ግን የኢትዮጲያ ሕዝብ ባላገሩንና ከተሜውን መለየት የሚችል አይመስለኝም። ይሄን ያህል ትልቅ gap ያለ አይመስለኝም። ብዙዎቻችሁ አዲስ አበባ ልትኖሩ ትችላላችሁ። ማናችሁ ቤተሰቦቻችሁ ክፍለ ሀገር የሌሉ? ይህ የገበሬው ድጋፍ አለን የሚሉት ነገር ያልተጨበጠና በጣም አጠራጣሪ ነገር ነው። በሕገመንግሥቱ ማርቀቅ ላይ ሕዝቡ አልተሳተፈም። ጉባኤው መሆን አለበት ብሎ ያመነበት በደንቡ መሠረት Assembly ተመርጦ ያ Assembly የሚመርጣቸው ሰዎች ሕገመንግሥቱን ያረቁና ረቂቁ ወደ ሕዝቡ ሄዶ በሕዝብ ፈቃደኝነት ተሳትፎ ተደርጐ በሕዝቡ ነው ተፈፃሚነት የሚኖረው የሚለውን ነው።

8. የኤኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳይ በተመለከተ:- የመጣው ፖለቲካ በሕብረተሰቡ መሐል የፈጠረው ችግር አስጊ ሁኔታ ላይ የደረሰ በመሆኑ ይህን ሁሉ ጉባኤው ከማህበራዊ ገጽታው አንፃር በሰፊው ተመልክቶታል። የኤኮኖሚው ጉዳይ ከተነሳ ፕሬዚዳንት መለስ በቀደምለት ኤኮኖሚው 7% አድጓል ብለው ገልፀዋል። መቼም መሃይም አይደለሁም። እኔ የታየኝ እድገት የለም። የሥራ ማጣቱ (Unemployment) ሰማይ እየነካ እየሄደ ኤኮኖሚ አደገ የሚባለው አይገባኝም። ኤኮኖሚው እየደቀቀ ነው።

በየቀኑ እያደገ የመጣው ሥራ አጥነት በትምህርት አካባቢ ያለውን ስሜት እንዲሞት አድርጐታል። ምክንያቱም እዚያ ላይ ያሉትን የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮች አውጥቶ መንገድ ላይ መጣል የቻለ መንግሥት እኛንማ ድራሻችንን ነው የሚያጠፋው የሚል አስተሳሰብ ተፈጥሯል። ነፃ ኤኮኖሚ ተብሏል። ኤኮኖሚው ምን ያህል ነፃ ነው። እኛ ከሌላው ዓለም የምንወዳደርበት ዓይነት ማለት ነው? አንድ የአቃቂ ፋብሪካ የማህበር መሪ ያለውን ልጥቀስላችሁ። "ዛሬ ኢትዮጲያ በሳልቫጅ ኤኮኖሚ ላይ ናት። ንፁህ ሸሚዝ አንለብስም፤" ዘጠና በመቶው የኢትዮጲያ ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ ከሳልቫጅ አርሚ የሚመጣለትን ልብስ ነው የሚለብሰው። ይህ የማህበር መሪ የተናገረውን ብናጤነው የኛ ኤኮኖሚ፣ የኛ ላብ የኢትዮጲያን ሕዝብ አዲስ ሸሚዝ እንዳይለብስ አድርጐታል ማለቱ ነው። የተተካው የሳልቫጅ ልብስ ነው። ለዚያውም ለመወዳደር የማንበቃበት። ያየነው ሁኔታ እኛ አንድ ሸሚዝ በምናመርትበት ዋጋ ታይዋንና ኰርያ አስር ሊሰጡ ይችላሉ። ከነዚህ ጋር ነወይ የምንወዳደረው? ይመጣሉ ነጋዴዎች ከኛ ውስዱ ስትላቸው አንወስድም ይላሉ። ፋብሪካው ምርታማ ስላልሆነ ይዘጋ ይባላል። በብዛት አምራች አይደሉም እየተባለ ፋብሪካዎች አሁን ትልቅ ችግር ውስጥ ነው ያሉት። ብዙዎቹ ሠራተኞች እየተባረሩ ነው። አንዳንዱም እየተዘጋ ነው። በዚህ ዓይነት የኤኮኖሚ ሁኔታ የኢትዮጲያ ነጋዴዎች ራሳቸውም እንኳ ቢሆን መወዳደር በማይችሉበትተ ሁኔታ ላይ መሆኑን በማሳየት የኤኮኖሚው ሂደት በተቻለ መጠን በደንብ ተገምግሞ Protection የሚያስፈልገው Protection ተደርጐለት ኤኮኖሚው በኤክስፐርቶች በተጠና መንገድ ጥሩ ሁኔታ እንዲይዝ በሚል የኤኮኖሚ ኤክስፐርት የሆኑትን ጉባኤው በመጋበዝ ውይይት አካሂዷል። በዚህ መሠረት ይህንን ነፃ ገበያ መሆኑን ብቻ ማየት ሳይሆን ኢትዮጲያን ይጠቅማታል የሚለው መንገድ ከተጠና በኋላ የዚያን አቅጣጫ መያዝ ያስፈልጋል። በነፃ ኤኮኖሚ ሰበብ በአሁኑ ጊዜ የተከፈተው ለውጪ ነጋዴዎች ጥቅም መስጫ እንጂ የኢትዮጲያ ነጋዴዎች የሚጠቀሙበት ስላልሆነ ይህ ጉዳይ በስፋት እንዲታሰብበት ተደርጓል።

ላንዳፍታ፤ - የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ሊቀመንበር እንደመሆንዎ መጠን ስለማህበሩ ሁኔታ ጥቂት ቢገልጹልን? ይህ ማህበር በፖለቲካው ትግል አኳያ ምን ዓይነት ሚና ሊጫወት ይችላል ይላሉ?

ዶ/ር ታዬ፤- በአሁኑ ጊዜ ሊደረጉ የሚገባቸውና ጥንካሬ ሊሰጣቸው የሚገባ የዴሞክራሲ ኃይሎች ኢትዮጲያ ውስጥ እነማን ናቸው? ይህ ድርጅት ከዚያ ድርጅት ይሻላል ልላችሁ አይደለም። እኔ የምለው ማንኛውም ኃይል ኢትዮጲያ ውስጥ ገብቶ እንደፈለገ ሊገዛ የሚችለው የሕዝቡ የዴሞክራቲክ ጉኑ ጠንካራ እስካልሆነ ድረስ ብቻ ነው። በዚህ

አጋጣሚ የኢትዮጲያ ሕዝብ አጋር ነኝ የሚል ሁሉ እነዚህን የዴሞክራቲክ ጐኖች እዚያው ሆነው የሚሰጡት ማለትም እንደ ሙያ ማህበራት (Professional Associations) ያሉትን መደገፍ፤ ሲጠቁ ማጋለጥ ያስፈልጋል እላለሁ። ለምሳሌ የመምህራን ማህበርን ለማንሳት እፈልጋለሁ። ይህ ማህበር ትልቅ የዴሞክራሲ ምሽግ ነው። አርባ አምስት ዓመት የቆየ ማህበር ነው። ከዚህ በፊት በዴሞክራቲክ መብቶች ትግሎች ውስጠ የተሳተፈ ነው። ብዙም ጊዜ ጐኑን ሰብረውታል። ከዚያም አልፎ ተርፎ ካድሬም አድርገውታል። በተቻለ መጠን ይህ ድርጅት ጥሩ የዴሞክራሲ ኃይል እንዲሆን ከተፈለገ ማህበሩ መብቱን የሚያስከብርበት Mechanism እንዲከበርለት ትልቅ የሞራልና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚያስፈልገው ነው። በኢትዮጲያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የኛ ማህበር ዘጠኝ ወር ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የባንክ ሂሣቡ ተዘግቶበታል። መንግሥት የዘጋው ሂሳብ ገንዘብ የመምህራን ወራዊ የአባልነት መዋጮ ነው። እየለመንን ነው ማህበሩን እስካሁን ድረስ የምናንቀሳቅሰው። ፍርድ ቤት ቀርበን መንግሥትን ከሰን በጐን ባለሥልጣኖች ይሄዱና "ፍርድ ቤት ቢፈርድም አትስጧቸው" ይላሉ። ፍትህና ፖለቲካ ምን ያህል እንደሆነ ማየት ትችላላችሁ። ለሦስተኛ ጊዜ ፍርድ ቤት ስንሄድ አምስት ሺህ የአዲስ አበባ መምህራን ግልባጥ ብለው ፍርድ ቤት ይሄዳሉ። ከዳኛው ጋር ፍጥጥ፤ የሕዝብ ኃይል ነውና ዳኞቹ ይፈራሉ። "ያፈራረደናል ቀን ሲያልፍ፣ ይህቺን ፍትህ ታዛቡና" ይላሉ መምህራን። በመጨረሻም የፖለቲካ አጋር እንዳይሆኑ መንግሥትን ፈሩ፤ በእኛ ላይ እንዳይፈርዱ ሕዝቡን ፈሩ። ስለዚህ ጥሩ መንገድ አድርገው የወሰዱት ቀጠሮውን አፈናጥረው ለረዥም ጊዜ መቅጠር ነበር። ዓላማቸው ገንዘባቸው ሲያልቅና ሲሰቃዩ ይወድቃሉ ነው። በገዛ ገንዘባችን። እና የምንለው ይህ ማህበር የዴሞክራቲክ መብቱን እያስከበረ፣ በዴሞክራቲክ ኃይሎች እየታገዘ፣ በቅርብ ደግሞ የሚያገኛቸውን ወጣት ልጆች መብትና ግዴታቸውን በማስተማር በጥሩ ባህል ሊያሳድግ ይችላል። ከዚያም አልፎ ደግሞ በየመሥሪያ ቤቱ የሚሠሩ የሙያ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ድርጅቶች እነዚህ ባለሙያዎች የኛ ጥቅም የሚከበረው የዚህ አይነቱን ድጋፍ ሲያገኙ ነው። እነዚህ ድርጅቶች ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል እላለሁ።

ላንዳፍታ፤- ለጉባኤው ውጭ ካሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች የተላኩትና ሳይሳተፉ መንግሥት ያሰራቸው ልዑካን ጉዳይስ ምን ደረሰ?

ዶ/ር ታዬ፤- ለሰላሙ ጉባኤ የመጡ ኢትዮጲያውያን ፍርድ ቤት ይቀርባሉ ተብለው ነው ያለው። የሰላሙ ጉባኤ ሁኔታውን አውግዞ ጉዳዩን በትልቅ ደረጃ አይቶት የጠበቆች ማህበርን በመወከል በመከታተል ላይ ነው። የኢትዮጲያ ሕዝብ በዚህ ጉዳይ የተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ጠይቆ እምቢ ተብሏል።እኔ እስከመጣሁበት ጊዜ ድረስ በእስር ላይ ናቸው።

ላንዳፍታ፤- በመጨረሻ ሊያስተላልፉ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ።

ዶ/ር ታዬ፤- ትግሉ አሁን የሰላሙ ጉባኤ ብቻ የሚያመጣው አይደለም። ትግሉ ብዙ አቅጣጫ (Multi-Dimensional) ያለው ነው። በብዙ መንገድ የሚታይ ነው። ለሰብዓዊ መብት ከሚታገለው አንስቶ ለራሱ መብት እስከሚታገለው፤ ከግለሰብ ሄዶ በየቦታው ሁኔታዎችን ከሚያጋልጠው አንስቶ በሙያ ማህበራቸው ሙያቸው እንዲከበር እስከሚታገሉት፣ ከዚያም አልፎ በመሣሪያ ትግል ከሚያደርጉ ሁሉ ማለት ነው። እዚህ ላይ ጠንቀቅ ብላችሁ አዳምጡኝ ጦርነት አላወጅኩም። እነዚህ ሁሉ ኃይሎች ናቸው። ሁልጊዜ Vicious Circle ከሆነ፤ ባለሥልጣኖች ሁል ጊዜ ሥልጣን ላይ የሚወጡት በጉልበት የመሆኑ ባህል ካልቀረ አሁንም ሌላው የሚመጣው ኃይል በጉልበት ከገባ በጉልበት ነው የሚወጣው። ፕሬዚዳንት መለስ ስልጣን በያዙ በሦስተኛው ቀን ከምሁራን ጋር በቲቪ ቀርበው ነበር። አንዱ ጥያቄ ፕሮፌሰር መስፍን የጠየቁት "ማ ማንዴት ሰጥቷችሁ ነው? ይህን ሁሉ ውሳኔ የምትወስዱት?" የሚል ነበር። ፕሬዚዳንቱ መለስ ሲመልሱ "ለአፄ ምኒሊክ ማነው ማንዴት የሰጣቸው?" ለአፄ ኃይለ ሥላሤ፣ ለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ማነው ማንዴት የሰጣቸው? እኛም እንደዚያው ነው።" ይላሉ። የሚቀጥለው ጥያቄ ምን መሆን እንዳለበት ጠያቂዎች የረሱ መሰለኝ። "እናንተ ታዲያ ከነሱ የተለየ ዴሞክራቲክ የሚያሰኛችሁ ባህርይ ምኑ ነው?" የሚል ጥያቄ ቢከተል ኖሮ ምን መልስ ይሰጡ ነበር? ለእኔ አሹራንስ ምንድነው? የሚመጣው ኃይል ዴሞክራቲክ ሆኖ ሥልጣን ማስከበሩ፤ ስለዚህ መሠረቱ እዚያው የሚኖረው ሕዝብ በስርዓቱ ተደራጅቶ የዴሞክራቲክ ኃይል መሆን ነው። ሰዓቱም አሁን ነው። ትልቅ የፖለቲካ ፍጭቶች በሚካሄድበት ጊዜ፤ እኔ የምፈልገው በሰላም መንገድ የጨዋታው ሕግ ወጥቶ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበትና ከዚያን በኋላ ለኢትዮጲያ ሕዝብ ፕሮግራማቸውን አቅርበው በሚመቻቹበት ጊዜ የሚወዳደሩበት ሁኔታ ነው። ግን እዚያ የሚቀበለው ሕዝብ በሕግ በሕዝብ እጅ እስካልሆነ ድረስ አሁንም ከጦርነት አንድንም። ስለዚህ እነኚህ ኃይሎች በደንብ እንዲንቀሳቀሱ ትልቅ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ነው የምለው።

ላንዳፍታ፤- ዶ/ር ታዬ ለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ በአንባብያንና በዝግጅት ክፍላችን ስም በጣም እናመሰግናለን።

# ልብወለድ

## የዴብራ ጦስ

(በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብ ወለድ)

ከገረሱ

"የዴብራ ጦስ" በተሰኘው ርዕስ የተጻፈው ልብወለድ ረዥም ስለሆነ በተለያዩ ክፍሎች በተከታታይ ይወጣል።

### ክፍል ስድስት

የዛን ዕለት ካሣሁንና ፈጠነ የዴብራን ጉዳይ አንስተው በሚነጋገሩበት ወቅት ዴብራ ስልክ በመደወሏ ውይይቱ ተቋረጠ። ቢያንስ ለዚያን ዕለት። ዴብራ የደወለችው ካሣሁን መጥቶ እንዲወስዳት ስለነበር እሷን እንዳነጋግር ጣደፍ ጣደፍ ብሎ ፈጠነን ሊሸኝ ፈለገ። ፈጠነም የካሣሁን በዴብራ ላይ ያለው ስሜት ምን ያህል መጥቆ እንደሄደ ተረዳ። ተቆጥቶ ስሜቱን ለማቀዝቀዝ እንደማይችል ገባው። ዝም ብሎ እንዳይተወውም ጓደኛው ነው።

ለመሄድ ብድግ እያለ፤ "ካሣሁን እስቲ ዴብራን አስተዋውቀኝ?"አለው ፈጠነ።

ካሣሁን ያልጠበቀው ጥያቄ ነበር። ጥቂት አሰብ አደረገ።

"ምን ሊያደርግልህ?" አለው ካሣሁን።

"አይዞህ አልጠብስብህም" አለና ሣቅ አለ።

"ባክህ አትቀልድ፣ እኔ እንደሱ አላሰብኩም"

"እንግዲህ የምትወዳት ከሆነ ለውድ ጓደኛህ ማስተዋወቅ ሥርዓቱ ይመስለኛል።"

"እሱማ ነው" አለ ካሣሁን ግራ በተጋባ ሁኔታ፤

"ጓደኛ ካላት ደግሞ እኔ የምጠላ መሰለህ?" አለው ፈጠነ።

"እዬ ፈጠነ፤ መቼ አጣሁት፣ ባክህ አትቀልድ።"

"እንዴት መቀለድ?"

"የውጭ አገር ሴት መጥበስ ወንጀል ነው ከሚሉት አበሾች ወገን ነሃ!"

"እንደዚህ ስትል ታናድደኛለህ። ግልፁን ልንገርህና የውጭ ሴት መጥበስ ወንጀል ነው የሚል አበሻ የለም። ዋናው ነገር ፍቅርና መግባባት ነው። መግባባት ስልህ ደግሞ ይገባሃል፤"አለው ፈጠነ ወደ ፍሪጅ ሄዶ በብርጭቆው ጭማቂ እየቀዳ።

"እና አሁን አንተ ከዚህ አገር ያለች ቆንጆ ልጅ ብታገኝ ታገባለህ? ከልብህ ነው መመለስ ያለብህ፤"

"ከወደድኳት ከተግባባን ለምን አላገባትም። እዚህ ላይ መግባባት ስልህ አንድ ነገር ማወቅ አለብህ። የማገባትን ሴት የውጪም ትሁን የአገሬ ልጅ በመልኳ፣ በቁመና ወይም በወሲብ ስሜቷ ብቻ አይደለም ለዚህ ታላቅ ዓላማ የማጫት፤ በርግጥ እሱም ወሳኝ ነው። ቢሆንም ከአስተዳደጌ፣ ከባህሌ፣ ከእምነቴ በተለይም ከአመለካከቴ ጋር ተቃራኒ የሆነ ሁኔታ ካየሁባት በሌላው አካላዊ ገፅታዋ ብትማርከኝም ለጋብቻ አልመኛትም። የአገሬም ልጅ ብትሆን፤"

"አየህ ፈጠነ ራስህን በራስህ ስትቃረን። 'አልሸሹም ዞር አሉ፤' አሉ አባቶቻችን። ከባህሌ፣ ከአስተዳደጌ ስትል ለጋብቻ የምትመኛት ያው የአገሬን ልጅ ብቻ ነው አትለኝም ከዚህ ሁሉ፤" አለው ካሣሁን ። "እንደሱ ከተረዳኸው ምን ማድረግ እችላለሁ፤ የውጪ አገር ልጅ ከባህሌና ከአስተዳደጌ የራቀች ስለምትሆን በአመለካከት ለመግባባት ጊዜና ትልቅ መስዋዕትነት ይጠይቃል። እንግዲህ ይህን ለማሟላት የምትችል በአስተሳሰብም በባህልም በቅርቡ ተመሳሳይነት ያላትን ያገሬን ልጅ ማግባት ይቀለኛል። ይህ ማለት ደግሞ የውጪ ሴቶችን መኮነኔ አይደለም። ደግሞ ጋብቻ የሁለታችን የባልና የሚስቱ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን የሁለት ቤተሰቦች ማለትም የአንተና የልጅቷ ቤተሰቦችም ጭምር የሚዋሃዱበት ክስተት ነው። እስቲ ይታይህ እናትህ መጥተው ከልጃቸው ሚስት ጋር መዋሃድ ቀርቶ መግባባት መነጋገር ተስኖአቸው ግራ የተጋባ ሁኔታ ላይ ሲወድቁ፤"አለ ፈጠነ።

"ምን አድርግ ትለኛለህ፤ ይኸ እንኳ የስደት አገር ኑሮአችን ያመጣብን አንዱ ጣጣ መሆኑን አትዘንጋ። በዚህ ላይ ደግሞ የአገሬን ልጅ ማግባት ጠልቼ አይምሰልህ እንዲህ የምለው። ስናወራ የቆየሁትን ለምን ወደዚያ ትመልሰኛለህ። እዚህ ያሉትን የኛን ሴቶች ጠባይ እያወቅህ፤" ይለዋል ካሣሁን።

"ይህን የእኛን ሴቶች ጠባይ የምትለውን አቁም። የኛም ሆኑ የሌላው አገር ሴቶች አንድ ናቸው። ምናልባት በሰው አገር የስቃይ ኑሮ አንዳንዱ ነገር ግራ እያገባቸው ሁኔታቸው የተቀየረ ቢመስልህ ይህን ያህል ልታጋንነው አይገባም።" አለው ፈጠነ።

"ማጋነኔ አይደለም። ሞከርኩ፤ አልገባ አሉኝ። ሌላ አገኘሁ ተረዳችኝ፤ ታድያ ለምን በዚህ መልኩ አታየውም።"

ፈጠነ ጥቂት አሰብ አደረገ። የካሣሁን ችግር ቢገባውም በቀላሉ ሊቀበልለት አልፈለገም።

"እስቲ እንዲህ እናድርግ ከተስማማህ። ከልቤ ነው ይህን የምነግርህ አንተ ዴብራን አስተዋውቀኝ ጓደኛ እንዳላት ታስተዋውቀኝና እናውጣቸው። አብረን ማለቴ ነው። አንተ ያው ዴብራህን እኔም ጓደኛዋን።"

"ይህ ታዲያ ላለው ችግር መፍትሔ ይሆናል ብለህ ነው?"ይላል ካሣሁን ግራ በተጋባ ሁኔታ።

"ቆይ አትጣደፍ። መቼ ጨረስኩልህና። እኔም ደግሞ ከማውቃቸው የኛ አገር ልጆች አንተን አንዷን አስተዋውቄ አንተም እኔም እናውጣ። እንያቸውና እንፈትናቸው።"

ካሣሁን ይስቃል። "እነማንን ነው የእኛ ልጆች

ብለህ የምታስተዋውቀኝ? እስከዛሬ የት ነበርክ?"
"እስቲ እስከዛሬ የት ነበርክ የሚለውን ጥያቄ ወደዚያ ተወውና ከአሁኑ እንጀምር።" "እኮ እነማንን?"
"አንተ ምን ቸገረህ? እሺ በለኝና እናድርግ። ከዚያ በኋላ ምናልባት እኔም አንተም አንድ ቋንቋ ይኖረናል።"
"ቆይ፤ አንተ የዴብራን ጓደኛ ተዋውቀህ ትጠብሳለህ፤ እኔ ደግሞ የአንተን ጓደኛ ጓደኛ እጠብሳለሁ። "ከዚያስ"
"ከዚያማ በተቻለ መጠን ለሲኒማም፣ ለራትም ሆነ ለሌላ መዝናናት ፕሮግራም ስናወጣ እኔና አንተ አንድ ላይ እንሆናለን። ማለቴ ዛሬ አበሾቹን ካወጣን፣ ከአንድ ሁለት ቀን በኋላ ደግሞ እነዴብራን እናወጣለን። ለአንድ ሁለት ወር ከዚያ በኋላ ሁሉንም እንገመግማለን።" ይለዋል ፈጠነ።
"ዕብድ ነህ ወይስ ጤነኛ፤ ምንድነው ይኸ ሁሉ ጣጣ? " ይለዋል ካሣሁን የፈጠነን ሀሳብ ላለመቀበል እያቅማማ።
"ሐቁን ለመረዳት የምትችልበትን መንገድ ሊያሳዩህ ሲሉ አትሽሽ፤" ይላል ፈጠነ።
"ከሆነ ምንጨነቀኝ፤ በል ሰዓት አለፈብኝ እንሂድ፤ አንተ ልጁ ቀልደኛ ነህ።" ይለውና በዚሁ ተስማምተው ይለያያሉ።
ካሣሁን ጓደኛውን ፈጠነን ከጓደኛዋ ጋር እንድታስተዋውቅ ለዴብራ ይነግራታል። ደስ ይላታል። ካሣሁንን በበለጠ ለማጥመድ ጥሩ ዕድል እንደሚሰጣት አድርጉ ታያትና እሺ አለች። ፈጠነም ቀደም ሲል ቀርቧት የነበረችውን ሰናይትን ግንኙነቱን ጠበቅ አድርጎ ያወጣትና ጓደኛዋን ራሄልን ለካሣሁን ለማስተዋወቅ ያግባባታል። ካሣሁንና ፈጠነ ባደረጉት ስምምነት መሠረት መጀመሪያ እነ ሰናይትን ያወጣሉ። ዕለቱ ዓርብ ነበር። ካሣሁንና ፈጠነ መጀመሪያ ካሣሁን ቤት ይገናኙና የመጀመሪያውን እስትራቴጂ በመንደፍ በፈጠነ በኩል በተደረገው ቀጠሮ መሠረት ራት ይዘዋቸው ይወጣሉ። የሄዱት በካሣሁን መኪና ነበር። አዲስ የምትባል ግራንዳም መኪና ነበረች። የአበሻ ሴቶች ደህና መኪና ሲያዩ ልባቸው ብን ይላል ብሎ ካሣሁን አጥብቆ ስለሚያስብ ነው ፈጠነን ያግባባው።
ከሴቶቹ ጋር ለመገናኘት የተቃጠሩት አንድ እነ ሰናይት ቤት አካባቢ የሚገኝ ካፌ ነበር። ልክ በ5:00 P.M. ሰዓት። እነ ካሣሁን ካፌውን ሲገቡ ግድግዳው ላይ የተሰቀለው ሰዓት ለአምስት አስር ጉዳይ መሆኑን ያያሉ። መቀመጫ ፈልገው ቁጭ ይሉና ቡና ያዛሉ።
"ታዲያስ ይለዋል!" ፈጠነ ካሣሁንን፤ "ዋናው ነገር አለመቸኮል ነው፤ አትቸኩል፤"
"ግዴለህም ለሱ እንኳ ታውቀኛለህ፤" ይልና ሰዓቱን ቀና ብሎ ያያል። አራት ደቂቃ ጉዳይ። ፈጠነ በር በሩን ማየት መጀመሩን ሲያይ ትንሽ ፈገግ አለ። አምስት ሰዓት ሞላ፤ አምስት ከአስር፤ አምስት ከአስራ አምስት፤ ከሃያ፣
"መኪና ተበላሽቶባቸው ይሆን?" አለ ካሣሁን የፈጠነ ዓይን ከወደ በሩ መለስ ማለቱን ጠብቆ።ካሣሁን ይህን ያለው ለማፌዝ መሆኑን በመረዳቱ መልስ ሊሰጠው አልፈለገም፤ ገላመጠውና ዓይኑን ወደ በሩ መለስ አደረገ።
አምስት ሰዓት ተኩል፣ ከሰላሳ አምስት፤ ከአርባ፣
"የሚወዳትን ልጅ የሚጠብቅ ወጣት፤
መስሎ ይታየዋል ደቂቃው እንደ ሰዓት፣
ሰዓቱም እንደቀን ቀኑም እንደ ሳምንት፤" ብሎ ካሣሁን የጀመረውን ግጥም ሳይጨርስ፤
"መጣች!" ይላል ፈጠነ መለስ ብሎ። ሰናይት ብቻዋን ነበረች።
በሩ ላይ ደርሳ ቀና ቀና እያለች ፈለገችና እነ ፈጠነ ያሉበትን ቦታ እንዳየች ወደነሱ ትመጣለች። እነ ፈጠነ ተነስተው ይቀበሏታል።
"ወይኔ! ራሔል አልመጣችም፤ የቀጠረችኝ ቦታ ዘገየሁባትና ነው መሰለኝ አጣሁዋት፤ እዚህ የመጣች መስሎኝ ነበር።" ትላለች ለመቀመጥ ኮቷን እያወጣች።
"እዚህ አልመጣችም" ይላል ፈጠነ፤ እንደገና መለስ ብሎ ወደ በሩ ያያል፣
"ዝርክርኮች፣ መቼም የማይሟላላችሁ? አይ የአበሻ ሴት፤" ይላል ካሣሁን በሆዱ።
"ካሣሁን ጋር ትተዋወቃላችሁ?" ይላል ፈጠነ ለካሣሁን በሆዱ ተንኮል ለማሰብ ጊዜ ላለመስጠት።
"በዓይን! ሰላም፤ ሰናይት እባላለሁ።" ትላለች ፈገግ ብላ።
"ካሣሁን!" ይልና እጁን ይዘረጋላታል።
"ይቅርታ ጥቂት አስጠብቅኋችሁ መሰለኝ?" ትላለች ካሣሁንን እያየች።
"አይ ምንም ያህል አልጠበቅንም" ይላል ካሣሁን ምንተፍረቱን። "አርባምስት ደቂቃ ምናላት" ይላል በሆዱ።

ካሣሁን በሆዱ ምን እንደሚያስብ ፈጠነ ያውቀዋል። ቁጭ ብለው ሳለ በዓይኑ የካሣሁንን ዓይን የሚሸሸውም ለዚሁ ነበር።በር በሩን ሲያይ ቆይቶ ድንገት "ያቻት ራሔል!" አለና ቁና ተነፈሰ።

ራሔል በቀጥታ ወደ መቀመጫቸው ትመጣለች። ተነስተው ይቀበሏታል። ካሣሁንንም ያስተዋውቁታል። እሷም ከሰናይት ጎን ትቀመጣለች።
"ይቅርታ ዘገየሁባችሁ መሰለኝ፤" ትላለች ራሔል።
"አይ ምንም አልዘገየሽም፤" ይላል ፈጠነ የካሣሁን ዓይን እየሸሸ።
"ኸረ ምን በወጣሽ!' ይላል ካሣሁን በሆዱ። የድምጿን ማማርና የቁመናዋን ሸንቃጣነት ግን በሆዱ ሳያደንቅላት አልቀረም።
ትንሽ ነፍሱ መለስ ያለችለት ፈጠነ ዘና አንደማለት ይልና ራሔል የምትፈልገውን እንድታዝ ይጋብዛታል። "ራት ከመብላቴ በፊት እንኳ ምንም አልፈልግም።" ትለዋለች።

"እንግዲያውስ እራታችንን የምንበላበት ቦታ እንሂዳ!" ይላል ፈጠነ። እሱም ቢሆን ለሰናይት ገና የቅርብ ጊዜ ጓደኛ በመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት አልዘነጋም፤ ምንም ዋናው ዓላማ ካሣሁንን ከአበሻ ሴት አገናኝቶ ከዴብራ ለማላቀቅ ቢሆንም።የራት ቦታው ምርጫ ዕድል ለሴቶቹ ተሰጠና እነሱ ወደ መረጡበት ምግብ ቤት ጉዞ ሆነ። ሁሉም በመኪናቸው ተከታትለው እነ ሰናይት መንደር ደርሰው የነሰናይትን መኪና ትተው በካሣሁን ግራንድ አም ጉዞ ሆነ።

"ቆንጆ መኪና አለህ" አለችው ሰናይት ከኋላ መቀመጫ። ሰናይትና ራሔል ከኋላ፣ ፈጠነ ፊት ከካሣሁን ጋር ነበር።

"አመሰግናለሁ።" አለና ካሣሁን በመስታወቱ ወደኋላ መቀመጫ ሲያይ ራሔል ጋር ዓይን ለዓይን ተጋጩ። እፍር እንደ ማለት አለች። "ቆንጆስ ቆንጆ ናት" አለ በሆዱ።

ሰናይትና ራሔል ተጠጋግተው ይንሾካሾካሉ። ፊት ላሉት አይሰማም ነበር።

"ይኸው እንግዲህ! ገና ከመቼው ተገናኝተው ምስጢራቸውን እንደጀመሩ" አለ ካሣሁን በሆዱ። ምግብ ቤቱ ደረሱና መኪናቸውን አቁመው ተያይዘው ገቡ። መቀመጫም አገኙና ተቀመጡ። ፈጠነ ሁን ብሎ ራሔልና ሰናይት ተራርቀው የሚቀመጡበትን ሁኔታ ቀይሶ ካሳሁን ከራሔል ጎን፣ እሱ ደግሞ ከሰናይት ጎን ሆኑ። ራቱም ታዞ እስኪመጣ ጨዋታ ተጀመረ። ፈጠነ ነበር የጀመረው።

"ካሣሁን ውድ ጓደኛዬ መሆኑን ነግሬሻለሁ አይደል ሰኑ?" ይላል ፈጠነ ሰናይትን በፈገግታ እያየ።

"አዎን! እዚህ አገር ከመጣህ ቆይተሃል?" ትለዋለች ሰናይት ካሣሁንን።

"መቆየት ስትይ?" ይላታል ካሣሁን። በሆዱ "መጣ እንግዲህ ጭቃ ጅራፉ" ይላል።

"ማለቴ ስንት ዓመት ሆነህ?"

"አንድ ስድስት ዓመት ይሆነኛል።" እሱም ሊጠይቃት ፈለገና ተወው።

"ገና ቅርብ ጊዜ ነዋ የመጣኸው፤ እኛ ትንሽ ከራርመናል" ትለዋለች ትንሽ በኩራት።

ፈጠነ አባባሏ ደስ ስላላለው አርዕስቱን ለመቀየር ሊሞክር ሲል፤

"ከአዲስ አበባ ነህ?" አለችው ሰናይት መልሳ።

"አይደለም፤" አላት፣ ከየት እንደመጣ ሊገልጽ አልፈለገም። ቀደም ብሎ የደረሰበትን ሁኔታ አስታወሰ። ጨዋታው ቀጠለ።

የራሔል ዝምታ ግን ልብ ልቡን ይበላው ጀመር። "ምን አባቷ ይዘጋታል?" አለ በሆዱ። ሰናይትን ግን አልወደዳትም።

"እንደሷ ባልሆንሽ?" አለ በሆዱ። ዝምታዋ ግን የበለጠ እንዲያስባት አደረገው።

በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል)

ADVERTISE ON LANDAFTA

A MAGAZINE

WHERE MOST ETHIOPIANS GET INFORMATION

በላንዳፍታ ላይ ድርጅቶን አስተዋውቁ

ጊፍቲ ታማክሎ
Gifty Tamakloe
Sales Associate
Pager: (404)871-6209
FAX: (404)288-3360
Home: (404) 414-1486

ቤት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ

HOMES TO PLEASE YOUR NEED

PROPERTY SYSTEMS REAL ESTATE

4319 Covington Highway
Suite 312
Decatur, GA 30035
(404)288-3366

EAI ADVERTISING AGENCY

EAI ADVERTISING AGENCY
P.O.Box 6322
Minneapolis, MN 55406
Tel. (612) 339 - 1777
Pager # (612) 622 - 2675

The Information Line is open 24 hours to inform you *THE HAPPENINGS* within the Abesha Community. The number is (612)339-1777

For *Outstanding Wedding Invitation Cards*, business cards, personal cards, flyers, restaurant menus, resumes, rubber stamps, or Direct mailing call *EAI Adevertising Agency at* (612)622-2675 or (612)339-1777 and leave a message after the tone.

ሰላም

**Thank You.**

# ኑሮ በአሜሪካ




## የአትላንታው ከንቲባ ቢል ካምብል በኢትዮጵያ ሰላምና ዴሞክራሲ መስፈን ምኞታቸውን የሚገልጽ የፕሌጅ ሰርተፊኬት ለአትላንታ ኢትዮጵያውያን አበረከቱ።

February 7 1993 በአትላንታ ከተማ በምትገኘው የኢትዮጵያ ቅድስት ማርያም ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፊትለፊት በሚገኘው የካፒቶል አደባባይ ላይ በተደረገው የኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የአትላንታው ከንቲባ ቢል ካምብል በአትላንታ ከተማ ሕዝብ ስም "በኢትዮጵያ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የበኩላችንን ለማድረግ ቃል እንገባለን፤" የሚል የቃል ኪዳን ምስክር ወረቀት ሰጡ።ቢል ካምብልን በመወከል በቦታው ተገኝተው የምስክር ወረቀቱን የሰጡት ሚ/ር ማይክል ላንግፎርድ ሲሆኑ በአሰጣጡ ሥነስርዓት ላይ በተናገሩት ንግግር " ለዚህ ታላቅ ዓላማ የተከበሩ ቢል ካምብልን በመወከል በዚህ ቦታ ተገኝቼ የምስክር ወረቀቱን ስሰጥ ትልቅ ክብርና ኩራት ይሰማኛል። እናንተ መሆን ያለባችሁን መሆን ሳትችሉ እኛም ነን የምንለውን መሆን አንችልም፤ ስለዚህም ትግላችሁ ትግላችን መሆኑን እንረዳለን፤" ብለዋል።



ቢል ካምብል ከኢትዮጵያውያን ጋር

## በአትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበርን ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው።

የአትላንታ ኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ ማህበርን ለማጠናከር በየአቅጣጫው የሚደረገው ርብርብ ጥሩ ውጤት እያመጣ መሆኑን የኮሚኒቲው ማህበር የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባልና ለዚሁ ማጠናከር ተግባር የተቋቋመው ግብረ ኃይል አስተባባሪ አቶ ማንደፍሮ ንጉሴ ገልጸዋል። የኮሚኒቲ ማህበርን ንድፈ ሀሳብና ዓላማውን የሚያስረዳ ጽሑፍ የያዘ ወረቀት ተበትኖ ብዙ ኢትዮጵያውያኖች እንዲያገኙትና ዓላማውን እንዲረዱ የተደረገ ሲሆን በየአቅጣጫው የተላከውን የአባልነት ቅጽ በመሙላት ከተጠበቀው በላይ ብዙ ኢትዮጵያውያን አባል ለመሆን ፈቃደኛ ለመሆን መመዝገባቸውን ለማወቅ ተችሏል። ቀደም ሲል የተበተነው መጠይቅ ብዙዎች ሞልተው በመላካቸውና ለአባልነት ብዙ ፈቃደኞች መገኘታቸው በጣም የሚያበረታታን ነው ሲሉ አቶ ማንደፍሮ ገልጸዋል።በሌሎች እስቴቶች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ማህበራት የድጋፍና የማበረታቻ መልዕክቶችን በመላክ ላይ መሆናቸውም ታውቋል። ■



አቶ ማንደፍሮ ንጉሴ

# ዕጣዬ

(ከአብረኸት)

. . . ከአለፈው የቀጠለ

## ክፍል ሁለት

ስለ ዕድገት በኅብረት ዘመቻ ብዙ ባላወራ ይሻለኛል። ዘመቻ ላይ የተሳተፋችሁ ታውቁታላችሁ። በመጀመሪያ አካባቢ በመካከላችን ማለትም በዘማቾች መሐል አንዳንድ አለመግባባቶች ቢፈጠሩ ወይ ምን አልባት ከአዲስ አበባ የመጣና ከዚያው ከክፍለ ሐገሩ የዘመቱ በሚል አለያም በአንዳንድ የአመለካከት ልዩነት እንጂ በዘር ወይም በጎሳ አልነበረም። ከአዲስ አበባ የሄደው ሁሉም ዘር ነው። ከዚያም የዘመቱት ከሁሉም ዘር ናቸው። የመሬት አዋጅ ከታወጀ በኋላ ይህ ሁሉ ያለመግባባት ጠፍቶ ገበሬዎችን እማደራጀቱ ተግባር ላይ ተፍ ተፍ ማለት ጀመርን። ትዝ ይለኛል። "እንሱ እንደሻማ እየተቀጣጠሉ . . ." የሚለውን የደርግ መግለጫ ደብዳቤ አዝማቾችን ያነበበልን ዕለት ማታ ብዙዎቻችን በመኮብለሉ ተስማማንና ኮበለልን። ጓደኛዬ አምሳለ የነበረችበትም ጣቢያ ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጠረና ከሷ ጋር ሻሸመኔ ተገናኝተን ወደ አዲስ አበባችን ተመለስን። አዲስ አበባ ስንገባ ደግሞ የኮበለሉ ዘማቾች እየተባልን በየቦታው መንገላታት ጀመርን። ለስቃይ ይሆን የተፈጠርኩት ያልኩበትን ምክንያት የምትረዱልኝ ከእንግዲህ በኋላ በምነግራችሁ ታሪኬ ይሆናል።

ደርግ በወቅቱ በወሰዳቸው እርምጃዎች አባቴ ትንሽ በስጨት ቢልም እንደአምሳለ አባት አላረረም። አባቴ አንድ አነስተኛ የሚከራይ ቤት ነበረው፣ እሱ ተወሰደበት። በአብዛኛው የሚተዳደረው በንግድ ሥራ ስለሆነ እሱ ብዙም እልተዳም። እንዲያውም ንግዱ ጥሩ ሆነለት ብል አልሳሳትም። የአምሳለ አባት ግን ገጠር የነበራቸው የቡናና የእህል መሬት በየጊዜው ደብረማርቆስና እዚህም አዲስ አበባ ያሰሩዋቸው የኪራይ ቤቶች ሁሉ በትርፍነት ተወሰደባቸው። አምሳለ ስለተወሰደባቸው ንብረት ምንም ሳይሰማት ሲወጡ ሲገቡ "እህ" ማለታቸው በጣም አሳሰባት። በሽታ ላይ ይወድቃሉ ብላ እንጂ ንብረቱ ስለተወሰደባቸው አልነበረም። የእኔ ቤተሰብ ምንም ጭንቅ ውስጥ አልገባም። ትንሽ ቤት በመወሰዱ አባቴ "የራሱ ጉዳይ" ምን አጥቼ በማለት ተወው። ትንሽ የሚከነክነው የወንድሜ መጥፋትና የኤርትራ ግንባር መግባቱ ነበር። አዲስ አበባ በተለይ በወጣቱ አካባቢ ለየት ያለ ሁኔታ ይፈጠር ጀመር። ከዘመቻ የመጣው ወጣት በኢህአፓ መደራጀት ሲጀምር በመጀመሪያ አምሳለ በጥናት ክበብ ተያዘችና ኋላ አምሳለ እኔን ጠየቀችኝ። "ባክሽ ምን ያደርጋል ብለሽ ነው?" ነበር መልሴ።

"አየሽ ደርግ ራሱን ጊዜያዊ ብሎ ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ ሊመቻች ነው። ለሕዝብ አይሰጥም። በዚህ ላይ ወታደራዊ ነው፣..." ብቻ ምናለፋችሁ ትንትን አድርጋ ስትናገር ድሮ የማውቃት አምሳለ አልመስል አለችኝ።

"ከየት አመጣሽው ይህን ሁሉ አነጋገር" አልኳት እየሣቅሁ። ሌላ ሆና ነበር። ለማንኛውም እንደሷ እንኳ ጠንካራ ባይሆንም ወረቀቶችን ተሰብስቦ በማንበብና በመወያየት ላይ መሳተፍ ጀመርኩ። ይህ ሁሉ ሲሆን አብረን አንድ ላይ ሆነን የምንወያየው ከተለያየ ጎሣም ሆነ ዘር የመጣን ነን። የነበረው መግባባት፣ ፍቅር፣ መደጋገፍ ሌላ ነው።

አለ አለና የቀይ ሽብር መጣ፤ በመጀመርያ አምሳለ ተይዛ ታሰረች። ቀጥሎ እኔን አሰሩኝ። አንድ ቀበሌ። አምሳለ እልህዋ፣ ስድቧ ሌላ ነበር። ብዙ ጊዜ ገረፉት። በመጨረሻ አንድ ምሽት ወሰዱዋት፣ አልተመለሰችም። እኔ በመጀመርያ በኢህአፓነት ተመረመርኩ፣ ተገረፍኩ። ምንም ሲያጡ ጊዜ ተገንጣይ ነሽ አሉኝ። አለመሆኔንና እኔ በኤርትራ መገንጠል እንደማላምን ለማስረዳት ብሞክር የሚሰማኝ አጣሁ። "ትግርኛ መናገሬ ብቻ ተገንጣይ ሊያሰኘኝ አይችልም፣" ብዬ ድርቅ ብዬ ተከራከርኩ።

የአምሳለን መገደል አባቴ እንደሰማ ወዲህ ወዲያ ተሯሩጦ ብዙ ብር ጉቦ ሰጥቶ እኔን አዳነኝ። የአምሳልዬ አባት ግን ቢፈልጉም አይችሉም ነበር። አቅሙ ሞቶአል። እኔም ከእስር ቤት ስወጣ ሁሉ ነገር አስጠላኝ። ት/ቤትም ተመልሶ መግባት አልሆን አለኝ። አምሳለ ጋር እማር የነበረበት ት/ቤት እንዴት ልግባ? እሷ የለች? ዘምዘም ዘመቻ ከወጣች በኋላ ብዙ አልተገናኘንም። በተለይ የአምሳለ መሞት የማይረሳ የልብ ውስጥ ቁስልና ቂም ፈጠረብኝ። እልኸኛ፣ ተነጫናጭ ሆንኩ። አባቴ ጉቦ ከፍሎ ያስወጣኝ መሆኑን የሰሙ የሠፈሬ ወጣቶች አፍ ገባሁ። አባቷ አለው፤ ገንዘብ ከፍሎ ያወጣታል ብለው የገመቱ ሌሎች ቀበሌዎች ደግሞ ሌላ ጥቆማ መጥቷል፣ በተገንጣይነት ትፈለጋለች፣ ወንድሟ የት እንደገባ እናውቅም፣ ወዘተ እያሉ ማስወራት መጀመራቸው ጆሮዬ ጥልቅ አለ። አባቴ አሳብ ገባውና ኤርትራን ከለቀቅን ብዙ ጊዜ ቢሆንም ራቅ ያለ ዘመድ ፈልጎ ወደዚያ ሊልከኝ እንዳሰበ አወቅሁ። አስመራ መሄዱን በፍፁም የማላደርገው ነገር መሆኑን በኔ በኩል እርግጠኛ ነበርኩ። እዚህ እያለሁ የምፋጠጠው አንድ ጠላት ነው፣ ደርግን። አስመራ ብሄድ ደርግም አለ፣ ደግሞ ግንባር ግቢ የሚሉ ኃይሎች አሉ፣ ሁለት አጥፊ ነገሮች፤ ብዬ አሰብኩ።

ይህ በዚህ እንዳለ አባቴ እኔን አስመራ ለመላክ መወሰኑን ስሰማ ከቤት ጠፍቼ ፒያሳ ገባሁ። አንድ ድሮ የማውቃት የት/ቤት ልጅ ፒያሳ አካባቢ ፔሌ ቡና ቤት የሚባል እየሠራች ስለምትኖር ቀጥታ እሷ ጋ ሄድኩ። ደስ ብሏት፣ ጓደኛ አገኘሁ ብላ ተቀበለችኝ። ከቤት ትንሽ ያምታታሁትን ገንዘብ ከፍዬ አልቤርጎ ተከራይቼ ተደበቅሁ። እችው ልጅ የሠፈረችበት ሆቴል ነበር የገባሁት። ለአንድ ሁለት ሳምንት ተደበቅሁ፣ ወላጆቼ ይከታተሉኝ ይሆን በማለት። ከዚያ በኋላ እኔም የፔሌ ቡና ቤትን "ግሪን ፋየር" (የተቀላቀለ ጂን) ገባሁበት።

ግማሽ ቀን ተኝቶ መዋል፣ ከሰዓት ሲኒማ መግባት፣ ማታ ልብስ ለባብሶ ፔሌ ቡና ቤት መሄድ፣ "ግሪን ፋየር" መስተናገድ፤ ለካራም ማስተናገድ "ቢዝነስ ማካሄድ"...። ይህ ኑሮ ተባለና ተያዘ። ቀን ተኝቶ መዋል፣ ከሰዓት ሲኒማ መግባት፣ ማታ መጠጣት...። በቃ ምናለፋችሁ! መንፈሴን እየረበሸ የሚያስቸግረውን ሁኔታ ሁሉ መርሻ ከዚህ የተሻለ ዘዴ ምን ሊሆን? በዚህ ላይ በየዕለቱ በቀይ ሽብር እየተመቱ በየመንገዱ የሚጣሉ ወጣቶች ቁጥር ፊት እኔ እስር ቤት ከነበርኩበት ትንሽ አነስ ቢልም የቀጠለ በመሆኑ ያንን ጠዋት ተነስቶ ላለማየት በመጠጥ አዕምሮን አበልዞ መተኛት ምን "መታደል" መሰላችሁ። በዚህ ላይ ደግሞ ማታ በሞቅታ መንፈስ የሚታየውስ ጉረምሳ እንዲያውም ገንዘብ ከፍሎኝ አብሮኝ አድሮ፣ ባላውቅም እቅፉ ውስጥ አግብቶኝ ስተኛ ከዚህ ሁሉ ሽብር የሚከላከልልኝ መከታ ያገኘሁ የሚመስለኝም ጊዜ ነበር። አንድ መከታ ብቻ መሰላችሁ፣ ብዙ፣ በየቀኑ የሚለዋወጡ።

ፒያሳን የምታውቁ ታውቁታላችሁ። ከፍተኛ 2 ቀበሌ 12 ከድሮ እቴጌ ሆቴል (የአሁኑ አውራሪስ ሆቴል) አካባቢ ያሉትን ቡና ቤቶች፤ ከቀበሌ ጽህፈት ቤት ግራና ቀኝ የነበሩት የትግራይ ቡና ቤትና የካሣ ቡና ቤት፣ ፊት ለፊት ያሉት ሁለት ሕንፃዎች በመደዳ አስራ ሁለት ቡና ቤቶች፣ አብዛኞቹ (ሁሉም ባልል እንኳ) ባለቤቶቻቸው ከኤርትራና ከትግራይ የመጡ በመሆናቸው አካባቢው የትግሬ አካባቢ ይባል ነበር። መንገዱ "ባቢሎን" ይባል ነበር። አስመራ ያለ መንገድ ለማስታወስ። የቀበሌውም ተመራጮችና አብዮት ጠባቂዎች እንዲሁም አብዛኞቹ ትግሬዎች ናቸውና እኔ በዚያ አካባቢ ብያዝም በተገንጣይነት ሊከሱኝ እንደማይችሉ እረዳ ነበር። ከሁሉ የሚገርመው ፒያሳ አካባቢ ከጊዮርጊስ ደሀብ ቡና ቤት ጀምሮ ያሉት ትልልቅ የንግድ ቤቶች 90% ከኤርትራም ይሁን ከትግራይ የመጡ ትግርኛ ተናጋሪ ሰዎች ባለቤትነት ያለ መሆኑ ነው። የገብረትንሣይ ኬክ ቤት፣ የአዳም፣ የኮንትኔንታል፣ የካሣ፣ የትግራይ፣ ወዘተ ቡናቤቶች የቱባ ቱባ ትግሬዎች ንብረት ነው። እና ይህም ሆኖ ታድያ በአካባቢው ሲወራ የምሰማው "ትግሬዎች ተበደልን፣ ተጨቆን" የሚለው አነጋገር አልገባ ይለኝ ነበር።

ምንም እኔ ትግርኛ ተናጋሪ ብሆንና ዘመዶቼ ኤርትራዊ ቢሆኑም በዓይኔ ከማየውና ከምረዳው ውጭ በቃል የሚነግሩኝንና የሚሰበክልኝን ለመስማትና ለመቀበል ሕሊናዬ አልተቀበለውም። ይፋ አይውጣ እንጅ በየቤቱ አማራና "ጋላን" መኰነንና፣ እኛ የሰለጠን፣ ለፈረንጅ የምንቀርብ መሆናችን፣ በአንፃሩ ደግሞ አማራንና ጋላን "አድጊ" አድርገን እንድንወስድ መቀስቀሳችን ይገርመኛል። እና እኔ የማውቀው ያየሁት በዚህ በፒያሳ አካባቢ ያለው ሁኔታና ከሌሎች የኔ ብጤዎች የምሰማው አልጣጣም ይለኛል። አማራ ጨቋኝ "አድጊ" ሆኖ እኛ ተጨቋኝ "ሥልጡኖች" መሆናችን አልታይ አለኝ። በዚህ ላይ መጠቃቀም፤ መደጋገፍ በኔ ቢጤዎቼ ሲያይል ነው የሚታየው።

አንድ ጊዜ የሆነውን ላጫውታችሁ። የፔሌ ቡና ቤትም ሕይወትም በዚያው አጫውታችዋለሁ። ከባለቤቷ ጭምር ሁላችንም ሴቶች ነን። በጣም ብዙ ወጣት ሴቶች ግማሾቻችን ከቤተሰብ ሸሽት፣ ግማሾቻችን ከምንኖርበት ቀበሌ ሸሽት ነው እዚህ የተደበቅነው። እንደሌላው ቡና ቤት መደበኛ ሴተኛ አዳሪ አድርገን አይደለም ራሳችንን የምናየው። አለ አይደለም፣ ባለቤቷ ደሞዝ አትከፍለንም። እኛ ለምንኖርበት ቤርጐ ክራይ፣ ለምግባችን፣ ለልብሳችን፣ ለሲኒማችንና በአጠቃላይ ለመዝናኛችን የሚሆን ገንዘብ ይሰጡናል የምንላቸውን ወንዶችን የምናገኝበት ቦታ ነው። እና ታድያ አንዳንዴ ብቻችንን፣ አንዳንዴ ደግሞ ሁለት ሆነን ወጠርጠር ያለ ልብስ ለብሰን ባታችንን እያሳየን በጐዳናዎች ላይ ተጉዘን የተመለከቱንን ወንዶች አስከትለን ፔሌ እንገባለን። ታድያ ከመደበኛ ሴት አዳሪ አያስቆጥረንም የምንለው ለዚህ ነው። ይህ በዚህ እንዳለ በተለይ እንደዚያ ለብሰን በመንገድ ላይ የሚያዩን አብዮት ጠባቂዎች ያስቆሙናል፣ ያባርሩናል ሲያሰኛቸውም ያስሩናል። ሲያስሩን የፖለቲካ ምክንያት ኖሮ ሳይሆን "ጆሊ ጃኪዝም" አስፋፊዎች በሚል ስለሆነ ያው በማግባቢያ ቋንቋችን አግባብተን፣ አየል ካለብንም ገንዘብ ሳይሆን የሚፈልገውን ሰጥተን እንላቀቃለን። እና አንድ ጊዜ ከዚቹ ጓደኛዬ ጋር ወተርጠር ያለ ልብሳችንን ለብሰን ስንዘዋወር ሁለት የአብዮት ጥበቃ ጓዶች አስቆሙን።

የማግባቢያ ቋንቋችንን ብንጀምርም አልገባ አላቸው። አንደኛው በትግርኛ አነጋገረኝ። እኔም መለስኩለት። "ከዚች 'አድጊ' ጋር ምን ታደርጊያለሽ?" አለኝ። የምሰጠው መልስ አጣሁና "ጓደኛዬ ናት" አልኩኝ። "አንቺ አዲስ ነሽ፣ እሷ የቆየች ናት፤ እሷ ናት ለዚህ ኑሮ ያበቃችሽ፤ " አለኝ። "ሽረ አይደለም" አልኩት። "ነው" ብሎ እሷን ማፋጠጥ ጀመረ። በትህትና ልታናግረው ብትሞክርም እንዴት መልስ ትሰጪኛለሽ ብሎ በጥፊ አጮላትና እኔን ትተው እሷን ይዘዋት ሄዱ፤ ሊያስሯት። እልህ ያዘኝና መልስ ልሰጠው ሞከርኩ። ሂጂ ከዚህ ብሎ አባረረኝ። እሷን ይዘው ወደቀበሌ ሲሄዱ ልከተላቸው ፈራሁ። ቢያንስ ያከረሟት እንደሆነ ስንቅ የሚሰጣት የለም ብዬ ወደ ፔሌዬ ተመለስኩ። ሌላ ጊዜ ሰው ሲጋብዘኝ ብቻ የምጠጣው በንዴት በራሴ ገንዘብ "ግሪን ፋየር" ገዛሁና በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረግሁ። ትግርኛ ቋንቋ ባለመናገሯ እንደታሠረች ለመረዳት አላቃተኝም።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ጉስቁል ብላ መጣች።

"ለቀቁሽ እንዴ?" አልኳት።

ዓይኗ እንባ ሞልቶት "እዎ!" አለችኝ።

"ምን ብለውሽ?"አልኳት በጉጉት።

"ያው ነዋ!" አለችኝ እንባ እየተናነቃት

"የፈለጉትን መች አጣሽው፤"

"የትኛው ነው የፈለገው?"

"ሁለቱም፤" አለችኝ እንባ እየተናነቃት፤

"ታድያ አደረግሽ፤"

"ምን ምርጫ ነበረኝ" ብላ ስቅስቅ አለች።

ሌላ ጊዜ እንዲሁ ከኮንቲኔኔታል ቡና ቤት አካባቢ ደግሞ ስንዘዋወር ቀጥሎ ያለው ቀበሌ 13 አብዮት ጠባቂዎች ያዙን። "እሺሽ ታጨሳላችሁ፤" ነው የእነኚህ ክስ ደግሞ። ይዘውን ወደቀበሌያቸው ወሰዱን። ይህ ደግሞ የትግሬዎች ቀበሌ አይደለም። እንዲያውም እኛ ያለንበትን የቀበሌ 12 ቀበሌ የተገንጣይ ቀበሌ የሚሉ ነበሩ። ከአነጋገሬ ትግርኛ ተናጋሪ መሆኔን አወቁ። "አንቺ እንዲያውም የተገንጣዮች ሰላይ ሳትሆኚ አትቀሪም፤" አሉኝ። "ኸረ እኔ አይደለሁም" ከማለት በቀር የምለው ጠፋኝ። ሁለታችንንም አሰሩን። ወደ ለሊት ገደማ አንደኛው አብዮት ጠባቂ እታሰርንበት ክፍል መጣና "ለምርመራ ትፈለጊያለሽ" ብሎ ጠራኝ። በዚያ ወቅት ቀይ ሽብር ትንሽ ቀዝቀዝ ብሎ ስለነበር "የምን ምርመራ" ብዬ ተከትዬ ከመሄድ በስተቀር ምርጫ አልነበረኝም። አካባቢ ጭር ያለ ነበር። አንድ ባዶ ክፍል ውስጥ ከተተኝ። ምንም የለም።

"አንቺ ተገንጣይ ስለሆንሽ ለከፍተኛ ምርመራ ወደከፍተኛ ቦታ ልንልክልሽ ነው፤" አለኝ።

ደነገጥኩ እኔ ድጋሚ መታሠር አልፈልግም። ስለዚህ ያለኝ ምርጫ መለማመጥ ብቻ ነበር።

ጠጋ አልኩና "እባክህ፣ እባክህ እኔ ተገንጣይ አይደለሁም፣ እና እርዳኝ፤" አልኩት።

"ብረዳሽ ምን ታደርጊልኛለሽ፤" ነበር ጥያቄው፤

"የፈለግኸውን!" ብዬ ፈገግ አልኩ። ገባኝ።

የዚህኛው የሚገርመው የፈለገው ያንን ብቻ ሳይሆን ገንዘብም ጭምር ነበር። ፈታተሸኝና ኪሴ የነበረውን ሰላሣ ብር ወሰደና ወዲያው የለበስኩትን ሱሬዬን ፈትቶ ወደታች አወረደው። የፈለገውንም ፈፀመ። እኔም ጓደኛዬም በጠዋት ተፈታን።

በአጋጣሚ ያስታወስኳቸውን ሁለት ገጠመኞቼን ገለጽኩ እንጂ ሕይወታችን፣ ኑሮአችን ሁሌ ከዚህ የተለየ አልነበረም።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ ነው ሰይፉን ያገኘሁት። ሰይፉ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ሚና የተጫወተ የምወደው ጓደኛዬ ስለሆነ እንዴት እንዳገኘሁት በሰፊው ላጫውታችሁ። አንድ ምሽት ከዚቹ ጓደኛዬ ጋር ፔሌ ቡና ቤት ቁጭ ብለን የባጡን የቆጡን እያወራን ስንጫወት ከእኛ አለፍ ብሎ ከአለው ጠረጴዛ ላይ ብቻውን ቁጭ ብሎ ቢራ የሚጠጣ አንድ ሰው አየሁ። ሳየው ወደእኛ አካባቢ ያይ ነበርና እኔም አየት አደረግሁት። ሁሌም የምናደርገው የመቅረቢያችን ዘዴ ነውና ዓይኔን አቁለጭልጩ ፈገግታ ሰጠሁት። እሱም ፈገግ ብሎ አንገቱን ሰበር አደረገ። ከዚያም ቀና አለና በዓይኑ ወደሱ መቀመጫ ጋበዘኝ። ተነስቼ ሄድኩኝና ቁጭ አልኩ።

"ታዲያስ" አለኝ።

"አለን እባክህ" አልኩት።

"ምን ልጋብዝሽ?" አለኝ።

ወትሮ ወደድ ያለ መጠጥ ነበር የምጋበዘው፤ "ለስላሳ?" አለኝና "ምነው መድኀኒት እየወሰድሽ ነው እንዴ?" አለኝ።

"አይ! አይደለም፤ ባክህ ዛሬ መጠጥ አላሰኘኝም" አልኩት። ውሸቴን ነበር። አሁንማ ሱስ ሆኖብኝ መጠጥ የማያሰኘኝ ምሽት አልነበረም። ጓደኛዬን ጠራሁዋትና ያዘዝኩትን ለስላሳ አመጣችልኝ። ገረማትና ገላምጣኝ ሄዳ ቦታዋ ቁጭ አለች።

"ሰይፉ" እባላለሁ አለኝ ረጋ ባለ አነጋገር።

ያልተለመደ ነገር ነበር። ስሙን ነግሮኝ በሥነስርዓት የሚተዋወቀኝ ወንድ የማውቀው ድሮ ፔሌ አካባቢ ሳልመጣ ነበር።

"ኤልሣ" አልኩት። ኤልሣ የፔሌ አካባቢ ስሜ ነው። አብረኸት የሚለው ስም ለቢያሳ የማይስማማ ደባሪ ስም ስለነበር ከጓደኞቼ ጋር ተመካክሬ ያወጣሁት ስም ነው። በዚህ አካባቢ የምታወቀው በኤልሣ እንጂ በአብረኸት አልነበረም።

ረጋ ባለ መንፈስ ኰስተር ያለ ጨዋታ ጀመርን። እንደሌሎቹ ወንዶች "ታድያ ዛሬ ይቻላል ወይ? ለአሁን ወይም ለአዳር" አላለኝም። ስለምንሰማው ሙዚቃ፣ ስላየነው ፊልም ነበር የምናወራው። ወትሮ ቢሆን ኖሮ "የማነው ፋራ" እል ነበር። በዚህ አካባቢ ያልተለመደ ወሬ ነበርና። ዛሬ ግን በፀጋ ተቀበልኩት። አነጋገሩ፣ ለሴት ልጅ ያለው ክብር፣ ብቻ ምን አለፋችሁ አኳኋኑ ደስ አለኝ። "ፋራ" አላልኩትም ሲያወራም አልሰለቸሁትም። ከረዥም ጨዋታ በኋላ "ለምን ፊልም አልጋብዝሽም ነገ?" አለኝ። "ደስ" አለኝ። ተስፋ የቆረጥኩበት ሕይወቴ የለመለመም መሰለኝ። እንደወጣት ሴት ሁሉ በሥነሥርዓት ልጋበዝ የምችል መሆኔን ተረዳሁ። "እሺ" አልኩት።

ሰይፉም በሚቀጥለው ቀን ሲኒማ ጋበዘኝ፣ ራት አበላኝና በክብር ሸኘኝ እንደሌላው ሁሉ ወደአልጋው ለምን እንዳልጋበዘኝ ቢገርመኝም በቃል ልገልጸው የማልችል ስሜት በውስጤ አሳድሮ መሄዱ ተሰማኝ። ከሱ ተለይቼ ፔሌ እንደተመለስኩ ፍዝዝ ብዬ ቁጭ አልኩበት ቦታ ጓደኛዬ መጣችና

"ምነው ፈዘሻል?" አለችኝ።

"እንጃልኝ!" አልኳት ዓይኔን እያቅለሰለስኩ።

"ምን? ፎንቃ" እንዳትይኝ? (ፎንቃ ፍቅር ለሚለው የተሰጠ የአራዳ ቋንቋ)

"እንጃልኝ! አልኩሽ እንግዲ ቢገባሽ"

"'በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ፤' አሉ፤ ጠንቀቅ በይ፣ በዚህ ኑሮ ላይ ፍቅር የሚባል ነገር በሽታ ነው። የዛሬ ወንዶች በተለይ እንደዚህ ያለ ቦታ የሚያገኙሽ ወንድ የማያዛልቅ ነው። ፍቅር የቢርጎሽን፣ የኑሮሽን አይከፍልልሽም።"

"ባክሽ እሱ ለየት ያለ ሰው ነው!" አልኳት። "አይምሰልሽ። እንዲህ ቅቤ ሆኖ የቀረበሽ በነፃ ሲሳፈርብሽ ሊከርም ነው፤...ነፍሴ፣ ነቃ በይ?" አለችኝ።

"እስቲ ላየው አይደል?" አልኳት፤

"ጠንቀቅ በይ እቴ" አለችኝ።

ብዙ ሳወራ አልፈለግሁም። ብቻ አንድ ለውጥ በራሴ ላይ አየሁ። እንደከዚህ በፊቱ ዓይኔን እያቁለጨለጭኩ፣ ፈገግታ እያሳየሁ ቡና ቤት የሚገቡትን ወንዶች ወደኔ ለመሳብ አደርግ የነበረው ጥረት ቀነሰ። ቁጭ ብሎ መተከዝ፣ ለስለስ ያለ ሙዚቃ መስማት አብሮም መዝፈን ጀማመርኩ።

ሰይፉ አንድ ሦስት ቀን ሳይመጣ ቀረ። ጭንቅ ጭንቅ ይለኝ ጀመረ። በዚህ ሦስት ቀን ውስጥ ቅልጥፍናዬ ስለቀዘቀዘና ከሌላ ወንድ ጋር ሳልወጣ ስለቀረሁ የቤርጎ የምከፍለው አጣሁ። እንደምንም ብዬ አንዱን እቀላጠፋለሁ ብዬ አንዱን በዓይኔ አግባባሁትና መጠጥ ገዝቶልኝ እጠገቡ ቁጭ አልኩ። አብሮኝ ለማደር ካግባባኝ በኋላ ገንዘብ ሰጠኝና ሌላ ቦታ አልጋ እይዛለሁ ብሎ ወጣ። እሱ እንደወጣ ሰይፉ ሆዬ ከች አለ። ሳየው ደነገጥኩ። ከሩቁ ፈገግታ ሰጠኝ። ሂጄ እጠገቡ "ምነው ጠፋህ?" አልኩት።

"ሥራ በዝቶብኝ ነው፣" አለኝ።

ያ አልጋ ሊይዝ የሄደው ሰውዬ ከመጣ ችግር ይፈጥራል ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። ሕሊናዬ ረብሻ ውስጥ ገባ።

"ለኔ ቢራ፣ ለአንቺ ደግሞ የምትፈልጊውን " አለኝ።

ድንጋጤና ፍርሃት ሰውነቴን እንደወረረው ተነስቼ ለኔም ለሱም ቢራ ይዤ መጣሁ።

"ጉሽ ዛሬስ እግዜር ከሰማይ ወርዷል "አለኝ።

"እንዴት?" አልኩት።

ለአንቺም ቢራ አመጣሽ" አለኝ። ለኔም ቢራ ማምጣቴ አሁን ነው ትዝ ያለኝ። ቀልቤ፣ ሃሣቤ፣ ዓይኔ በሩ ላይ ነው። ካሁን አሁን ያ ሰውዬ መጣ፣ እያልኩ። በዚህ ላይ ደግሞ መንፈሴ ሙሉ በሙሉ የወደደው ሰይፉ ጉኔ ቁጭ ብሏል። "ምነው ገንዘብ ባልተቀበልኩት ኖሮ?" አልኩ በሆዴ። የዓይኔን መቅበዝበዝና የመንፈሴን እረፍት ማጣት ሰይፉ የነቃብኝ መሰለኝ። ይህም ደግሞ አስፈራኝ። ሰይፉን የማስቀየምም አቅም አጣሁ።

በሆዴ "እባክህ ይዘሽኝ ሌላ ቦታ ሂድ" ልበለው እያልኩ ከሕሊናዬ ጋር መሟገት ጀመርኩ። የልቤን፣ የሆዴን አወቀልኝ መሰለኝ "ለምን ሌላ ቦታ ሄደን አንጠጣም፣ ቢራ ከጠጣሽ፤" ሲለኝ እውነት አልመሰለኝም። "እሺ" ብዬ ተስፈንጥሬ ተነሳሁ። ሂሣቡን ከፈለና እያንደረደርኩ ይዤው ወጣሁ። ያኛው ሳይመጣ።

"ሌላ ሰፈር ውሰደኝ" አልኩት።

"ሀብተጊዮርጊስ ድልድይ ምን ይመስልሻል?" አለኝ።

"እሺ" አልኩት።

ታክሲ ተከራይተን ሄድን። ጠጣን፣ አመሸን፣ ከዚያም ሆቴል ተከራየን፣ አደርን። ወደድኩት፤ ምናለፋችሁ ወደድኩት። ጧት ስንነሳና ልንለያይ ስንል ቦርሳውን ከፍቶ ሀያ ብር አውጥቶ ሊሰጠኝ ሲል ብር ብሩን እያየሁ ዓይኔ እንባ አዘለ።

ገንዘቡን ብቀበለው አብሬው ያደርኩት በፍቅር ወድጄው ሳይሆን ለገንዘብ ስል ያደረግሁት ይመስለዋል፤ እኔም በፍቅር ያደረግሁት ሳይሆን የሸረሞጥኩ ይመስለኛል ብዬ ገመትኩ። ባልቀበለው ደግሞ የኔን ያለብኝን ወጪዬን የምሸፍንበት ገንዘብ ላይኖረኝ ነው ብዬም አሰብኩ። ብር ብሯን እያየሁ ዝም ማለቴን ተመልክቶ አንሶኛል ያልኩት መስሎት ነው መሰለኝ እንደገና ቦርሳውን አውጥቶ ሌላ ሃያ ብር ጨመረበት። በእጄ እጁን ያዝኩትና

"አነሰኝ ያልኩህ መስሎህ ነው?" አልኩት። ዓይኔ እንባ አቅርሯል። ዝም አለኝ።

"አይደለም ሰይፉ፤ ብር ብቀበልህ ወድጄህ ከአንተ ጋር ያደርኩ ሳይሆን ለገንዘብ ስል ያደርኩ ይመስልብኛል ብዬ ስለፈራሁ ነው፤" አልኩት።

"እኔ እንደሱ አይመስለኝም"አለ።

"አንተ ባይመስልህ እኔን እንደሱ ይመስለኛል። ስለዚህ እባክህ ይቅርብኝ። ባይሆን እኔን መርዳት ከፈለግህ አብረን ያደርን ዕለት ሳይሆን ሌላ ጊዜ ስጠኝ፤" አልኩት። ዓይን ዓይኔን ትክ ብሎ አየና እቅፍ አድርጎ ሳመኝ። ቁርስ በላንና ዕለቱ ቅዳሜ ስለሆነ ሲኒማ ልጋብዝሽ ብሎ ይዞኝ ሄደ። ያለኝን ሁሉ እሺ አልኩት። ከፊልምም ማታ ስንለያይ ቀስ ብሎ "ኤልሰዬ አሁንስ" ብሎ አርባውን ብር እጄ ውስጥ አደረገልኝ። የቤርጎ ዕዳ ባይኖርብኝ ኖሮ አልወስድም ነበር። ወሰድኩ። በታክሲ ሲሸኘኝ "ነገ እንዳትቀር" አልኩት። እመጣለሁ ብሎኝ ተለያየን። እኔም ወደ ፔሌ ቡና ቤት ተመለስኩ። መሸትሸት ብሎ ነበር። ገና ቡና ቤቱ ስገባ በቦታው የነበሩት በሙሉ ጓደኞዬና ሴቶቹ ብቻ ነበሩና በሙሉ በግልምጫ ጨረሱኝ። ደነገጥኩ። ያለፈው ምሽት ሸውጄው የሄድኩት ብሩን የተቀበልኩት ሰውዬ ችግር እንደፈጠረ ተሰማኝ። የፔሌም ሴቶች የገላመጡኝ በዚሁ እንደሆነ ተሰማኝ። "የፔሌ ቡና ቤት ሴት ከአንዱ ብር ተቀብላ በመሸወድ ከሌላ ወንድ ጋር ትወጣለች" የሚል አባባል ለነሱም እንደሚተርፍ አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው ዓይንሽ ለአፈር ያሉኝ። በዚህ ላይ ባለቤቷ ስትመጣ ሌላ ነገር እንደሚጠብቀኝ በመረዳቴ የፔሌ ቡና ቤት ኑሮዬ ያከተመ መሰለኝ።. . . (ይቀጥላል)

---

ታሪኩ እውነተኛ ነው። እንዲጥም አድርገን ከማቅረብ በቀር የጨመርነው ነገር የለም። ስሞችን ግን ቀይረናል። ባለታሪኳ የምትኖረው አሜሪካ ነው።

---

## ውድ አንባብያን፤-

በሕይወት በተለይም በስደት የገጠማችሁን ገጠመኞቻችሁን ላኩልን። የኑሮን ውጣ ውረድ፣ የስደትን ችግር በታሪክ መልክ ቀርጾ ለማስቅምጥም ሆነ ለሌላው ትምህርት እንዲሆን የሚረዳ ስለሆነ ላኩልን። የጽሑፍ ችሎታ የለንም ብትሉ ታሪኩን ጻፉልንና እንደሚቀርብ አድርገን እናወጣዋለን።

ከዝግጅት ክፍሉ




# ምን ትመክሩኛላችሁ?

አ. ለ.(ስሜን አታውጡት)

ዕድሜዬ 31 ዓመት ነው። እዚህ ከመጣሁ ወደ ስምንት ዓመት ገደማ ሆነኝ። ከአንድ አራት ዓመት በፊት አንዱን አገኘሁና ወደድኩት። እሱም ወደደኝ። አንድ ስድስት ወር ያህል ከወጣን በኋላ ተግባባንና በኑሮም ወጪ ለመረዳዳት ብለን አብረን መኖር ጀመርን። ልጅ መውለድ እፈልግ ነበርና አብረን መኖር በጀመርን በአስረኛው ወር አንድ ወንድ ልጅ ወለድን። አብሮ መኖር እንጂ በውል የተፈራረምነው ጋብቻ የለም። ይህ በዚህ እንዳለ ልጁ በተወለደ በዓመቱ ገደማ ጓደኛዬ ጠባዩ እየተቀየረ መጣ። በርግጥ አልዋሽም በእኔና በልጁ ላይ ፍቅር አለው። ግን እሱ ፖለቲካ ውስጥ ጥልጥል ብሎ ገባ። ስልክ ደውሎ ቢያወራ፣ ስብሰባ ሄድኩ ቢል የፖለቲካ ብቻ ሆነ። ስብሰባ እያለ እያመሻሸም መምጣት ጀመረ። እቤት ውስጥ ከእኔ ጋር ሲያወራ የሚፈልገው ይህንኑ ፖለቲካ ብቻ ነው። እኔ ደግሞ ደስ አላለኝም። ግዜ ወስደን ስለልጃችን፣ ስለኑሮአችን እናስብ ነው የምለው። እሱ ግን ደንታ የሰጠው አልመሰለኝምና አለመግባባት በመካከላችን እየተፈጠረ መጣ። እኔ ጥሩ የቤተሰብ ባል እንጂ ፖለቲከኛ አልፈልግም። ብነግረው ጭራሹኑ እኔን ሊሰብከኝ ይፈልጋል። በዚህ አለመግባባት ምክንያት ይኸው አንድ ቤት ውስጥ እየኖርን መኝታ ቤት ለይተን መተኛት ጀምረናል። እንግዲህ ተግባብተን መኖር ስላልቻልን መለያየቱ ብቻ ነው የሚታየኝ። ይህንኑ ነግሬዋለሁ። እሱ ግን ፖለቲካውን አልተወም፣ አንቺንም አልተውም ይላል፤ ቤቱን ጥዬለት ልጄን ይዤ ልጠፋ ነው፣ ምን ትመክሩኛላችሁ።

## ከዝግጅት ክፍሉ፤-

በመጀመሪያ ነገር ይህን "ፖለቲካ" የምትይውን ነገር ግልፅ ብታድርጊ ደስ ባለን ነበር። ትርጉሙን እየሳተ እየሄደ መሰለን። ጓደኛሽ ፖለቲከኛ ሆነ የምትይው ምን ስለሚያደርግ፣ ወይም ምን ስላደረገ ነው? እንደምታውቂው አገራችን (የአንቺም የሱም የኛም) አገር ትልቅ ችግር አለባት። ለዚህ ላለችበት ችግር መድህኗ እኛው ወገኖቿ ነን። በአሁኑ ግዜ እኛ በአካል ባንኖርባትም አባቶቻችን፣ እናቶቻችን እህት ወንድሞቻችን በአጠቃላይ ወገኖቻችን እየኖሩባት ስለሆነ መንፈሳችን እዛው ነው። ያንቺም እንዲሁ ይመስለኛል። ችግር ላይ ስትወድቅ የሚደርስላት ማነው? እኛው ልጆቿ ነን። እዚያ የሚሆነውን፣ የደረሰውን ሁኔታ መከታተል፤ ችግር ሲፈጠር ለችግሯ ማቅለያ መንገድ መሻት፣ መርዳት፣ ከኛ የሚጠበቅ መሰለኝ። (ወርቃየሁ ከአ.አ. የጻፉልንን ገጽ 4 ላይ እስቲ አንብቢው።) የትም እንኑር የትም ያንን ማንነታችን (Identityአችንን) ልንክደው አንችልም። በተለይ በውጭ አገር ነን የምንለው ልጆቿ በዕውቀትም፣ በኑሮም አገር ቤት ካሉ አብዛኞች ወገኖቻችን ሻል ባለ ሁኔታ ላይ እንገኛለን፣ ቢያንስ ጦማችንን አናድርም። ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቅ ነገር ይኖራል። በየጊዜው በሚፈጠሩ የተለያዩ ዓላማ ባላቸው መሠሪ ፖለቲከኞች ግፊት ሳቢያ ትልቅ ውዥንብር ውስጥ ገብታ፣የአገሪቷ ኤኮኖሚ ቁልቁል እየወረደ፣ ኑሮ እየተወደደ፣ እርስ በርስ የሚያፋጅ ሁኔታ እየተፈጠረ አገር ቤት ያለው ወገናችንን ትልቅ የችግር ማጥ ውስጥ እየገባን እንዳለ መቼም የምታውቂው ነው። ይህ የወገናችን ችግር የኛም ችግር ነው። ምክንያቱም "አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳልና።" እንግዲህ ችግሩን ለመወጣት እኛ በውጪ ያለን ወገኖች ሁሉ የሚጠበቅብንን ለመፈፀም እንዲያስችለን ተቀራርበን መወያየት፣ በሚያስፈልገውና በሚታመንበት መንገድ ሁሉ መርዳት የምንችልበትን መንገድ ለመመካከር፣ ችግሩ ከአቅም በላይ ሲሆን ሌላው የውጪው ክፍል ዕርዳታ እንዲያደርግ ዘዴ መሻት ያለብን ይመስለኛል። በውስጣችን ሁሌ የሚኖር፣ ያለ፤ የዜግነት ግዴታችን ነው ብል ትንሽ ያጠነከርኩ አይመስለኝም። ይህ ደግሞ በሁሉ ያለ ነው። በኛ ብቻ አይደለም።

አሜሪካን አገር ያሉ እስራኤላዊያን፣ ስለእስራኤል ይቆረቆራሉ፣ ፓሌስቲንያንስ ስለፓሌስቲንያ፣ ራሺያኖች ስለራሺያ፤ ሁሉም እዚህ ቢኖሩም ባገሩ ጉዳይ ላይ ይወያያል፣ ይከታተላል የሚችለውን ያደርጋል።እኛ ጋ ሲደርስ ግን የሚቆም አይመስለኝም። እና እንግዲህ ጓደኛሽ ይህ በአገር ቤት ያለው ሁኔታ አስጨንቆት ሃሣብ ገብቶት፣ ተሳትፎ ቢያደርግ 'ጉሽ በርታ" የሚባል ነው። እናቶቻችን አባቶቻችንን እያበረታቱ "ጉሽ የኔ ባትሆን ይቆጨኝ ነበር"እያሉ ነው አገርን አንድነቷን ጠብቀው ለኛ ያስረከቡን። እነሱም እየተወያዩ፣ እየተሳተፉ። እና ይህንን ሁኔታ በማየት "ጓደኛዬ ፖለቲከኛ ሆነ" የምትይ ከሆነ ስህተት አለብሽ፤ ወይም ያልተረዳሽው ነገር አለ ማለት ነው። አገርን ከመውደድ የሚመነጭ ስሜትና፤ ለአገር ፍቅር ስሜት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ

"ፖለቲከኛ" መሆን አይደለም። ከአገር ፍቅር ስሜ ወይም (patriotism) የመነጨ "አገር ወዳድነት" ቢባል ጥሩ ነው። አገሩን የሚወድ ባህሉን ይወዳል። ባህሉን የሚወድ ቤተሰቡን ይወዳል። ቤተሰብ የአንድ አገር መሠረት ነውና። አገሩን፣ ባህሉን መውደዱ እኮ ነው አንቺንም የአገሩን ልጅ እንዲወድ ያደረገው ስለአገሩ ደንታ ባይኖረው ስለባህሉም ደንታ አይኖረውም። ስለቤተሰቡም ደንታ አይኖረውም። ስለዚህ አገሩን ወድዶ፣ ለአገሩ ችግር መፍትሄ ለመሻት አስተዋጽዖ ለማድረግ ሲሯሯጥ ከጐኑ ሆነሽ "አይዞህ በርታ" ማለት የሚገባሽ መሰለኝ። እሱ ብቻውን የሚሯሯጥበትን አንቺ ሩቡን እንኳ ብትሳተፊበት፣ ቢያንስ በውስጡ የሚያቃጥለውን የአገሩን ሁኔታ ሲያወራ ብትሰሚለት ውጪ ውጪ አለ የምትይውን በቀነሰ ነበር። በርግጥ በአንቺ ላይ ለመፍረድ አይደለም። በየጊዜው እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ ያለው የአገራችን ሁኔታ አንቺን ተስፋ አስቆርጦ ሊሆን ይችላል። ስለችግርም ማውራቱ ሰልችቶሽ ሊሆን ይችላል። የሰው አገር ኑሮ ምርር አድርጐሽም ሊሆን ይችላል። አንቺም "ፖለቲካ " ብለሽ የሰየምሺውን ነገር እስቲ አንዳንዴ አውሩ፤ እንዳው ድፍን አድርገሽ አትጥይው። "እኔንና ልጁን እንደሚወድ አውቃለሁ" ብለሻል ታዲያ አንቺም እሱም የመጣችሁበትን፣ እትብታችሁ የተቀበረበትን አገር በመውደዱ እንዴት የሚወዳችሁን አንቺንና ልጁን በማጣት ይቀጣ? ጥሩ ፍርድ ይመስልሻል? እስቲ አስቢው። አንቺም ከሱ በአንቺ ግፊት በዚህ ምክንያት ተለያችሁ፤ ልጁንም ይዘሽ ሄድሽ፤ ቆይቶም ልጁ ሲያድግ "አባቴስ?" ቢልሽ ምን መልስ ልትሰጪው? አገሩን የሚወድ "ፖለቲከኛ" ስለሆነ ፈታሁት "ብትይው በልጅ አዕምሮ ምን እንደሚቀረጽ ከወዲሁ ገምተሽ ይሆን? መልሱን ለአንቺ ትቻለሁ። ባል ሆዬም ለቤተሰብህ ጊዜ ስጥ፤ ቤተሰቡን በጥሩ ሁኔታ ያልያዘ ለአገርም አይጠቅምምና።■

## "አላለልኝ ይሆን. . . "

ከትዝታ አለብኝ (L.A.)

በዕድሜዬ ገፍቻለሁ። አሁን ሰላሳ ስድስቴን ጨርሼ ሰላሳ ሰባት መግባቴ ነው። በአሜሪካን አገር ወደ አስራ ሁለት ዓመት ሊሆነኝ ነው። ተዝናናሁ፣ ጨፈርኩ ሁሉንም አየሁት፤ ትርጉም ግን አልሰጠኝም። ቢሆንም አይቆጨኝም። ትንሽ የሚያሳስበኝ ትምህርት አለመማሬ ነው። ፊት ከነበርኩበት እስቴት ቀየርኩና ሌላ እስቴት ሥራ አገኘሁ። ከአንድም ሁለት ሥራ እየሠራሁ ቤት ገዛሁ። የምርጌጅ ዕዳ እንዳለብኝ አትርሱ። እዛም እዛም ስዘል ከርሜ ረጋ ያለ ሰላም የሰፈነበት ኑሮ መሻት ጀመርኩ ዘግይቼ በተለይ የዕድሜዬ መግፋት ቶሎ ትዳር ካልያዝኩ ልጅ መውለድ የማልችልበት ደረጃ እንደሚያደርሰኝ አስረዳኝ። እና ዘመቻዬን ቀጠልኩ።

እንደወጣትነት ጊዜዬ ቁመናው ዘለግ ያለ፣ የቀይ ዳማ፣ በቃ ምን አለፋችሁ ሴቶች የምንወደው አይነት ቁመና ያለው የአገሬን ጐረምሳ ባየሁ ቁጥር ዓይኔን ባቁለጨልጭ ዞር ብሎ የሚያየኝ ጠፋ። እንዳው ተሳክቶልኝ አንዱን ባገኝ ከኔ ጋር ተደብቆ መውጣትን እንጅ ፊት ለፊት አብሮኝ መታየትን እንደማይፈልግ ከሁኔታው ተረዳሁ። እስቲ የሆነውን ላጫውታችሁ። አንድ የአበሻ ፓርቲ ላይ ነው። ከጓደኞቼ ጋር ሆኜ ይህን ቁመናው ዘለግ ያለ ሰው ሳይ ልቤ ደንገጥ አለ። ቀደም ብዬ እንዳልኳችሁ እንዲቀርበኝ ፈልጌ ዓይኔን ባቁለጨልጭ ስሜት አልሰጠሁትም። እልህ ገባሁና አጋጣሚውን ራሴ ፈጥሬ ድርቅ ብዬ ተዋወቅሁት። "የት እንደሆነ እንጃ የማውቅህ ይመስለኛል " ነበር የመጀመሪያው ጥያቄዬ። ትንሽ ግራ ቢገባውም ገፋ ብዬ አነጋገርኩት። መጀመሪያ ላይ ከአበሻ ሴት ያልጠበቀው ነገር ሆነና ግራ ቢገባውም ኋላ ሞራሌን አይቶ ስልክ ቁጥሬን ጠየቀኝ። ሰጠሁት። ከዚያም በኋላ በሳምንቱ ገደማ ደወለ፤ ትንሽ አወራን፤ ራት ጋበዘኝ። አገኘሁት አልኩ። የዚያኑ ዕለት ማታውኑ እቤት ይዤው ከነፍኩ። ያንን ቁመና ያለውን ገላም ተቋደስኩት። የወደድኩትም መሰለኝ። በቃ ከዚያ በኋላ በሥራ ምክንያት እንደማይመቸው ነግሮኝ የምንገናኘው ሐሙስ ሐሙስ ማታ ብቻ ነበር። ከጓደኞቼ ጋር ላስተዋውቅህ ብለውም "ተይ ጥሩ አይደለም" አለኝ። እኔም ጓደኞቼ ትንሽ ተፌ ብጤ ስለነበሩ ይነጥቁኛልም ብዬ ፈርቼ እንደሆነ እንጃ ብቻ "ዕውነት ነው" ብዬ ሳላስተዋውቀው ቀረሁ። "አበሻ አካባቢ እንድረስ፣ ወሬኞች ናቸው"ሲለኝ እኔም እሺ ብዬ ሐሙስ ሐሙስ ስንገናኝ አበሻ የማይሄድበት መዝናኛ ቦታ እንሄድና አመሻሽተን እቤቴ ይዤው እሄዳለሁ። የሚገርመኝ ነገር ለምን እቤትህ ውሰደኝ እንዳላልኩት ነው። አንድ የማውቃት ልጅ አለች። ታድያ እንዲሁ አንዱን አግኝታ በድብቅ ማንም ሳያውቀው ለጓደኞቿ እንኳ ሳታሳይ እያወጣችው በመጨረሻም አግብታው ስታረግዝለት ይዛው አደባባይ ወጣች። ሰው ሲያይ ጉድ አላት። እኔም በቃ የሚታየኝ እንደዚሁ አድርጌ ይኼን ባል አጣች የሚል "ወሬኛ"ሕዝብ አፉን ለማስያዝ በድብቅ ማድረጌ ጥሩ ነው በማለት እሱ ባለኝ ብቻ ነበር የምመራው። እና ታድያ ይሽውላችሁ በመጨረሻም እንዲህ እየደበቅሁ ሳወጣው የነበረው ባሌ ይሆነኛል ያልኩት ግለሰብ ከስድስት ወር በኋላ ሁለት ልጆች ያሉት ባለትዳር እንደሆነና እኔ ከምኖርበት ከተማ ትንሽ ራቅ ያለ Suburb እንደሚኖር አረጋገጥኩ። ለምን ስልኩን እንዳልሰጠኝ ለምን ቤቱን እንዳላሳየኝ ለምን አበሻ ያለበት ቦታ እንድረስ እንዳላለኝ፣ ለምን ሐሙስ ሐሙስ ምሽት ብቻ እንውጣ እንዳለኝ የገባኝ ኋላ ነው። ለካ የነሚሚዬን አባት ነበር ሳወጣ የከረምኩት እኔም በጣም የቅርብ ጓደኛዬ ከሆነችው እንዲት ልጅ በስተቀር ጉዴን ለማንም ሳላወጣ ሁለተኛ አጠገቤ እንዳይደርስ አስጠንቅቄ ሸኘሁት። አንድ በሉ።

